# የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ዘመን

እንግዲህ፡ እርሱ ፍጹም አልጨረሰውም። እኔም አልኩ፡ “በጋብቻዬ አርፍጄ ነበር... ለመወለድም አርፍጄ ነበር፡ በጋብቻዬም አርፍጃለሁ፡ እንደው ለመቀበርም ባረፈድኩ!” በጣም እንዲዘገይልኝ፡ ዘግየት እንዲልልኝ የምፈልገው ያ ነው።

2 በቤት ውስጥ የሰልክ ጥሪዎች፡ በፍጹም፡ መላወስ አልቻልኩም፡ ሌላ አይደለም። ከዚያም ባለቤቴ እና ሌሎቹም ቀድመው ከሄዱ በኋላ፡ ብዙ ነገሮች ማድረግ ነበረብኝ። እና ከብዙ ቦታዎች የመጡ ብዙ ሰዎች፡ ይጸልያሉ፡ አሁንም ልክ እንደገባሁ፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስለ አንድ ወንድም መገለጥ መጣ፡ ከኋላ የቆምሽው እህታችን፡ የታመመችው፡ መቼም ምን ለማለት እንደፈለግኩ ይገባሻል፡ በል ሂድ፡ ሂድ፡ ሂድ፡ ሂድ አለው። ከጆርጂያ ከመጣችሁ አንዳንድ ጓደኞቼ ጋር እንኳን መጨባበጥ አልቻልኩም እስከ ካናዳ፡ እና ከተለያዩ ቦታዎች ሁሉ ጭምር። እጆቻችሁን መጨበጥ ባለመቻሌ በጣም አዝኛለሁ።

3 እና፡ በነገራችን ላይ፡ ፍሬድ ዛሬ ማታ የት አለ፡ ፍሬድ ሶትማን? ፍሬድ፡ ከካናዳ እየመጣህ ሳለህ፡ የደወልክልኝ ጊዜ፡ በመኪና እንዳትመጣ ያልኩህ ጊዜ ታስታውሰዋለህ? አንተ ግን፡ እንዲሁ መጣህ፡ አደጋ ገጠመህ፡ እንደው... መኪናው ተሰባበረች፡ ሚስቱ እና ቤተሰቡ ሁሉ፡ ጠፍተው ነበር፡ እርሱም አፍንጫው ተሰብሮ፡ ሁሉም ሆስፒታል ገቡ።

4 ቀደም ብዬ ሰወጣ አካባቢ፡ ልክ ከሰዓት በኋላ ላይ፡ ወንድም ቤን እዚህ ቆሞ ነበርና፡ ወደ እኔ መጣ። ሮዜላም ወደዚያ መጣችና፡ “ወደ ቤት ልሄድ ነው፡” አለችኝ።

“ሮዜላ!” አልኳት፡

“ምን ችግር አለ፡ ወንድም ብራንሃም፡” አለችኝ?

“የእውነት ጥሩ ስሜት አይሰማኝም፡” አልኳት። አያችሁ?

እንዲህ አለች፡ “ችግር ይፈጠራል? ”

“አላውቅም። ለእኔ እንደዚያ ይመስለኛል፡ የሆነ ነገር ያሰጠነቅቀናል፡” አልኳት።

5 ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ደወለችልኝ፡ አደጋ አጋጥሟታል። እና ስለዚህ፡ ማንም አልተጎዳም፡ የጌታ እጅ ነው። እና ተንሸራተተች (በሰሜን ሁሉም በረዷማ ነው።) ኢንዲያናፖሊስ ላይ ተንሸራተተች፡ እና **ወደዚህ** መንገድ በፍጥነት መንሸራተት ጀመረች። “ጌታ ሆይ፡ እርዳኝ!” ብላ ጮኸች፡ መኪናው **በዚህ** መንገድ እንደገና ተወዛወዘ፡ ተመልሶ መጣ እና ወደ ትክክለኛው መስመር ገባ፡ እና በጥሩ ሁኔታ መሄድ ጀመረ። መንገድ ላይ ወጣችና፡ እንዲህ አለች፡ “አቤት፡ አቤት፡ ከዚ በመውጣቴ ምንኛ አመሰግናለሁ፡ ምክንያቱም ሌሎች መኪኖች እዚያው መስመር ላይ እየበረሩ፡ ይመጡ ነበርና።” እናም መንገድ ዳር ወጣች፡ እና ከዚያ ወደዚያ ፈቀቅ ብላ ቆመች... የሆነ ነገር፡ ቡና ወይም ሌላ ነገር ልትገዛ የቆመች፡ ይመስለኛል። እና ከመኪናው ከመውጣቷ በፊት፡

እነሆ ሌላ መኪና ከኋላዋ ተጋጨ፡ ሌላውም ከኋላው፣ ሌላውም ከኋላው፡ በቃ ሁሉም ተከመሩ። ለክፉ አይሰጥም እንጂ፡ ትንሽ ግን ደነገጥኩ አለች፡ ጌታን ግን ማመስገን ፈልጋለች፡ እና ምንም ነገር አለመሆኗ እና አለመጎዳትዋን አስባችሁ ጌታን እንድታመሰግኑላት ቤተክርቲያንን ጠይቃለች፡ ቤቷ በሰላም እንድትገባም ቤተክርሰትያንን በጸሎት እንድታስባት ተማጽናለች። እያችሁ፡ ገና አዲስ ሾፌር ነች፡ መንጃ ፈቃዷ ገና መቀበሏ ነው። ስለዚህ፡ እኔም እጅግ አመሰግናለሁ።

6 ነገር ግን እነዚያን የጌታን ማስጠንቀቂያዎች መቀበል ሁልጊዜ ዋጋ አለው። "እንግዲህ፡" አለች፡ "የአንድ ቀን ስራ ያልፈኛል፡" አለች። የአንድ ቀን ሥራ ምንድን ነው? የመኪናውን ጀርባ ለመጠገን ከዚያ በላይ ያስወጣል፡ እያችሁ። ስለዚህ የሚሻለው—ይህን ለማድረግ… ከጌታ ጋር ተጣበቁ። ልክ ነው? የሆነ ነገር ከነገረን፡ ብንታዘዘው ይሻለናል። ምክንያቱም እሱ ሁል ጊዜ ትክክል ነው። አይደል? ሁልጊዜ ትክክል ነው!

7 ኦህ፡ ይኸው፡ ይኼኛው… ልዩ ሳምንት ነበር። ስለዚህ አሰደናቂ ሳምንት ራሴን ለእግዚአብሔር እና ለእናንተ እንዴት እንደምገልጽ አላውቅም። በህይወቴ ከሰበክኳቸው ሰምንት ቀናት በጣም ደስተኛ ከሆኑት መካከል ጥቂቶቹ ናቸው። እውነት ነው። ስለ ጌታ እና ስለ ርኅራኄው ብዛት፡ ለእኛ ስላደረገልን ነገር ሁሉ ብዙ—ብዙ ተምሬአለሁ፡ እንዲሁም መንፈሱ በቤተክርስቲያን ውስጥ ተመልሶ ሲሰራ ማየቴ። እናም ስጦታዎቹ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ እንደገና መሰራት ሲጀምሩ በማየቴ በጣም ደስተኛ ነኝ። እያችሁ?

8 አሁን፡ እንደው አንዴ፡ አንዴ ከራቅሁ፡ የሆነ ሰው መጥቶ የሚገባ፡ እና—የሚበርዛችሁ ይመስለኛል፡ ታውቃላችሁ፡ የሆነ ነገር የሚያደርጉ ይመስላችኋል። ስጦታዎችን ካላከበራችሁ፡ እግዚአብሔር አያከብራችሁም። እያችሁ? ልክ ነው። ማስተካከል አለባችሁ። እና፡ እንዲሆን የምንፈልገው በስርዓት ሲደረጉ ማየት ነው፡ ማለት በልሣን የሚናገሩበት አደራረግ። ቅዱሳት መጻህፍትን መጥቀሴ ብቻ አይደለም፡ ሊሆን ያለ ነገር መኖሩም መናገሬ እንጂ። በዚህ ጉዳይ ላይ እጅግ በትህትና ከጠበቃችሁት፡ እንዲህ መሆን ይጀምራል… ማንም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሥርዓት ውጪ ከሆነ፡ መንፈስ ቅዱስ በትክክል ተናግሮ ማን እንደ ሆነ ይነግራል። በዚያም ደግሞ፡ ተግሣጽ ይ—ይሰማቸውና ወደ መሰውያው ይቀርባሉ። የእነዚያ ስጦታዎች አገልግሎት ይህ ነው።

9 ፓስተራችን ወንድም ኔቪልን፡ ብታዩት ኖሮ፡ አይናፋር፡ እና ኋላ ቀር አይነት ልጅ ነበር። እንደው እላችኋለሁ፡ ስለ ጴንጤቆስጤ ካላችሁማ… ይገባዋል ብላችሁ አትገምቱትም። ተነሥቶ ልሳኖችን ሲተረጉም ትንቢትም ሲናገር ለማየት ግን፡ እውነት እላችኋለሁ፡ ረጅም መንገድ መጥቷል። በትክክል። ለፓስተራችን እንጸልይለት።

10 እና፡ እያችሁ፡ ስጦታዎቹ ቤተክርስቲያን ውስጥ መምጣት ይጀምራሉ። ሌላው ምስኪን፡ ትሁት ወንድም አለ፡ እዚህ ካለ፡ ምናልባት… የሆነ ቦታ ይኖራል። ያለ ይመስለኛል፡ ሁል ጊዜ አይቀርምና። በጣም ትሁት ሰው ነው፡ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካሉ ባለአደራዎች አንዱ ነበር፡ ወንድም ሂጊንቦታን፡ የተወደደ፡ የእግዚአብሔር ሰው። በልሳኖችም የመናገርን ስጦታ እንደ ተቀበለ ስታዩት፡ ወንድም ሂጊንቦታን እንዲህ ያደርጋል ብሎ ማን ገምቶት

ያውቃል? አይናፋር፡ ኋላ ቀር ምስኪን ሰው፡ በማንም፡ ልታወቅ የማይል፡ ከኋላ የሚቀመጥ ሰው ነው። አያችሁ፡ እግዚአብሔር ግን፡ እንዲህ ያለውን ሰው ወስዶ ሊጠቀምበት ይችላል፡ አያችሁ፡ ምክንያቱም በመጀመሪያም፡ ይህን ላድርግ ብሎ አልተነሳምና። ይህን ማድረግ እፈልጋለሁ ቢል ኖሮ፡ ምናልባት ሸሚዙ ርሶ ይወጣ ነበር። በራሱ ማድረግ በማይፈልግበት ቦታ ስለመጣ ግን፡ ምናልባት እግዚአብሔር እሱን ሊጠቀምበት ይችላል።

11 ሌላው ጂኒ ነው፡ እሱም... አቤት፡ ከማስታወቂያው ጀርባ ከኋላዬ በኩል አለ።

12 ልንገራችሁ፡ ብዙ ሰዎች በልሳኖች ሲናገሩ ሰምቻለሁ። እና ሁሉም ከእግዚአብሔር የመጡ ይመስለኛል፡ ምክንያቱም ለአንድ ሰው፡ በሆነ መልኩ ትርጉም የሚሰጥ ከሆነ በቀር ድምጽ ማሰማት አትችሉም። መጽሐፍ ቅዱስ፡ “ትርጉም የማይሰጥ ድምጽ የለም፡” እንደሚል ታውቃላችሁ፡ ማለት ትርጉም ላይኖረው የሚሰማ ድምጽ የለም። አንድን ነገር ማለት ካልሆነ በቀር ምንም አይነት ድምጽ አታሰሙም። ብዙ ድምጾች ሰምቼ ስለነበረ ወደ አፍሪካ እስክሄድ ድረስ እንዴት ይሆናል እያልኩ አስብ ነበር፡ የሆነ ሰው ድምጽ መሆኑን ያስተዋልኩት ያኔ ነው። አንዳንዴ የመላእክት፡ እና ልዩ ልዩ ድምጽ ይሆናል።

13 አይናፋሩ፡ ያልተማረ፡ የሜቶዲስት ቤተክርስትያን የገጠር ሰባኪ፡ ፈሪው፡ ጂኒ ጃክሰን ግን፡ እዚያ—በኤልዛቤት፡ ኢንዲያና፡ በጫካዎቹ ታች ሰባኪ ነው። የተረጋጋ፡ ምንም የማይናገር፡ ያልተማረ አይነት፡ የሚመስል... እንደውም አንዳንዴ እየውና፡ እንዲህ አንሰቼ፡ እንዲህ ወዝውዤ፡ “የሆነ ነገር በል እንጂ፡ ጂኒ፡ እየህ፡ ቁጭ ብለህ እኔን ማየት አቁም፡” በለው ይለኛል።

14 አንዳንዴ ጫካዎቹ ላይ ግንድ ላይ ተቀምጠን፡ እሱም በዚያ ቁጭ ይልና፡ “አይ፡... ችግር ያለው... አይመስለኝም” ይላል።

15 “ኦህ፡ ኧረ ጂኒ፡ አንተ ለእኔ—እጅግ ቀርፋፋ ነህ፡ እየህ። ይኸውልህ፡ ‘እኔ ራሴ ልናገርልህ እንዴ’ ብዬ—እሰባለሁ እየህ፡” እለዋለሁ። እግዚአብሔርም በልሳኖች የመናገር ስ—ስ—ስጦታ ሰጠው፡ በህይወቴ ሁሉ ከሱ የበለጠ ግልጽ የሆነ ልሳን ሰምቼ አላውቅም። አያችሁ?

16 በቤተክርስቲያን ውስጥ እሱን ተመልከቱት። ዛሬ ጠዋት የተናገረች ያቺን ሴት ሌላኛይቱን ሴት እንደማታውቃት አይታችኋል? አንደኛዋ ሌላኛዋን ሳታውቃት፡ ይህችኛዋ፡ ልክ ነገሩ በተነገረበት ድምጽ፡ ሲተረጎምም፡ አናባቢዎቹ ሳይቀር፡ በተመሳሳይ ድምጽ፡ ሰርዓተ ነጥብ፡ በአንድ አይነት መልኩ፡ ተመልሶ መጣ። መልእክቱም፡ ለቤተ ክርስቲያን ፍጹም የሚመጥን ነበር። እንዴት እንደሆነ አያችሁ? አሁንም፡ እግዚአብሔርን ማመስገን ይገባናል። እንግዲህ፡ አንገታችሁን አታደንድኑ። እንዲህ ከሆናችሁ፡ እራሳችሁን ታዋርዳላችሁ፡ ዲያብሎስ ይይዛችኋል። ትሁታን ሁኑ፡ “ጌታ ሆይ፡ አቤቱ ሰውረኝ፡ ጊዜው ሳይደርስ አትግለጠኝ፡” በሉት።

17 ከትዕዛዝ እንድትወጡ በፍጹም አያደርጋችሁም። አንዳንዴ፡ ትወጣላችሁ፡ ያም—ያም ችግር አይኖረውም። ምክንያቱ፡ ስትወጡ፡ ፓስተሩ ይ—ይነግራችኋል። አያችሁ፡ ስጦታዎች—በእነዚህ አይነት ሁኔታዎች... በስብከት ጊዜ ብቻ አይደሉም። እንደውም ብዙ ጊዜ፡ ስጦታዎች በቤተክርስቲያን ውስጥ በጥሩ ሁኔታ ሊሰሩ ከተፈለገ፡ ከዋናው አገልግሎት በፊት ቀድማችሁ

እንድትገናኙ እናደርጋለን፡ አያችሁ፡ ጌታ ከእናንተ ጋር እንዲሰራ ፍቀዱለት፡ ምክንያቱም በዚህ መልኩ ከተደረገ በጭራሽ አይረባበሽም። ማለት፡ በጉባኤ መካከል እያለን ከሆነ፡ አንዳንዴ ለጥቂት ጊዜ መታገስ ይኖርባችኋል። እግዚአብሔር መልእክት ካለው፡ የሆነ ቦታ ወይም በሆነ ነገር መልኩ ያመጣዋል፡ አያችሁ፡ እንዲያደርገው ፍቀዱለት፡ ይሁን እንጂ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ይሁን። ምናልባት እኛ ለማስተማር በምንሞክራቸው፡ ወንድም ኔቪል እነዚህን ጉዳዮች ያስተምር ይሆናል። አቅማችን በፈቀደው እኔም አብሬው ሆኜ፡ ሁለታችንም እናሳያችኋለን፡ ይህም ጥቅም ላይ መዋል እንዴት እንደሚገባቸው ለማሳየት ነው።

18 ፖላንዳዊው ወንድሜ፡ ጥሩ ስሜት እየተሰማህ ነው? በጣም ጥሩ። ኦህ፡ ጌታ እንዴት ባረከው መሰላችሁ! ከሰምንት ዓመታት በፊት፡ የሆነ ነገር እንደሚከናወን ነገረው። በሁሉ ነገር ግራ ተጋብቶ ነበር፡ ወግ አጥባቂ የሥላሴ ተከታይ ነበር። በቀደም ለት፡ ጌታ እንዲህ ብሎ ነገረኝ "እነሆ ባለ ጥቁር ጸጉር፡ እና ቡናማ አይኖች ያሉት፡ ወፈር ያለ ሰው ይመጣል። እነሆ ወደ አንተ ልኬዋለሁና፡ አትመልሰው አለኝ።" እኔም እሱ ግራ የተጋባበት አንድ የመፅሃፍ ክፍል መረጥኩና፡ ቁራጭ ወረቀት ላይ በደንብ አሰፈርኩት። ከአፍታ በኋላ መጣ።

"አንተን ማየት የፈለገ አንድ ሰው ውጭ ቆሟል፡" አለችኝ ሚስቴ።

እኔም "እሱ ነውና፡ ግባ በይው፡" አልኳት።

19 እርሱም—በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ውስጥ… የተነገረውን ነገረኝ። በሕዝቦቹ መካከል መልእክቱን፡ እና ሌላውን ሁሉ እንዴት አጥብቆ እንደያዘ፡ እና እንዴት እንዳመነ፤ ቢነቅፉትም እንኳ፡ ታምኖ ጸና። ከተወሰነ ጊዜ በፊት፡ በስብሰባው ላይ፡ ሰሙን ጠርቼ፡ እንዳነጋገርኩት ነግሮኛል። ያንን ሰም እንዴት እንደጠራሁ እንኳን፡ አላውቅም። እሱ እንዳለው ከሆነ—በጉባኤው ላይ፡ የሰሙን ፊደል፡ ወይም የሆነ ነገር ጠራሁ። ፊቱ በሽፍታ የተወረረ ህጻን ልጅ በክንዶቹ ላይ አቅፎ እንደነበረ ይናገራል፡ እና ህጻኑ ሙሉ በሙሉ ተፈወሰ፡ በቃ በሙላት። አቤት ጌታ'ኮ…

20 እኔም አልኩት፡ "እንግዲህ፡ አሁን የሚያስፈልግህ ነገር ወደ ቤተ ክርስቲያን ወርደህ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መጠመቅ ነው።"

21 ቀደም ብዬ በተራራው አናት ላይ አገኘሁት፡ ምክንያቱ ወርዶ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ስለ ተጠመቀ። አሁን በደንብ ረክቶ፡ ደስ እያለው፡ ወደ ቤቱ ይመለሣል። ከእነዚህ ቀናት በአንዱ በፖላንድ እንደሚተረጉምልኝ ተስፋ አደርጋለሁ፡ እንዲሁም በጀርመን፡ እና፡ በእነዚያ አገሮች ዙርያ። ጌታ ይባርክህ፡ ወንድሜ።

22 ጌታችን ብዙ ታላላቅ መልካም ነገሮችን አድርጓል! ከምስራቅ፡ ከምዕራብ፡ ከሰሜን፡ እና ከደቡብ፡ ውድ ልጆቹን እየመራ ነው፡ ምህረቱ—ለማየት ብቻ፤ አንድ እንዲሆኑ፡ ሰቦ ሲያወጣቸው፡ ሲያንቀሳቅሳቸው። ብዙ የሚባል ነገር አለ!

23 አሁን፡ ይህን እንዳትረሱ፡ ቀጣይ እሁድ ማታ፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ ቀጣይ እሁድ ማታ ላይ፡ ይህ ይኖረናል… ይቅርታ እሁድ ጥዋት፡ ማለቴ ነው፡ የፈውስ ጉባኤ ይኖራል። በዚያ ላይ ያን ያልኩበት ምክንያት፡ ምናልባት ለእሁድ ጠዋት በጣም ብዙ ነገር የሚኖረን ከሆነ ወደ እሁድ ማታ ላይ አሸጋግረዋለሁ፡ አያችሁ።

ሁሉንም እሁድ ጠዋት በአንድነት መጨረስ ከቻልኩ ግን፡ እንግዲያውስ፡ መልካም ነው።

24 እሮብ ምሽት የመካከለኛው ሳምንት የጸሎት ስብሰባ ይኖረናል። እንግዲህ፡ እዚህ አቅራቢያ ለምትገኙ ሰዎች፡ እናንተ ሰዎች እዚህ ተሰብሰቡ፡ የጸሎት ጉባኤ አድርጉ። እንዲያመልጣችሁ፡ በደንብ ያዙ፡ አያችሁ። ጸልዩ፡ እግዚአብሔርን አጥብቃችሁ ፈልጉ። ወግ አጥባቂነት በመካከላችሁ እንዲገባ ፈጽማችሁ አትፍቀዱ። ጠብቁት... ውሸትን የምትቀበሉበት ብዙ እውነት አለ፡ አያችሁ፡ በስህተት ጎን—አትስለፉ። እውነትን ጠብቁ።

25 ለብዙ ዘመናት ስሰማው የኖርኩትን፡ የወንድም ሩሰል ክሪችን "አሜንታ" ይሰማኛል። በቀደም ማታ ላይ በልሳን ስትናገር የነበረችው ፓቲ እንደነበረች ነገረውኛል። የት አለሽ፡ ፓቲ? ያቻትና፡ የኔ ማር? እሰይ፡ አቤት፡ እንደው ባያት እንኳን አላስታውሳትም። ይህች ልጅ፡ እዚህ ቦታ ላይ በክንዶቼ አቅፌ ለጌታ አሳልፌ የሰጣኋት ልጅ ናት። "አሁን ወጣት ሴት ነች፡" ሚዳ እንዳለች፡ "በአሥራዎቹ-ዕድሜ ላይ የምትገኝ፡ ቆንጆ፡ ልጃገረድ ናት፡" የመንፈስ ቅዱስ ኃይል፡ በእሷ የሚናገር... ሩሰል፡ አንተ ባለጸጋ ሰው ነህ። በእውነት፡ ነህ።

26 እህት ክሪች የት ነች? አላየኋትም። መጥታለች? ማዶ ላይ። ኦህ፡ እህት ክሪች፡ እግዚአብሔር እንዲህ አይነት ልጅ ስለሰጠሽ ምንኛ አመሰግናለሁ፡ አየሽ፡ ምስጋንዬ—ምን ያህል እንደሚሆን አታውቂም። በአሥራዎቹ-ዕድሜ ውስጥ ያሉ ልጃገረዶች እየተሳለቁ እና እየሳቁ በሚሄዱበት ዕድሜ፡ እንደምታውቁት፡ ወጣት ወንዶችም ብዙ ከንቱ ነገሮች፡ የዳክ ጸጉር አቆራረጥ እና ልዩ ልዩ ነገሮች፡ ሌላም ያደርጋሉ፤ ይቺ ህጻን ልጅ ግን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል፡ እዚህ በልሳን ትናገራለች። ኦህ፡ ማይ!

27 እምም! ዛሬ ማታ ሰንቶች፡ የጴንጤቆስጤ ሰባኪዎች የሆኑ ሰዎች፡ በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ የምትገኘውን ሴት ልጃቸውን እንዲህ እንድትሆንላቸው፡ ከሮክ-እና-ሮል ፓርቲ ለማውጣት፡ ህይወታቸውን ምንኛ በከፈሉ!

28 እንደው—እንደው ወንድሜ፡ አክበረህ ያዘው። በኢንተርስቴት ውስጥ ምን እየሰራህ እንደሆነ አውቃለሁ፡ እኔም ተመሳሳይ ነገር አደርጋለሁና፡ ብዙ ከባድ ቀናት ሰርቻለሁና፡ ይሁን እንጂ፡ ወንድሜ... ልጆችን ለማሳደግ ነው። ነገር ግን አስታውስ፡ እግዚአብሔር ታማኝ ነው፡ ይሸልማልና። አዎን፡ በትክክል! "እከፍላለሁ ብሏል።"

29 እግዚአብሔር ይባርክህ፡ ፓቲ። የኔ ማር፡ እንደው ባይሸም፡ የማውቅሽ አይ—መሰለኛም፡ ይሁን እንጂ ይህን ቀጥተኛ መንገድ በፍጹም አትልቀቂው፡ የኔ ማር። ልክ እንደ ወርቃማ አፕል፡ ቶሎ እንዳይቆመጥጥብሽ፡ ዲያብሎስ ምንም ነገር በአንቺ ላይ እንዲያሰቀምጥ—ፈጽመሽ አትፍቀጂለት፡ እሺ። ነገሩን ጣይው እና እንዲሁ ተይለት። ዓይኖችሽን በክርስቶስ ላይ፡ በመሰቀሉ ላይ ትከይ። ሰዓቱ ቀርቧልና፡ ቀጥይበት። አየሽ?

30 ማለት የምችላቸው ብዙ ምክር፡ እና የእግዚአብሔር በረከቶች ነው። ብዙዎችን መጎብኘት አልቻልኩም፡ በዚህ ሳምንት ከሃምሳ ለሚበልጡ ሰዎች አልጸለይኩም፡ ይመስለኛል፡ ውጣ ውረዱ ሁሉ፡ ድንገተኛ የሚላኩ ነገሮች፡ እና ልዩ ልዩ ነገሮች ነበሩ፡ ይሁን እንጂ ጥናት ላይ ተጠምጄ ነበር። አሁን ግን፡

በሚቀጥለው እሁድ፡ ለሰዎች እንጸልያለን፡ ጌታም እንዲወርድ እና ታላቅ ኃይል እንዲሰጠን እንለምነዋለን፡ በሚቀጥለው እሁድ ጠዋት ጌታ ቢፈቅድ፡ ራሱን ይግለጥልን።

31 ኦህ፡ ይሄኛው የቤተክርስቲያን ዘመን መጀመራችን ደስ አይለኝም ምክንያቱም ይህ የመጨረሻው መሆኑን ስለማውቅ ነው። አሁንም፡ የሰባቱ የቤተክርስቲያን ዘመን ማጠቃለያ—የሚሆነው፡ በዚህኛው ነው። ተባርካችሁበታል? [ጉባኤው "ኣሜን፡" አለ።—አርታዒ።] አሁን፡ አስታውሱ፡ መጀመሪያ ላይ እንዳልኩት መጨረሻ ላይ ይህን እላለሁ፡ ምናልባት በብዙ ነገሮች፡ ከእኔ ጋር የማትስማሙባቸው ብዙ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ፡ ይህን ግን በእኔ ላይ አትያዙብኝ፡ አያችሁ፡ እንዲሁ፡ ውደዱኝ፡ ምክንያቱ የምታደርጉት እና የምትሉት ነገር ምንም ለውጥ አያመጣም፡ እኔም ስለእናንተ ተመሳሳይ ነገር አስባለሁ፡ ሌላ፡ ተጨማሪ ነገር ካለ፡ አያችሁ፡ ቢኖር፡ ስለ እናንተ ማሰቤ ነው። እኔ ግን እወዳችኋለሁ፡ እግዚአብሔር ያውቃል፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ስም የሚጠራ ሆኖ እኔ የማልወደው ሰው ሊኖር አይችልም። አያችሁ?

32 ምንም እምኳን ፈጽመን ባንስማማም፡ ምንም አይነት ግዴለሽነት እና መራራነት እንዲኖርብኝ አልፈልግም። በማዕድ ተቀምጠን ፓይ ስንበላ፡ አንዱ አንደኛውን ሌላውን፡ ሌላ ዓይነት እንደሚበላው፡ እዚህ የምናደርገው ነገርም ያው እንደዚያው አይነት ነው፡ አያችሁ። ኅብረት ስለማድረጋችን ስንመጣ ግን፡ እርስ በርሳችን እንዋደዳለን። የማንዋደድ ከሆነ፡ መዋደድ አለብን። እንዲህ ካልሆነ… ያንን እስካላደረግን ድረስ በእግዚአብሄር ነገር ፈቀቅ አንልም።

33 ይህን አስቡ፡ የስጦታዎች ሁሉ ትልቁ ስጦታ ፍቅር መሆኑን አትርሱ። "በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገርም፡ ሰውነቴ መሥዋዕት ሆኖ ቢቃጠል፡ እውቀትን ሁሉ ባውቅ፡ ወዘተረፈ፡ ከንቱ ነኝ። ስለዚህ… ፍጹም የሆነው ግን፡ እርሱም ፍቅር ነው… " ሁሉም መንፈሳዊ ስጦታዎች በፍቅር ቡኮ ካልተለወሱ፡ አይጣበቁም። ሌላ አይነት ማጣበቂያ ሁሉ ይሰባበራል፡ "ፍቅር ግን ለዘለአለም ይጸናል።" አያችሁ፡ አንደኛ ቆሮንቶስ 13 ነው።

34 አሁን፡ ዛሬ ማታ፡ ወደዚህ ታላቅ የቤተክርስቲያን ዘመን ስንገባ። ኦህ፡ ማይ! ምናልባት (ዛሬ ማታ) ዘጠኝ ከሩብ ላይ ነን። አሁንም ሰውን ሁሉ የምናስቀምጥበት በቂ ቦታ ባለ ማዘጋጀታችን ይቅርታ እንጠይቃለን፡ ቢሆንም… ሁላችሁንም ለማስቀመጥ፡ ማለቴ፡ ለሁላችሁ የሚሆን ወንበር፡ አሁን ባይኖረንም፡ ምናልባት ሌላ ቀን ይኖረናል።

35 አሁን ግን አንድ ውለታ እንድትውሉልኝ እጠይቃለሁ። አቋሜን እና አንድ ቀን የሚያስከፍለኝ ዋጋ ምን እንደሆነ ታውቁታላችሁ፡ አያችሁ፡ ጊዜውም ሩቅ አይደለም። አያችሁ? አሁን፡ እንድታደርጉልኝ የምፈልጋችሁ ይህ ነው፡ ሁል ጊዜ ጸልዩልኝ። አያችሁ፡ በቅንነት መሄድ እንዴት እንዳለብኝ በምችለው ሁሉ በቅንነት መኖሬን፡ አትርሱ። ከእንግዲህም ህጻን ልጅ አለመሆኔን አውቃለሁ፡ ኃምሣ-አንድ አመቴ ነውና። እኔም—ይህ ሲሆን… እግዚአብሔር እስኪጠራኝ ድረስ መሄድ አልችልም። እና እንድሄድለት በሚፈልገኝ ሁሉ እሄዳለታለሁ፡ ያ ነው። አያችሁ? ምንም ቢሆን ግን፡ ቅን መሆን ግድ ይለኛል። አንዳንዴ የብቸኝነት ጉዞ እንደሆነ አውቃለሁ፡ ይሁን እንጂ እርሱ አብሮ ካለ፡ ምን ልዩነት ይፈጥራል? አያችሁ?

36 አሁን፡ ወደዚህ ታላቅ የቤተክርስቲያን ዘመን ከመግባታችን በፊት፡ ለአፍታ ያህል፡ ለጸሎት መቆም እንችል እንደሆነ እሰባለሁ። እንድታፍታቱ እና ሞቶት እንዲሰማችሁም ይረዳችኋል። በመዝጊያ አገልግሎት፡ ያላችሁ... እስኪ በእግዚአብሔር ፊት መታወስ የምትፈልጉ ሰንቶች አላችሁ? እጃችሁን ወደ እግዚአብሔር አንሡ፡ "አቤቱ ጌታ ሆይ፡ በዘመኑ ፍጻሜ፡ አስበኝ። የህይወት ማብቂያ ላይ፡ አስበኝ።"

37 የሰማይ አባታችን፡ ምስጋናችንን ለመግለጽ በቂ ቋንቋ የለንም በዚህ ባለፈው ሳምንት በመካከላችን ስለ ነበረው ስለ ሕያው እግዚአብሔር መገኘት፡ እና ከአንተ ስለተማርናቸው ነገሮች፡ በነበረን ጊዜ ሁሉ ራስህን ገልጠህልናል፡ አቤቱ ቃልህንም እጅግ ግልጽ አርገህልናልና። እነሆ አንተን እጅግ ጠብቀንሃል፡ እነሆም——ፍቅራችን ለአንተ ለመግለጽ ጥረናል፡ ይሁን እንጂ፡ ጌታ ሆይ፡ አልተቻለንም የሟች አንደበቶች ይህን አይችሉትምና። ለ-... እኛንም ለማዳን፡ እነሆ... አንተን የምንራብበት ነገር ሰጥተህናል። በቃልህም እንዲህ ተብሎ እንደተጻፈ፡ "የሚራቡ ብፁዓን ናቸው፡" (መራብ፡ ብጽዕና ነውና) "ጽድቅን መራብ እና መጠማት።" ከዚያም ያንን ታላቅ ጥቅስ አስከትለህ አልህ፡ "ይጠግባሉና!" ስለዚህ፡ ጌታ ሆይ፡ ያንን እናምናለን። ጉድለታችንን ይቅር በለን።

38 እና ዛሬ ማታ ወደዚህ የመጨረሻ የቤተ ክርስቲያን ዘመን... ይህም ሎዶቅያ ውስጥ፡ ስንገባ ሳለን፡ ቅዱሳት መጻሕፍትንና ታሪኩን ሰንመለከተው ዘወትር በትክክል ይስማማል። ስለዚህ፡ አባት ሆይ፡ ከዚህ ከመጨረሻው ዘመን፡ ከተናገርከው ከታላቅ ትንቢትህ የወጣውን ጥቅስ እናውቃለን፡ ይህም ልክ እንደ ሌሎቹ ስድስት ዘመናት ይሆናል። አባት ሆይ፡ ዛሬ ማታ መንፈስ ቅዱስ ወደ እኛ እንዲመጣ እጸልያለሁ፡ አሁንም፡ ቀሪው ላይ አንተን ሰንጠባበቅ አቤቱ ባርከን። በኢየሱስ ስም። አሜን። አረፍ በሉ።

39 ጌታ ቢፈቅድ፡ መጽሐፉ... በተቻለ ፍጥነት ይዘጋጃል። ወንድም ሊዮ ከማግኔቲክ ቴፕ እየጻፈው ይገኛል፡ ይህ የሚሰራጨው... ወደ ሌላቸው ይሆናል፡ ከዚ ወደ ጽሑፍ፡ ከዚያም ወደ መጽሐፍ።

40 እና በነገራችን ላይ፡ **ከአልኮል ሱሰ ነጻ የወጣችው** ሮዜላ፡ መጽሐፏ በቅርብ ቀን ያልቃል፡ መንፈስ ቅዱስ በጉባኤ ውስጥ እንዴት እንደጠራት፡ ሁላችሁም ታሪኳን ታስታውሳላችሁ። በአራቱ ታላላቅ የአልኮል ተቋማት ተሰፋ ተቆርጦባት... እንደነበረች፡ በቺካጎ ውስጥ ከነበረው ሆስፒታል እንድትወጣ ተገዳለች፡ ጌታ ኢየሱሰ ግን፡ በቅጽበት፡ ሁሉንም ከውስጧ አስወገደው። እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያድን ለሰዎች እየተናገረች፡ ከእሰር ቤት ወደ ሌላ ቦታ ትዞራለች፡ ከአልኮል ሱሰኞች ጋር ትነጋገራለች ወዘተ። በምስክርነቷ፡ ብዙ ሰዎችን ለክርስቶስ የምታሸንፍ... ሆናለች።

41 አሁን፡ የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ ማን እንደነበረ ትነግሩኛላችሁ? ኤፌሶን። ሁለተኛ? ሰምርኔስ። ሶስተኛ? ጴርጋሞስ። አራተኛ? ትያጥሮን። አምስተኛ? ሰርዴስ። ሰድሰተኛ? ፊላዴልፊያ። ሰባተኛ? ሎዶቅያ።

42 የመጀመሪያው ኤፌሶን፡ ከ 55 እስከ 170 **ዓ.ም.** ገደማ ነበረ። ሰምርኔስ፡ ከ170 እስከ 312። ጴርጋሞስ፡ 312 እስከ 606። ትያጥሮን፡ 606 እስከ

1520። ሰርዲስ፡ 1520 እስከ 1750። ፊላዴልፊያ፡ 1750 ወደ ስድሰት... 06 ድረስ፡ አሁን፡ የሎዶቅያ ዘመን ይጀምራል፡ ይደረባል፡ እና ትናንት ማታ በመጠኑ ሲደረብ አይተናል። አሁን፡ ዛሬ ማታ፡ የሎዶቅያውን ፍጻሜ እናያለን።

43 የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን የተጀመረው በ1906 **ዓ.ም**. ነው። እኔም በግምቴ... እንግዲህ፡ ለእናንተ በቴፕ ስለምትሰሙት እላለሁ፡ "ግምት፡" ማለቴን እንዳትረሱ። ይሆናል አልልም፡ ግን በ1977 እንደሚያልቅ እገምታለሁ፡ ማለት ቤተክርስቲያን ሙሉ በሙሉ ወደ ክህደት ትገባለች እናም ከእግዚአብሔር አፍ ትተፋለች። ስለዚህ ዳግም ምጽአት፡ ወይም የክርስቶስ መነጠቅ፡ በማንኛውም ጊዜ ሊመጣ ይችላል። እንግዲህ፡ በአንድ አመት፡ ወይም በሃያ አመታት፡ ወይም ደግሞ በመቶ አመታት ግምቴ ስህተት ሊሆን ይችላል። መቼ እንደሆነ አላውቅም... እኔ ግን በራእይ እንዳሳየኝ መሰረት፡ ያንን ጊዜ በመጠቀም ግምቴን አሰቀምጣለሁ፡ እንደ አካሄዱ አይነት፡ በ 33 እና በ 77 መካከል ሊሆን ይችላል። ቢ—ያንስ፡ ይህች ታላቅ አገር አድቅቆ የሚበታትን ጦርነት ይመታታል፡ አያችሁ። ያም በጣም በቅርብ ነው፡ እጅግ በቅርብ ነው። እና እኔ ልሳሳት እችላለሁ፡ ግምቴ ስለሆነ። ሁላችሁ ተረድታችሁኛል? እስኪ "አሜን" በሉ። [ጉባኤው "ኣሜን።" አለ—አራታዒ] አያችሁ?

44 ነገር ግን ጌታ በ 33 ላይ፡ ማለት በ 1933 ላይ፡ስለ ታላቋ ሴት ራዕይ አሳይቶኛል፡ ጋዜጣ ላይ ወጥቷል። ይህም እንዴት "በሩዝቬልት ጠንቅ... ዓለም ወደ ጦርነት እንደሚመራት።" እንዴት "ሙሶሎኒ የመጀመሪያውን ወረራ በኢትዮጵያ እንደሚያደርግ እንደሚይዛትም፡ በአሳፋሪ ፍጻሜ እንደሚጠፋ።" ከዚያም በመቀጠል "ሶስት ኢዝሞች፤ ናዚዝም፡ ፋሺዝም፡ እና ኮሙኒዝም፡ ሁሉም በኮምኒዝም ውስጥ ይወድቃሉ።" እስኪ ይህን ስናገር ስንቶች ታስታውሱኛላችሁ፡ በተደጋጋሚ፡ እንዲህ ስነግራችሁ፡ ገብቷችኋል፡ "ሩስያን ተመልከቷት! ሩስያን ተመልከቷት፡ የሰሜኑ ንጉስ! ሩስያን ተመልከቷት!፡ የሰሜኑ ንጉስ! ሩስያን ተመልከቷት፡ የሰሜኑ ንጉስ!"? እይህን ሰናገር ሰንቶች ሰምታችሁኛል፡ እስኪ፡ እስኪ አወዛውዙልኝ? ከቀደምት-መካከል፡ አያችሁ፡ የቤተ ክርስትያኒቱ መጀመሪያዎቹ ዘመናት ላይ። እንዲሁ ቆሜ ደግሜ ደጋግሜ እያወዛወዝኩ፡ "ሩስያን ተመልከቷት፡ የሰሜኑ ንጉስ! ምን እንደሚያደርግ፡ ተመልከቱ፡ እነዚያ ሁሉ ኢዝሞች በሩስያ ይዋጣሉና።"

45 ከዚያም፡ እንዲህ አልኩ "ይህች አገር በስተመጨረሻ ከጀርመን ጋር ጦርነት ትገጥማለች። ጀርመንም በሲሚንቶ ግንብ ትገነባለች።" ያም ደግሞ የማጊኖት ድንበር ነበር፡ መገንባት ከመጀመሩ አሰራ አንድ አመት በፊት፡ ከአሰራ አንድ አመት በፊት። "አሜሪካኖች በዚያ ድንበር ላይ አስቃቂ ድብደባ ይፈጽማሉ፡" ብያለሁ። ከእነዚህ ወንድሞች መካከል አንዳንዶቹ በዚያ ድንበር አጠገብ ነበሩ፡ እነ ወንድም ሮይ ሮበርሰን እና ሌሎቹ፡ ምን እንደተፈጠረ ጠይቋቸው። በትክክል ነበሩ። እሺ። "በመጨረሻ ግን፡" "እኛ እናሸንፋለን በእኛ እና በጀርመን መካከል ባለው ጦርነት ከአሸናፊዎች አንዱ እንሆናለን፡" ብዬአለሁ።

46 ከዚያም፡ እንዲህ አልኩ፡ "እነሆ ከእነዚያ ቀናት በኋላ፡ ሳይንስ በእርግጥ ያድጋል።" አደጉም፡ የአቶሚክ ቦምቡን እና ሁሉንም ነገር ሠሩ። "በእድገታቸውም ወቅት፡ እነሆ የሚሰሯቸው... መኪኖች ያለማቋረጥ

እንቁላል መምሰል ይጀምራሉ፡” ብያለሁ። እና በ 1933 ትልቁን ባለ ኮፈኑ ታስታውሳላችሁ፡ ትልቁ የኋላውን አካል እንዲህ ይወርዳል፡ ስፔር ጎማቸው ከኋላ ነው? አሁን እንዴት እንደሆኑ፡ አያችሁ፡ እንደ እንቁላል፡ ውልውል ያሉ ናቸው፡ አያችሁ። እንዲህም ብዬ ነበር፡ “በመጨረሻም መሪ የሌለው መኪና ይሰራሉ። አንድ ቤተሰብ... በሉት፡ ጣራው መስተዋት በሆነ-መኪና ውስጥ፡ ‘መንገዱ፡’ ምርጥ ትልቅ ጥሩ- መልክ ያላቸው መንገዶች እና ጥሩ መኪና ላይ ሲኳዙ አይቻለሁ። ተቀምጠው፡ እርስ በርሳቸው እየተያዩ፡ መኪናው በራሱ ሲሽከረከር ነበር፡ በኩርባዎች እና በሁሉም ላይ በትክክል ይሄዳል።” መኪናውም አሁን ደርሰውበታል፡ ሰርተውታል። መኪናውን ደርሰውበታል። ያን ጊዜ ብያለሁ፡ “እነሆ፡ በዚያ ቀን ሳይነስ ታላቅ እደገት ያሳያል!”

47 ሌላውም እንዳልኩት፡ “እነሆ እየሁ... ሴቶች ምርጫ ላይ እንዲሳተፉ ይፈቅዳሉ አሁንም ተፈቅዷል። እና ድምጽ በመስጠታቸው፡ ከእነዚህ ቀናት ውስጥ አንዳንዶቹን የተሳሳተ ሰው ይመርጣሉ።” በባለፈው ምርጫም እነሆ እንዲሁ አደረጋችሁ። ኬኔዲን ያስመረጠው የሴቶች ድምጽ ነበር። ይህን ማወቅ የቻልነው፡ አያችሁ፡ ኤፍቢአይ ካጋለጣቸው፡ ጠማማ ማሽኖች እና ሌሎች ነገሮች ተነስተን ነው። እስኪ እንዴት ቢሆን ነው... እንዴት አንድ ነገር እምኳን አያደርጉትም ወይ? ለምን ዝም ይባላል? አሃ! ሰው ሰራውን እንዳያጣ በመፍራት። አያችሁ፡ እስከ ሰሩ ድረስ የበሰበሰ፡ የፖለቲካ ሰብሰብ ብቻ ናቸው። ይኸው ነው። በትክክል!

48 ምንም ነገር—ምንም... ምንም፡ ይቅርታ የለም። አገሪቱ ውስጥ መዳን የለም፡ በየትኛውም አገር መዳን የለም። መዳን በኢየሱስ ክርስቶስ እና በእርሱ ብቻ ነው! ኧሃ-ሃህ! ልክ ነው። አሁን፡ ስለ አሜሪካ አመሰግናለሁ። ከካናዳ በቀር... በዓለም ውስጥ ካሉ ከማንኛውም ቦታ፡ እዚህ ብኖር እመርጣለሁ። ምክንያቱ እንደምናውቀው፡ ካናዳ እና ዩናይትድ ስቴትስ መንትዮች ናቸው፡ ጎርቤት አገሮች፡ ድንቅ አገሮች፡ ነገር ግን ከ—ከማውቃቸው ሌሎች ቦታዎች ሁሉ ይልቅ እዚህ መኖር እመርጣለሁ ብዬ እምናለሁ፡ ምክንያቱም ቤቴ ነው። አሜሪካዊ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ፡ ስለዚህም አመሰግናለሁ። ነገር ግን እላችኋለሁ፡ በእርግጥ ዳግም ሪቫይቫል ያስፈልጋታል፡ በእርግጥም ያስፈልጋታል። ቢሆንም አታገኘውም እንጂ! በጭራሽ፡ ጌታዬ። እንደገና አትነሣም! በጭራሽ፡ ጌታዬ። ጠፍታለች! ከአምስት አመት በፊት፡ በቺካጎ ታስታውሳላችሁ፡ በቴፕ ውስጥ ተቀድቷል። ገብቶሃል፡ ጂን። “በዚህ ዓመት ይቀበላሉ፡ ወይም ያለማቋረጥ ይወድቃሉ፡” ብዬ ነበር። እነሆም ተቀብለውታል፡ አያችሁ፡ ፍጻሜዋ እስኪደርስ ድረስ እንዲሁ ያደርጉታል።

49 ይሁን እንጂ እነሆ አንድ ታላቅ ሴት አለች! እንግዲህ፡ አስታውሱ! ይህም፡ ቴፕ ውስጥ የተቀዳ ነው። ኃይለኛ ሴት፡ ታላቅ ሴት ትሆናለች፡ ወይ ፕሬዘዳንት ትሆናለች፡ ወይም የካቶሊክ ቤተክርስቲያንን የምትወክል ሴት ትሆናለች (እኔም ይሄኛው ይመስለኛል) አንድ ቀን ድል አድርጋ ይህችን አገር ትገዛለች። ይህ አገር የሴት አገር ናት። ባንዲራዋ የተሰራው በሴት ነው፡ ቁጥር አስራ ሶስት ናት። አስራ ሶስት ኮከቦችን፡ አስራ ሶስት ስትራይፖችን ያሏት፡ አጀማመርዋም፡ በአስራ ሶስት ቅኝ ግዛቶች ነው። ሁሉም ነገር እስከ ታች ድረስ፡ አሥራ ሦስት፡ አሥራ ሦስት፡ አሥራ ሦስት ነው። አሁን በብር ዶላር ላይ አስራ ሶስት ኮከቦች አሏት። ሁሉም ነገር አሥራ ሦስት ነው። ቁጥሯ አሥራ ሦስት ነው፡ እና በራእይ ምዕራፍ 13 ላይ

ትታያለች። ሙሉ በሙሉ አስራ ሶስት! ሁሉም ነገር እስከ ታች ድረስ፡ “ሴት፣ ሴት፣ ሴት፣ ሴት፣ ሴት።” ሹመቱ ሁሉ ተቆጣጠረች። ሆሊውድን ተቆጣጠረች። አገራትን ሁሉ ተቆጣጠረች። ያሉትን ሹመቶች ሁሉ ተቆጣጥራለች። አለ በተባለ ሁሉ ድል ነሰታለች፤ ከወንዱ ጋር እኩል መብት፡ ከወንዱ ጋር አብራ ትመርጣለች፡ እንደ ወንድ ትሳደባለች፡ እንደ ወንድ ትሰክራለች፡ ሁሉም ነገር ታደርጋለች። ለሴት አምልኮ መጠቀሚያ፡ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ወጥመድ ናት! እንደው፡ እንዲሁም ሴትን እያመለኩ ናቸው።

50 አንደኛ ናት... ክፉ ሴት ዲያብሎስ ሊጠቀምባቸው ከሚችል ማጥመጃዎች ዋና ናት። አሉ ከተባሉ መሸታ ቤቶች ዋነኛ ናት። በአገሪቱ ካሉት መሸታ ቤቶች ሁሉ በበለጠ ነፍሳትን ወደ ገሃነም መላክ ትችላለች። ትክክል ነው።

51 “መልካም ሴት በወንድ ዘውድ እንዳለች ጌጥ ናት፡” ብሏል በምድር ላይ የነበረው ጠቢብ ሰው። ወንዱ መልካሟን ሴት ማሞገስ ይገባዋል፡ አያችሁ። “ክፉ ሴት ግን በደሙ ውስጥ እንደ ውኃ ናት፡” ደሙ ማለት ህይወቱ ነው። ጥሩ ሚስት ያላችሁ ወንዶች ሆይ፡ ስለ መልካም ሚስት እግዚአብሔርን እንዴት ማመስገን ይገባችሁ ይሆን! እግዚአብሔር ለሰው ከሷ የተሻለ ነገርን ለረዳትነት የሚሰጥ ቢሆን ኖሮ፡ ይሰጠው ነበር። ሴት ግን እግዚአብሔር ለወንድ ሊሰጠው ከሚችለው የላቀ ረዳት ነች። ሲያምጹ ግን...

52 ሰይጣን በኤደን ገነት እንደ መሳሪያ እሷን ተጠቀመ። ሴቲቱን እንጂ፡ ሰውየውን አልመረጠም። ልዩ ሰሜትን ይሰጠው ዘንድ ወደ አዳም ለምን አልሄደም? ወደ ሴቲቱ መጥቶ ሰጣት፡ አያችሁ፡ የመረጠው እሷን ነበርና። እግዚአብሔር ወንዱን መረጠ፡ ሰይጣንም ሴቲቱን ወሰደ።

53 እስከ ታች ወርዳችሁ ተመልከቱ፡ ፍጻሜው ላይ... መጀመሪያ ላይ ባቢሎን ስትዋቀር፡ የሂሎፕ **ቱ ባቢሎስ፡** ሴት! ወደ ዘመናት እየወረደ በመጣ ጊዜ፡ እነሆ የአሕዛብ ዘመን ፍጻሜ ነው። ባቢሎንም እንደዛ ተዋቀረች፡ ፍጻሜውም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሴት-አምልኮ (በማርያም) ያከትማል። የምንኖረው እንዴት ባለ ዘመን ነው!

54 አሁን፡ **ሎዶቅያ**፡ የ—የሎዶቅያ ዘመን፡ የቃሉ ትርጉም “ለብ ያለ” ማለት ነው። በነዋይ የበለጸገች ናት፡ ሌላ ምንም የማያስፈልጋት እንደሆነች ታስባለች። መጽሐፍ ቅዱስ ግን “ጎሰቋላ፡ ዕውር፡ ምስኪን እና ራቁት፡” ነሽ ይላታል። እንዴት ያለ አጋጣሚ ነው!

55 በዚህ የቤተ ክርስቲያን ዘመን ድል ለሚነሱ ሰዎች ሽልማታቸው “ከጌታ ጋር በዙፋኑ ላይ መቀመጥ፡” ነው።

56 አሁን፡ የዚህች ቤተ ክርስቲያን ዘመን ኮከብ፡ ወይም መልአክ፡ ወይም መልእክተኛ፡ አይታወቅም።

57 እስኪ፡ የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ዘመን መልእክተኛ፡ ማን ነበር? ጳውሎስ፡ ኤፌሶን። ሰምርኔስስ? ኢራኒየስ። ጴርጋሞስ? ቅዱስ ማርቲን። ትያጥሮን? ኮሎምባ። ሰርዴስ? ሉተር። ፊላዴልፊያ? ዌስሊ። ይህ... የሎዶቅያ ሰው ግን፡ አሁንም እናውቀውም፡ ምናልባትም ሁሉም እስኪጠናቀቅ ድረስ ላይታውቅ ይችላል።

58 ነገር ግን ይህ እና የምንፈልገው መልአክ ምን እንደሚመስል፡ የራሴ አንቀጽ ማስቀመጥ እፈልጋለሁ። እንስማማበታለን አይደል? [ጉባኤው፡ "ኣሜን" አለ።—አርታዒ።] ትንሽ ጊዜ ስላለን፡ ያሰብኩትን አንቀጽ እዚህ ላይ አስፍሬዋለሁ።

59 የሎዶቅያዋ ቤተ ክርስቲያን መልአክ፡ ለማጠናቀቅ ይመጣል። አሁን፡ እንደ ሌሎቹ፡ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ፡ በዘመኑ መጨረሻ ላይ ይመጣል። በዘመኑ መጨረሻ ላይ የሚመጣ ይሆናል። በመጨረሻው ሳይሆን፡ በፍጻሜው ላይ ነው፡ ምክንያቱ መልአኩ ሁል ጊዜ የሚመጣ... ስለ ስራቸው ለመገሰጽ ነው። "ወደ ሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ—ብለህ ጻፍ።"

60 እያችሁ፡ "ወደ ሰምርኔስ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ጻፍ።" እያችሁ፡ እያንዳንዱ በዘመኑ ማለቂያ ላይ ለመልአኩ ነው። ጳውሎስን፡ የዘመኑ ማለቂያ ላይ። ወደ ታች ስንወርድ፡ የዘመኑ ማለቂያ ላይ። ድርቡ፡ በዘመኑ ማለቂያ ነው። ድርብ ሚያደርገው፡ የዘመኑ ማለቂያ ነው። እያችሁ፡ "ለመልአኩ፡" ሲል ምን እንደነበረ ያሳያል። ይህ ድርብ፡ "ለመልአኩ፡" የዚያን ዘመን ማለቂያው ነው። ተመልከቱ፡ እነዚህ ነገሮች ሰናነሳቸው፡ ድራቢዎቹ እንደ መወጣጫ የሚወጡ፡ ሰባቱ የቤተ ክርስቲያን ዘመናት መወጣጫ ይሰራሉ።

61 አሁን፡ ይህ በዚህ ዘመን የሚመጣው መልአክ፡ እዚህ የተጻፈ ነገር አለኝ እና፡ እንግዲህ... ማንበብ እፈልጋለሁ። በዘመኑ የመጨረሻ ክፍል ላይ ግን ይታወቃል። እንግዲህ አሁን ያለንበት እጅግ ቅርብ ስለሆነ—ማለት ለዚያ ብርሃን ዘመን እጅግ የቀረብን ስለሆንን፡ ምናልባት አሁን ምድር ላይ ሊሆን ይችላል። እያችሁ፡ እያውቁትም። እርሱም እነሆ የዓለም ቤተ ክርስትያን የማታውቀው—ታላቅ ነብይ ይሆናል፡ በኃጢአታቸው ቀድመው በመሄዳቸው ከእግዚአብሔርም እፍ ይተፋሉና፡ ከእግዚአብሔር መገኘት እፍ ይርቃሉ።

62 እንደ ኤልያስ አንድ ይሆናል ብዬ አምናለሁ። ለምን እንደሆነ ምክንያቶቼን እሰጣለሁ። አሁን፡ ወደዚህ ወደ መጽሐፈ ሚልክያስ እንሂድና፡ ለአፍታ ብቻ እከፍታለን፡ በኤልያስ መንፈስ የሚቀባው ለምን እንደሆነ እነግራችኋለሁ። አሁን፡ እንግዲህ የጸጋ ራስ—ቁራችሁን እንድታጠልቁ እጠይቃችኋለሁ። ሚልክያስ፡ ምዕራፍ 4። አሁን፡ እኔ ከመጽሀፉ ሳነበው ሳለሁ፡ በደንብ ተከታተሉኝ። አሁን፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን ዘመን ከመግባታችን በፊት፡ አሁን፡ ለሚቀጥሉት ጥቂት ደቂቃዎች በደንብ አሰቡ።

> **እነሆ፡ እንደ ምድጃ እሳት፡ የሚነድድ ቀን፡ ይመጣል፤ ትዕቢተኞችና፡ ኃጢአትን የሚሠሩ፡ ሁሉ፡...** ገለባ **ይሆናሉ፤ የሚመጣውም ቀን ያቃጥላቸዋል፡ ሥርንና ቅርንጫፍንም አይተውላቸውም፡ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር።**

63 ምን እያለ ነው? እየመጣ ስላለው ቀን እየተናገረ ነው። በዚህ ላይ ትስማማላችሁ? የሚመጣው የጌታ መምጣት ቀን።

### ነገር ግን ለእናንተ...

64 አሁን ተመልከት፡ አሁን ለእስራኤል እየተናገረ ነው። አሁን፡ ምን አለ? "እነሆ፡ የሚቃጠል ቀን (የወደፊት) ይመጣልና።"

**ነገር ግን ስሜን ለምትፈሩት... ለእናንተ የጽድቅ ፀሐይ ትወጣላችኋለች ፈውስም በክንፎችዋ ውስጥ ይሆናል፤** እናንተም **ትወጣላችሁ፡ እንደ ሰባም እምቦሳ ትፈነጫላችሁ።**

**በምሠራበት ቀን በደለኞች፡ ... -ከእግራችሁ ጫማ በታች አመድ ይሆናሉና እናንተ ትረግጡአቸዋላችሁ፡ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር።** (አይ... ምድርን በሚያቃጥላት ዘመን፡ በአመዳቸው ላይ እንሄዳለን። በርግጥ፡ ይህ የሺ አመት መንግስት ነው፡ አያችሁ።)

ለእስራኤል **ሁሉ፡ ሥርዓትንና** ፍርድን **አድርጌ በኮሬብ ያዘዝሁትን... የባሪያዬን፡ የሙሴን ሕግ... አስቡ።**

**እነሆ፡ ታላቁና የሚያስፈራው የእግዚአብሔር ቀን ሳይመጣ... ነቢዩን ኤልያስን እልክላችኋለሁ፤**

**መጥቼም ምድርን በእርግማን እንዳልመታ እርሱ የአባቶችን** ልብ **ወደ ልጆች፡ የልጆችንም** ልብ ወደ **አባቶች ይመልሳል፡ ምድርን በእርግማን እንዳልመታ።**

የብሉይ ኪዳን ፍጻሜ ነው።

65 አሁን፡ ኢየሱስም እንዲህ አለ... የማቴዎስ ወንጌል 17፡10 ላይ፡ ይህን ሲናገር። አይሁዳውያን ሁሉ የሚመጣውን ኤልያስን ይጠባበቃሉ። አሁን፡ ኢየሱስ ስለዚህ ጉዳይ የተናገረውን ተመልከቱ፡ ማቴዎስ 17፡10። በ9ኛው ቁጥር፡ ማቴዎስ 17፡9 እንጀምራለን፦

**ከተራራውም በወረዱ ጊዜ ኢየሱስ፡ የሰው ልጅ ከሙታን እስኪነሣ ድረስ፡ ያያችሁትን** ለማንም አትንገሩ... **ራእዩን ለማንም አትንገሩ ብሎ፡ አዘዛቸው፡** (አያችሁ፡ "ይህን አትንገሩ። ይኸውላችሁ፡ ለራሳችሁ ያዙት።")... ራእዩን ለማንም **አትንገሩ፡ የሰው ልጅ... ከሙታን እስኪነሣ ድረስ።** አትናገሩ።

**ደቀ መዛሙርቱም፡ እንግዲህ ጻፎች፡ ኤልያስ አስቀድሞ ሊመጣ ይገባዋል ስለ ምን** ይላሉ **ብለው ጠየቁት?** ይህ የጽድቅ ፀሐይ የተባለው ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት፡ ኤልያስ አስቀድሞ መምጣት ያለበት ለምንድነው? ለምን እንዲህ አሉት፡? እነሆ፡ አንተ መጥተሃል እዚህ ነህ፡ ጻፎች ግን ስለ ኤልያስ—አስቀድሞ ይመጣል ይላሉ።

አሁን፡ ተመልከቱ፦

**ኢየሱስም መልሶ፡ ኤልያስማ አስቀድሞ፡** ይመጣል፡ **ሁሉንም ያቀናል።**

**ነገር ግን እላችኋለሁ፡ ኤልያስ ከዚህ በፊት መጣ፡ የወደዱትንም ሁሉ አደረጉበት እንጂ አላወቃ**ችሁትም፡ (አያችሁ፡ ማን እንደነበረ አልተናገረም፡ አያችሁ፡) **ነገር ግን የፈለጋችሁትን ሁሉ አደረጋ**ችሁበት። **እንዲሁም ደግሞ የሰው ልጅ ከእነርሱ መከራ ይቀበል ዘንድ አለው አላቸው።**

**በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ስለ መጥምቁ ስለ ዮሐንስ እንደ ነገራቸው አስተዋሉ።** (እንግዲህ—አሁን፡ መጥምቁ ዮሐንስ ሊመጣ ያለው ኤልያስ ነው።)

66 አሁን ተመልከቱ፡ እንደገና፡ ወደ ሚልክያስ ምዕራፍ 4 እመለሳለሁ። አሁን አስታውሱ፡ እዚህ ጋር ተናግሯል "ታላቁና እና የተከበረ፡ የሚያስፈራው የእግዚአብሔር ቀን ሳይመጣ፡ ነቢዩን ኤልያስን እልክላችኋለሁ።" 5ኛው ቁጥር፦

**እኔ** ግን... **ነብዩን እልክላችኋለሁ... ታላቁ ቀን ሳይመጣ በፊት ነቢዩን ኤልያስን እልክላችኋለሁ ከአስፈሪው የማን... ቀን በፊት** [ጉባኤው "**የጌታ**፡" አለ።—አርታዒ።]

67 "በጌታ ቀን" በዘመኑ መጨረሻ! ምን ይሆናል? ዓለም የሚቃጠልበት ጊዜ ያኔ ይሆናል። በነጭ ዊግ፡ እና—ጡቶቹ፡ የታጠቀውን ጡቶቹ፡ ምን ብለን እንደተማርነው ታስታውሳላችሁ። ትዝ ይላችኋል? ስለ ጌታ ቀን፡ **ሰንበት** ወይም **እሑድ፡** አለመሆኑን በመጽሐፍ ቅዱስ አረጋግጠነዋል። ልክ ነው? እርሱም እንደ ፈራጅ ሆኖ የሚመጣበት ቀን ነው። "ምድርንም በእርግማን ይመታል።" ልክ ነው?

**ታላቁና የሚያስፈራውም የእግዚአብሔር ቀን ሳይመጣ ነቢዩን ኤልያስን እልክላችኋለሁ፡**

68 አሁን፡ የኤልያስ ድርብ አመጣጥን ተመልከቱት። አሁን፡ ካስተዋላችሁ፡ ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ ድርብ ፍቺዎች አሏቸው፡ "ነገር ግን ከጥበበኞች እና ከአስተዋዮች ዓይኖች ተሰውሮ፡ ለሚማሩ ለሕፃናት ይገለጣል።" ይህን አታምኑም? አሁን፡ ሚልክያስ 4 በደንብ ያዙልኝ።

69 እና ወደ ማቴዎስ 2 እንሂድ፡ አንድ ደቂቃ ብቻ፡ ማቴዎስ 2 ቀጥሎ ባለው ገጽ ይገኛል። በማቴዎስ 2 ፈንታ ሉቃስ 2ን ለማለት ፈልጌ ነው። እዚህ ጋር ጽፌዋለሁ፡ ብቻ ግን ከአፍታ በፊት ቸኩዬ ነበር፡ መንፈስ ቅዱስም በክፍሉ ውስጥ አብሮኝ ነበር እና ጥሩ ጊዜ እያሳለፍኩኝ ነበር። ስለዚህ... 2 ማለቴ ነው፡ እስኪ እንየው። አሁን፡ እዚህ አንድ ደቂቃ ብቻ ልፈትሸው። ማቴዎስ 2? የምፈልገው ይህ አይመስለኝም፡ አይደል´ዴ? አሁን፡ አንድ ደቂቃ ብቻ ስጡኝ፡ ቶሎ አገኘዋለሁ... ትንሽ ጊዜ ብቻ ስጡኝ ምክንያቱም ቅዱሳት መጻሕፍት፡ ድርብ ትርጉም የያዙ መሆናቸውን እንድታዩ እፈልጋለሁ። **ዘ አዶሬሽን ኦፍ እና፤ ሪተርን ቱ ናዝሬት፤ ዘ ፓሶቨር፤ ዘ ሚኒስትሪ ኦፍ ጆን።** እስኪ፡ ሉቃስን ለማለት ፈልጌ እንደሆነ እስኪ ልየው፡ እዚህ ዙርያ እያነበብኩት ነበርና... አይ—በሉቃስ ፈንታ ማርቆስን ማለቴ ነው፡ ማርቆስ ሊሆን ይችላል። ይህ የጌታ ስራ መሆኑ ታውቂ ዘንድ—ቅዱስ ቃሉን እንድታዩት እፈልጋለሁ፡ ይህም እርሱ የሚሰራው በዚህ መንገድ እንደሆነ ነው። አሁን፡ የት እንደ፡ የት እንደምፈልግ እነግራችኋለሁ፡ "ልጄን ከግብፅ ጠራሁት።" እስኪ በፍጥነት ሊያገኘው ወይም ሊያነብልን የሚችል ማጣቀሻ ንባብ ያለው ሰው ካለ? "ልጄን ከግብጽ ጠራሁት። ልጄን ጠራሁት።" አሁን፡ አንዴ ጠብቁኝ።

70 [አንድ ወንድም፡ "ሉቃስ 1፡17።" አለ—አርታዒ።] ሉቃ 1፡17። አመሰግናለሁ፡ ወንድሜ። ልክ ነው፡ ሉቃስ 1 ላይ። ማርቆስ... 2 ሳይሆን፡ ሉቃስ 1፡17 ላይ። 14ኛውን ማግኘት ፈልጌ ነው፡ ያ ነው... ያ ነው፡ ወንድሜ። ልክ ነው፡

ሉቃስ 1፡17 ላይ ነው። እሺ። አሁን፡ መጻፍ ትችላላችሁ። አሁን፡ ከጌታ ዘንድ የመጣለት በረከት፡ ምን ነበረ፡ በረከት ነው።

> **ተድላ እና ደስታም ይሆን**ልሃል፡ **በመወለዱም ብዙዎች ደስ ይላቸዋል።**
>
> **በእግዚአብሔር ፊት ታላቅ ይሆናልና፡ የወይን ጠጅና የሚያሰክር መጠጥ አይጠጣም፤**

71 ይህ የሚወጣው ሰው ከመወለዱ ጀምሮ መጠት እንዳይጠጣ ወይም ከኃጢአት ጋር ምንም ግንኙነት እንዳይኖረው የተማረ ይሆናል። ገባችሁ?

> **... ገናም በእናቱ ማኅፀን ሳለ፡ መንፈስ ቅዱስ ይሞላበታል።**
>
> **ከእስራኤልም ልጆች ብዙዎችን ወደ ጌታ ወደ አምላካቸው ይመልሳል።**
>
> **እርሱም የተዘጋጁትን ሕዝብ ለጌታ እንዲያሰናዱ፡ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች፡ የማይታዘዙትንም ወደ ጻድቃን ጥበብ ይመልስ ዘንድ፡ በኤልያስ መንፈስና ኃይል በፊቱ ይሄዳል።**

72 እንግዲህ፡ በትንቢት የተነገረለት እንደነበረ አስተውለናል፡ እርሱም ስለ ዮሃንስ ነበረ! ልክ ነው? በዚያ ዘመን፡ ሊመጣ ያለው ኤልያስ፡ ዮሐንስ ነበር።

73 አሁን፡ ቅዱሳት መጻሕፍት አንዳንድ ጊዜ ድርብ ትርጉም እንዳለኣቸው እናውቃለን። በማቴዎስ ላይ፡ "ልጄን ከግብጽ ጠራሁት፡" ተብሎ እንደተጻፈ በንድ በኩል አንድ ነገር ይናገራል። እሺ፡ ሰፈልገው የነበረው ይህ እንደሆነ ይመስለኛል፡ "ልጄን ከግብጽ ጠራሁት።" እና ያ ነገር ከመረመራችሁት "ልጅ" ስትፈትሹት፡ ሰለ እርሱ... ሳይሆን... ያ ወደ ሆሴዕ ይወስዳችኋል፡ **ኢየሱስን** ማለቱ አይደለም፡ ልጁ፡ **እስራኤል** ነበረ፡ ልጁን፡ "እስራኤልን ከግብጽ ጠራሁት።" ሰለ—ሰለ ኢየሱስ መምጣት ሲናገር ግን የበለጠ እና የጠለቀ ድርብ ትርጉም ይኖረዋል፡ እስራኤልን ሊያሰወጣው በጠራው ጊዜ፡ ከ—እስራኤል ይልቅ የሚበልጥ ነበረ። በጣም ጥሩ።

74 በተጨማሪም፡ የመጀመሪያው አመጣጡ... የጌታ ቀን እንዳልነበረ እንዲህ ደግሞ እናያለን። ልክ ነው? አሁን፡ ወደ ሚልክያስ እንመለስ፡ እና ይህን አስቀድመን እናስተካክለው፡ "በጌታ ቀን ይመጣል።" አሁን፡ ድርብ አመጣጡን ተመልከቱት፡ አንደኛው መምጣት እና ሁለተኛው መምጣቱ። መንፈሳዊ አረዳዳችሁን ዝግጁ ነው? አሁን ወደ 6ኛው ቁጥር፡ "ምን ያደርጋል... "

> ... **ኤልያስን... ይልካል... ከታላቁና... ከሚያስፈራው የእግዚአብሔር ቀን በፊት፡** (ልክ ነው? )

75 ሰለዚህ፡ የሚያስፈራው የጌታ ቀን ያ ሰልላነበረ፡ ያ ማለት ዮሐንስ እንዳልነበረ እንረዳለን (ያ ነበር እንዴ? )፡ ደግሞም... ምድርን ገና አላቃጠላትምና። ሰለዚህ ሌላ ቅድመ እይታ ማለቱ መሆን አለበት፡ ወይም—ወይም የዮሐንስ... ወይም የ—የኤልያስ የወደፊት መምጫም ሊሆን ይችላል። ልክ ነው? ምክንያቱ እንዲህ ብሎናልና፡ "ኤልያስን እልክላችኋለሁ፡ ምድርንም ሁሉ እቃጥላለሁ፡ በደንብ አጸዳታለሁ፡ እናንተም በአመዳቸው ላይ ትመላለሳላችሁ።" ይህን እናውቀዋለን፡ የሺ አመቱ መንግስት ነው። የአቶሚክ

ቦምብ ፍንዳታ ካደቀቃት በኋላ፡ እንዲህ ይሆናል... ምድር ትቃናለች። እነሆ ያን ጊዜ ታላቅ ቀን በምድር ላይ ይሆናል፡ ቤተክርስቲያንም ከኢየሱስ ጋር በምድር ላይ ለሺህ ዓመት ትነግሣለች። ልክ ነው? "ከታላቅና ከሚያስፈራው የጌታ ቀን በፊት ግን፡ እመድ ከመሆኗ በፊት፡ ኤልያስን እልክላችኋለሁ።" ልክ ነው? ስለዚህ በዚያ ሁኔታ መጥምቁ ዮሐንስ ለማለት አይደለም፡ ምክንያቱ የሚያስፈራው የጌታ ቀን ያኔ አልነበረምና፡ ሁለት ሺ አመታት ቆይቷል። ልክ ነው?

76 አሁን፡ የሚቀጥለውን ቁጥር ተመልከቱት። በትክክል መንፈሳውያን ከሆናችሁ፡ አሁን፡ ይህ የፍቅር ደብዳቤ ነው፡ እናንተም ውስጥ ለውስጥ ማንበብ አለባችሁ ያኔ ልክ ይመጣል። ምን ለማለት እንደፈለግኩ አውቃችኋል። እንዴት እንዳልኩ አስታውሱ፡ ቅዱሳን ቃላት፡ "ኢየሱስ እግዚአብሔርን ያመሰገነው ከጥበበኞች፡ (ከሚያዩ አይኖች) እና ከአስተዋዮች ሰውሮ ለሕፃናት ገልጿልና።" እና፡ ሚስቴ ስለጻፈችልኝ ደብዳቤ ብዙ ጊዜ ገለጻ ለማድረግ ሞክሬ አውቃለሁ፡ በደብዳቤዋ ውስጥ የምትለው መልእክት እየዋለሁ፡ ምን ለማለት እንደፈለገች ግን ውስጥ ለውስጥ አንብቤ አውቃለሁ፡ አያችሁ፡ ምክንያቱ እወዳታለሁ እ—እንዲሁም ተፈጥሮዋን አውቀዋለሁ። እናንተም የእግዚአብሔርን ተፈጥሮ ማወቅ እና እሱን መውደድ አለባችሁ፡ ያን ጊዜ ቅዱሳት መጻህፍት ጎልተው ይታዩላችኋል። ይገልጠዋል።

77 አሁን፡ ቀጣዩን ጥቅስ ተመልከቱ፡-

> **የአባቶችንም** ልብ **ወደ ልጆች ይመልሳል፡** (አሁን፡ ተከታተሉ።)
> **የልጆችም** ልብ **ወደ አባቶች፡**... (አያችሁ? )

78 አሁን፡ ዮሐንስም እንደ ኤልያስ በመጣ ጊዜ፡ የእስራኤልን ልጆች ልብ መለሰ፡ በዚያን ጊዜ መልእክቱን ይቀበሉ የነበሩት የልጆቹ ልብ መለሰ፡ የአባቶች ልብ ወደ ልጆች። **በዚህ** ጊዜ ሲመጣ ግን፡ የቤተክርስቲያንን ልብ ወደ ጴንጤቆስጤ አባቶች ይመልሣል። አያችሁ፡ በተቃራኒው ገጽ ነው። ገባችሁ? አሁን፡ እንብቡት!

79 አሁን፡ በደንብ ተከታተሉት፡-

> **የአባቶችንም ልብ** ወደ **ልጆች ይመልሣል፡...**

80 ጥንታዊ የኦርቶዶክስ ካህን፡ ይህ ይነግራቸዋል፡ "ለምን፡ እግዚአብሔር ከእነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆችን ሊያነሣለት ይችላል። ይህ እና ያ አለን አትበሉ... " አያችሁ? አሁን፡ የዚህ ባለ ወፍራም ቅርፊት የጥንት ኦርቶዶክስ ካህን ልብ ወሰዶ እነሆ አሁን ልጆች ወደያዙት እምነት ልባቸውን ይመልሣል። አያችሁ፡ "አሁን፡ እነዚህ የተጠመቁት ሁሉ የሚመጣውን መሲሕ የሚጠብቁ ነበር። እናንተ የእፉኝት ልጆች፡ ከሚመጣው ቍጣ እንድትሸሹ፡ ማን አስጠነቀቃችሁ? " ኦህ፡ ማይ! አያችሁ፡ "የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች ይመልሥ ነበር።"

81 "የልጆችም ልብ ወደ አባቶች።" እንግዲህ፡ **ይህ** ታላቅ ኤልያስ በዚህ ዓለም ፍጻሜ ሲመጣ፡ ልጆቹን ወደ አባቶች እምነት ይመልስ ዘንድ የጴንጤቆስጤውን መልእክት ያመጣል። ይህም መጀመሪያ ላይ የነበረውን ይህ እምነት ስላልጠበቁ ይወቅሳቸዋል። አሜን! ይህ፡ ኤልያስ እንደሚሆን በሚገባ እንደተገነዘብን አምናለሁ። አይደል? አሁን አውቀናል።

82 ይህ ሲሆን... አሁን ተመልከቱት፡ የሚያስፈራው የጌታ ቀን ገና ነው አልመጣም። ብዙ ጊዜ ሳስበው፡ "እንግዲያውስ፡ ይህ ሰው ሰባኪ ይሆን?" ኤልያስ ሳይሰብክ፡ ተአምራትን ሁሉ አድርጎ ነበር። መንፈሱ በዮሐንስ ላይ በወረደ ጊዜ ግን ስብከትን ሁሉ ሰብኳል፡ ተአምራት ግን አላደረገም። ለምን? ኢየሱስ ከእሱ በኋላ መጥቶ፡ ተአምራቶቹን ማድረግ ስለነበረበት፡ "ፈውስ በክንፎቿ ይዛ፡" "የጽድቅ ፀሐይ ትወጣለችና፡" ብሏልና። ስለዚህ ለዮሐንስ የክርስቶስን መምጣት መናገር እንጂ፡ ተአምራትን ማድረግ አላስፈለገውም። እነርሱም...

83 አሁን፡ አስታውሱ፡ እና ይህን ዮሐንስ... ወይም ይህ የሚመጣው ኤልያስ ተቀባይነት አያገኝም፡ ሰዎች መሲህ ነው ብለው እስኪያስቡት ድረስ በጌታ ፊት ታላቅ ኃያል ሰው ይሆናል።

84 ምክንያቱ የቅርብ ጓደኞቹ "አንተ መሲሕ ነህ፡" ብለውት ነበር።

85 እርሱም አላቸው፡ "እነሆ ከእኔ በኋላ ይመጣል፡ እኔ ግን ጫማውን ልፈታ አልበቃም!"

86 ምክንያቱ ያን ጊዜ፡ መሲሑን ለማየት፡ በመጠባበቅ ስለነበሩ፡ መሲሑ የመጣ ይመስላቸው ነበር... በመካከላቸውም ይህን ታላቅ ክስተት ባዩ ጊዜ; "መሲሕ ነው፡" አሉ።

87 ዮሐንስ ግን አላቸው፡ "እኔ እሱ አይደለሁም! እነሆ ከእኔ በኋላ ይመጣል!"

88 ኦህ፡ ማይ! ገባችሁ? ስለዚህ የቅርብ ጓደኞቹ መሲህ ነው ብለው ያስቡታል።

89 አሁን፡ ሌላ የሚፈጸም ነገርም፡ ስለ ተፈጥሮው፡ ከጌታ ቀን መምጣት በፊት ይመጣል ነው። ሌላው፡ ምድር በዮሐንስ ዘመን አልተቃጠለችም፡ ይህ ማለት ወደፊት ይሆናል ነው። መጀመሪያ በመጣ ጊዜ፡ ስብከት ብቻ ሰበከ፤ ሁለተኛው ጊዜ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጣቸውን የተሰፋ ቃልና ምልክቶች ሁለቱንም ያ—ያደርጋል። እሺ፡ አሁን ደግሞ፡ እስኪ ባህርይውን እንመልከተው፡ የዚህ የሚመጣው ነብይ ባህርይ፡ ምን እንደሚመስል እንየው።

90 እንግዲህ፡ የዚህ የመጨረሻው የቤተ ክርስቲያን ዘመን መልአክ፡ ከብሉይ ኪዳን ጀምሮ የተነገረለት ስለነበረ ረክተናል፤ ስለ ሌሎቹ ግን የተባለ ነገር፡ አልነበረም። ስለ ጳውሎስ፡ ኢራኔዎስ፡ የተነገረ አገር አልነበረም። ይህ በነገር ሁሉ ፍጻሜ፡ የመጨረሻው ዘመን፡ የዓለም ፍጻሜ ግን፡ እነሆ ከፊታችን ያለው ጊዜው እጅግ አስደናቂ ይሆናል፡ ስለዚህ የዚህ ዘመን መልአክ በቅዱሳት መጻሕፍት፡ በብሉይ መጽሕፍት ውስጥ አስቀድሞ የተነገረለት፡ የዚህ ዘመን ፍጻሜ ነው። ይህም ታላቁ፡ የተቀባው ኤልያስ ነው።

91 አሁን፡ ተከታተሉ! ኤልያስ ምን ዓይነት ተፈጥሮ ይኖረዋል? በመጀመሪያ፡ ስለ እግዚአብሔር ቃል እውነተኛና ኃያል ነቢይ ይሆናል፡ ኤልያስም እውነተኛ ነበርና፡ ዮሐንስም እውነተኛ ነበር። ትክክል ነው። ተአምራትን እና ድንቆችን በማድረግ፡ የልጆችን ልብ ወደ ጴንጤቆስጤ አባቶች እምነት ይመልሣል። እንደ ኤልያስ የሐይማኖት ተቋማትን የሚጠላ ይሆናል። ልክ ነው፡ እንዲሁ ይሆናል! አሁን ነገሩን ስለ እርሱ የጀመርነው ይመስለኛል፡ የሚመጣበት ጊዜ አሁን ነው።

የሐይማኖት ተቋማትን አይወድም! ኤልያስ አይወድም ነበር፡ ዮሐንስም እንዲሁ የሐይማኖት ተቋማትን አይወድም።

92 ዮሐንስ እንዲህ አለ፡ "ተው፡ እንዲህ አታስቡ፡ 'አብርሃም አባት አለን' አትበሉ። እናንተ ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን፡ የእፉኝት ልጆች። የሳር ውስጥ እባቦች፡" ሌላ ቃላቶች ጭምር። "እላችኋለሁ፡ ከእነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች ያስነሣላቸው ዘንድ እግዚአብሔር ይችላልና።"

93 ኤልያስም ሲናገር "እነሆ ሁሉም ሄዱ፡ እኔ ብቻ ቀረሁ! ከእኔ በቀር ሌላ የለም፡" አለ። ኦህ፡ ማይ!

94 ቅምጥል ሴቶችንም የማይወድ ይሆናል! ኤልያስ በኤልዛቤል ላይ፡ ያን አደረገ። ልክ ነው? ዮሐንስም፡ በሄሮድያዳ ላይ። ሁለቱም ነቢያት፡ መንፈሳቸው፡ አንድ መንፈስ ነው። ሁለቱም ዓለማዊ ተቋም፡ ዓለማዊ የቤተ ክርስቲያን ተቋም ይጠላሉ። እንዲሁም፡ ቅምጥሊቱን፡ እርባና-ቢስ ሴትን፡ ሁለቱ ይጠላሉ። በሁለቱም... በመንፈሳቸው ውስጥ ነገሩን የሚጠላ ነገር ነበረባቸው! ኤልዛቤል የኤልያስን ራስ ለመቁረጥ ታሳድደው ነበር፤ ሄሮድያዳም፡ የዮሐንስን ራስ አስቆርጣለች። ሁለቱም!

95 ይህ ነቢይም ልክ እንደ ኤልያስ የምድረ በዳ ወዳጅ ይሆናል፡ በምድረ በዳ ብቻውን ኖረ፡ ዮሐንስም፡ ብቻውን በምድረ በዳ ኖረ፡ ስለዚህ ኤልያስም እንዲሁ እንደሚሆን እናውቃለን። መልካም።

96 እናም ይህ ነቢይ ከእውነተኛው የእግዚአብሄር ቃል ጋር የሚኖር ይሆናል። አዎን፡ ከቃሉ ጋር፡ አብሮ ይኖራል። ምን ለማድረግ? በዘመናት ሁሉ የጠፋውን እምነት (ወደ ኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን) ለመመለስ፡ በፊቷ የነበረውን "የተከፈተ በር" ያክፋፋችውን ቤተ ክርስቲያን፡ እምነት።

97 ያልተማረ ሰው ነው። ቴስቢያዊው ኤልያስ፡ የተማረ ሰው አልነበረም። ዮሐንስም የተማረ አልነበረም። ሉቃ 1፡67 መፅሃፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል... "ልጁ እንደተወለደ... በተወለደ ጊዜ፡ ለእስራኤልም እስከ ተገለጠበት ቀን ድረስ በምድረ በዳ ኖረ፡ ወደ ምድረ በዳ ተወሰደ።" በትክክል። ማስታወሻ መያዝ ከፈለጋችሁ፡ 1፡... ሉቃ 1፡67 እስከ 80ኛው ቁጥር ድረስ።

98 በተጨማሪ ይህ ነብይ በባህርዩ ተለዋዋጭ ስሜት ያለው ይሆናል። ኤልያስ፡ ታላቅ ጉባኤ ካደረገ በኋላ፡ ማንም ሊገዳደረው አልቻለም። ኤልያስ ከአፉ ቃል ይወጣልና። ወጥቶ እሳትን ከሰማይ በጠራ ጊዜ የበኣልንም መሠዊያዎች አቃጠለ፡ ወደ ምድረ በዳም ሸሽቶ እንዲህ አለ፡ "ጌታ ሆይ፡ እኔ ከአባቶቼ አልበልጥምና፡ ልሙት።" ልክ ነው? (ዮሐንስ... ) ከታላቁ ሪቫይቫል በኋላ፡ ከ—ከዛፍ በታች ተቀምጦ፡ እነሆ ሞትን ተመኘ።

99 ዮሐንስም፡ (በዚህች ክፉ ሴት) ወደ ወህኒ በጣሉት ጊዜ እንደገና ስሜቱ መቀያየር ጀመረ። ፔምበር ወይም ሌላ ሰው ይመስለኛል፡ "የንስር አይኖቹ፡ በእስር ቤት ተጭበረበሩ" ብሎታል። ከደቀ መዛሙርቱም የተወሰኑትን ላከ።

100 እንዴ፡ ለምን፡ እንዲህ በማለት፡ "የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ፡" በማለት አውጆ ነበር። ዮሐንስ የእሳት ዓምድ፡ በርግብ አምሣል፡ ወርዶ፡ ሲያርፍበት አይቶ ነበርና። ይህን ሁሉ መስክሮ፡ እንዲህ አለ፡

“የእግዚአብሔር በግ ይህ ነው!” እንዲህም አለው፡ “እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል እንጂ፡ አንተ ወደ እኔ እንዴት ትመጣለህ? ”

ኢየሱስም “አሁንስ ይሁን ፍቀድልኝ፡” አለው።

101 ወደ እስር ቤት ባስገቡት ጊዜ ግን፡ እነሆ በፍጥነት ቁልቁል ወረደ። አያችሁ፡ ይከብዳል፡ ልትረዱት ይከብዳችኋል። በሄዱም ጊዜ፡ እንዲህ አላቸው፡ “ሄዳችሁ ጠይቁት ሊመጣ ያለው እርሱ ነው፡ ወይስ ሌላ የሚመጣ እንጠብቅ? ” አያችሁ፡ ልክ እንደ ኤልያስ፡ ተመሳሳይ ነው።

102 ተለዋዋጭ ስሜት ያለው፡ አይነት ሰው ነው፡ ምን ማለት እንደሆነ ስለሚገባን እናዝንለታለን። በጣም ጥሩ።

103 አሁን፡ አሁን በ... ቤ—ቤተ ክርስቲያን፡ በመገለጡ... እሺ ያን ብተወው ይሻላል። በመገለጡ፡ በ—ቤተ ክርስቲያን... እግዚአብሔር ወደ እኛ የሚልከው፡ ይህ ኃያል ኤልያስ፡ ራሱን ሲገልጽ፡ እንደ ኤልያስ ራሱን በገለጠ ጊዜ፡ ቤተ ክርስቲያን ራሷን ለማስመለጥ ተዘጋጅታ ነበር። ከአረማዊነት እጅ ነፃ ለመውጣት ዝግጁ ነበረች። ልክ ነው? ልክ እዚያ መጥቶ፡ “አምላክ ማን እንደሆነ እናያለን” ባላቸው ጊዜ፡ ኤልያስ ቤተ ክርስትያንን አስመለጠ። ዮሐንስም፡ ዮሐንስ ኢየሱስን ባየው ጊዜ፡ እንዳደረገው፡ እንዲህ አለ፡ “እኔ ላንስ እሱ ግን ሊልቅ ያስፈልጋል።” ዮሐንስ መሰበክ ጀመረ፡ ጌታ ከመምጣቱ በፊት ራሱን አሳወቀ። ልክ በመጨረሻው ሰዓት፡ በመገለጡ ጊዜ። መልካም።

104 እንግዲህ፡ ኤልያስ በዚህ ዘመን ለዚህች ቤተክርስቲያን መሆን እንዳለበት ተረድተናል። ኤልያስ መሆኑን ለማረጋገጥ፤ ኤልያስ ትንቢቱን ከተናገረ በኋላ፡ ኤልያስ አልሞተም፡ ተነጠቀ እና ወደ ሰማያት ተወሰደ፡ የቤተ ክርስቲያን ጥላ ነው (በዚህ ኤልያስ መጨረሻ ላይ፡ **በእርሱ** ዘመን ፍጻሜ)፡ ቤተክርስቲያን በሞት ጥላ ውስጥ ሳታልፍ፡ በመነጠቅ ትሄዳለች። መነጠቅ ይሆናል! ሊመጣ ያለውም፡ ታላቁን ኤልያስንም፡ በመጨረሻው ዘመን ትንቢት የተነገረለት የተቀባው ኤልያስ እንደሚሆን እምናለሁ። አሜን! እርሱ ሲመጣ፡ ለመጨረሻይቱ ዘመን ቤተ ክርስቲያን፡ መልአክ ወይም መልእክተኛ፡ እንደሚሆን አስባለሁ፡ (እንደዚህች ቤተ ክርስቲያን፡ እንደሆነችበት ሁኔታ፡ ለተጠላ፡ ለተዋረደው ህዝብ)፡ ኤልያስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቃል የተገባለት ይመስለኛል። ያንን መረዳት የምንችል ይመስለኛል፡ ማለት በዚህ ዘመን እንዲመጣ በመጽሐፍ ቅዱስ የተነገረለት ኤልያስ እንደሆነ። ይህን ታምናላችሁ?

105 አሁን፡ ወደ ሎዶቅያ እንሂድና ጌታችን ዛሬ ማታ ስለ ሎዶቅያ፡ ስለ ሎዶቅያ የሚናገረንን እናያለን። መልካም፡ ለቤተ ክርስቲያኒቱ የተሰጠ ሰላምታ፦

... **ለጌታ መልአክ...**

106 ከራዕይ 3ኛ ምዕራፍ 14ኛው ቁጥር፦

> **... በሎዶቅያ ወዳለው**... **ለጌታ መልአክ... እንዲህ ጻፍ፤ አሜን** የሆነው፡ **የታመነውና እውነተኛው ምስክር፡ በእግዚአብሔርም ፍጥረት መጀመሪያ የነበረው እንዲህ ይላል፤**

107 ኦህ፡ ማይ! እንደው... በዚች ርዕስ ላይ ሌሊቱን ብናድር፡ አቤት ጌታ እንዲሁ በገለጠልን ነበር! ተከታተሉ!

108 “አሜን” ማለት “ፍጻሜ” ነው። እስከ መጨረሻ ድረስ፡ ራሱን በተለያየ መንገድ ሲያሳይ ቆይቷል፡ በዚህ በመጨረሻው የቤተ ክርስቲያን ዘመን ግን “ይህ ፍጻሜ ነው፡ እኔ... የመጨረሻው ነኝ፡” ይላል።

109 የነበረ፡ እንዲሁም ያለው፡ “የመጀመሪያ” መሆኑን ለማሳየት ደግሞ፡ “የእግዚአብሔር ፍጥረት መጀመሪያ ይላል።” አቤት! ተረዳችሁት? አያችሁ? እግዚአብሔር መንፈስ ከሆነ እንዴት ሊፈጠር ይችላል? እንዴት ሊሆን ይችላል? እርሱ’ኮ—ዘለአለማዊ ነው! ከመጀመሪያ ጀምሮ አምላክ ስለሆነ፡ አልተፈጠረም፡ ወደፊትም አይፈጠርም። “የእግዚአብሔር ፍጥረት መጀመሪያ” ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡ እርሱም በተገለጠ ጊዜ ማለት እግዚአብሔር በእርሱ ዘንድ በኖረ ጊዜ ነው። እርሱ የእግዚአብሔር **ፍጥረት** ነው! ኦህ፡ ማይ! አያችሁ፡ “የመጀመሪያው እና የመጨረሻው፡ አሜን የሆነው፡ የእግዚአብሔር ፍጥረት መጀመሪያ።” እግዚአብሔር ለራሱ የሚሆን ሰውነት በፈጠረ ጊዜ፡ ወርዶ በውስጡ ኖረ፡ የእግዚአብሔር ፍጥረት መጀመሪያ ያ ነው። አያችሁ? አቤት፡ አይደንቅም ወይ?

110 አሁን፡ በመጀመሪያ፡ አምላክነቱን **እዚህ** ውስጥ አሳይቶ እናገኘዋለን፡ “ሁሉን ቻይ እኔ ነኝ! የነበረው፡ ያለዉና፡ የሚመጣውም እኔ ነኝ። ሁሉን ቻይ!” ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን፡ ሦስት ጊዜ ተናገራት። ልክ ነው? ወዲያው ወደ ሎዶቅያ መጥቶ እንዲህ አለ፡ “አሜን እኔ ነኝ። ያኔም **እዚያ** ጋር መጀመሪያ ነበርኩ፡ **እዚህ** ጋርም የመጨረሻው እኔ ነኝ። የእግዚአብሔር ፍጥረት መጀመሪያ እኔ ነኝ። ወደፊት በሚኖረን የቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ እግዚአብሔር መሆኔን፡ እግዚ አብሔር በሰው አምሳል እንደተፈጠረ ትማራላችሁ። የእግዚአብሔር ፍጥረት መጀመሪያ እኔ ነኝ!” ኣሜን።

111 ይህ ፕሪስባይቴሪያኑን ያስጮኸዋል። እስቲ አስቡት! “የእግዚአብሔር ፍጥረት መጀመሪያ።” አሁን፡ እ... አቤት፡ እንዴት እንደምወደው፡ “የእግዚአብሔር ፍጥረት፡” እግዚአብሔር ሲፈጠር፡ እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ሆኖ ሲያድር ማለት ነው።

112 አሁን—አሁን፡ የሚቀጥለው ጥቅስ (ለሌሎች አብያተ ክርስቲያናት) ያመሰግናቸዋል፡ ይህችን ቤተክርስቲያን ግን አላመሰገናትም። ቅሬታ እንጂ፡ ምስጋና አልነበረም። ይህን የሎዶቅያ ዘመን፡ በከንቱ አላመሰገናትም። ያን ሁሉ ብርሃን በርቶላቸው፡ እንደገና በዚያ መውደቃቸው፡ ምስጋና አያስፈልጋቸውም። ኧሃ-ሃህ። ተግሣጽ ያስፈልጋቸው ነበር፡ ተገሰጹ! ለዚህች ቤተ ክርስቲያን ቅሬታ እንጂ፡ ምስጋና አልነበረውም።

113 አሁን እዚህ 15ኛው እና 16ኛውን ቁጥር ማንበብ እፈልጋለሁ፦

> **ሥራህን አውቃለሁ... በራድ ወይም ትኩስ አይደለህም፤ በራድ ወይም ትኩስ** ብትሆንስ **መልካም ነበር።** (በሌላ አባባል፡ “ለብ ያለ—ብቻ አትሁን።”)
>
> **ስለዚህ ለብ ስላልህ፡ በራድም ወይም ትኩስ ስላልሆንህ፡ ከአፌ እተፋሃለሁ።** (እምም!)

114 ይህ ምስጋና ነውን? ይህ ከሌሎቹ ሁሉ ይልቅ ክፉ ለሆነው፡ አምላካዊ ላልሆነው ለሎዶቅያ ዘመን ተግሳጽ ነው። ሌሎቹ ሁሉ በሰቃይና በነበረባቸው መከራ ሆነው፡ ምንም አልነበራቸውም፡ በድህነት-የተጠቁ፡ የበግና የፍየል ለምድ

ሊብሰው የሚዞሩ፡ ግራ የተጋቡ፡ በመጋዝ እየተሰነጠቁ እና በእሳት እየተገደሉ፡ ለአንበሶች እየተሰጡ፡ እና ልዩ ልዩ ነገር እየሆነባቸው፡ እምነታቸውን ያጸኑ ነበሩ። ይህ መንጋ ግን “ምንም ነገር የማያስፈልገው ባለጸጋ” ሲሆን፡ ያለሆነው ነገር የለም፡ ዘማዊ ነው! ልክ ነው።

115 አሁን፡ ትልቅ ትምህርት አግኝተናል፡ ጌታ እንደሚረዳን ተሰፋ አደርጋለሁ። “ለብ ያልክ፡ ትኩስ ወይም ቀዝቃዛ ስላልሆንህ፡” ይ—ይለዋል።

116 ልክ እንደ ወተት፡ አያችሁ። ቀዝቀዝ ያለ ወተት ደስ ይላል። አይደል? ትኩስ ወተትም ይጠቅማችኋል። ለብ ያለው ወተት ግን ያስታውካችኋል።

117 ትዝ ይለኛል የዛሬ ሃያ-አምስት አመት፡ ወንዙ ማዶ፡ አንድ ቀን ማታ ላይ አሞኝ ያውቃል። እነሰ ባለች የጀልባ ቤት ውስጥ፡ እኖር ነበር። ታመምኩና፡ ወዳለሁበት መጥተው፡ የ-እህቴ-ባል መጥቶ ወደ ዶ.ር ኢሰለር ወሰደኝ። “ምን ገጠመህ፡” አለኝ?

እኔም፡ “ሆዴ ላይ በጣም ታምሜአለሁ!”

118 “ለብ ያለውን አንድ ብርጭቆ ወተት ጠጣበት፡” አለኝ። ኡህ፡ ወንድሜ! ለብ ያለ ወተት፡ ያቅለሸልሸኛል፡ ብቻ ሙሉውን ጠጥቼ ጨረስኩት።

119 አሁን፡ እግዚአብሔርም አለ፡ “ትኩስ ማለትም የቀላ-ትኩስ፡ ወይም ቀዝቃዛ፡ ከሁለቱ አንዱ፡ እንድትሆን እፈልግሃለሁ። ታቅለሸልሸኛለህና፡ ለብ ያልክ አትሁን።”

120 ይህ የቤተክርስቲያን ዘመን ለእግዚአብሔር እንዲሁ ነው፡ ያቅለሸልሸዋል! አያችሁ? “ወይም እንዲሁ ሁኑ… ወይም… አትሁኑ-… የቀላ አ-… የቀላ-ትኩስ ሁኑ ወይም… ለብ ያለ አትሁኑ! ትኩስ ወይም ሙቅ፡ ካልሆንክ ታቅለሸልሸኛለህ።”

121 በጆን ዌስሊ ዘመን የአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን ቅዝቃዜ የበረደች፡ ቀዝቃዛ ስለነበረች፡ ወደ ሌላ ቦታ ሰብሰባ እንዲያደርግ ተገዷል።

122 የሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን ቅዝቃዜ ዊልያም ቡዝን የቀላ-ትኩስ ሳሊቬሽኒስት እንዲሆን አደረገው። አያችሁ፡ እግዚአብሔር እንዲህ አለው፡ “ንስሓ ባትገባ፡ መቅረዝህን ከስፍራው እወስደዋለሁ። ወሰጄ፡ ለሌላ እሰጠዋለሁ።” ስለዚህ የሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን የጆን ዌስሊን መቀደስን አልቀበልም ባለች ጊዜ፡ ዊልያም ቡዝ ሳሊቬሽን አርሚ ይዞ መጥቶ አስቀጠላት። በትክክል። ለምን? ድርጅት ስላደረጓት! እውነቱ ይህ ነው። ያቺን ድርጅት ባደረጓት ጊዜ እግዚአብሔርም፡ “ነገሩን ጠላሁት፡” አለ!

123 በኋላ… ዊልያም ቡዝ ወዲያውኑ መጥቶ አነሳት፡ ከዚያስ ሳልቬሽን አርሚስ፡ ምን አደረጋት? ተመሳሳይ ነገር ነው፡ ዞረው መጡና እንደገና ድርጅት አደረጓት። ከእሱ በኋላ ካምቤላይቶች መጡ፡ እና ጥቂት ጊዜ ደስ አላቸው፡ ከዚያም ጆን ሰሚዝ ባፕቲስቶች ጋር መጣ፤ ከዚያም በኋላ ናዝሪኖች መጡ፡ ከዚያም ከናዝራውያን በኋላ ጴንጤቆስጤ መጡ።

124 ናዝሪኖችስ፡ ምን አደረጉ? እራሳቸውን በተመሳሳይ ቀንበር አሰሩ፡ ተቋም አደረጓት።

125 በዚያ ጊዜ ምን መጣ? ሁለት ትንንሽ ቅርንጫፎች፡ ዘ ቸርች ኦፍ ጋድ እና ሌሎች፡ አደገው ወጡ። ምን አደረጉ? ተደራጀ፡ ለቀቃቸው።

126 ጴንጤቆስጤዎች ከኋለኛው ዝናብ በረከት ጋር ተነሱ፥ ምን አደረጉ? ተደራጁ፡ እነሱንም ለቀቃቸው። በትክክል።

127 አሁን ወደ መጨረሻው እንወርዳለን፡ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ እውነተኛ ጠንካራ ነገር ታያላችሁ። በጣም ጥሩ።

128 በጣም ጥሩ፡ የቀላ-ትኩስ ወይም—ወይም ቀዝቃዛ፡ ከሁለቱ አንዱ እንድትሆኑለት ይፈልጋችኋል። ለብ ያላችሁ አትሁኑ! ያልሆናችሁትን ለመሆን አታስመስሉ፡ ወይ ለእግዚአብሔር እሳት ሁኑለት ወይም ወደ—ወደ—ወደ ድርጅቱ ውስጥ ተመለሱ። እንዲሁ—ለብ ያላችሁ አትሁኑ!

129 አሁንም ተመሳሳይ ነገር ነው! አሁን ባሉ በእነዚህ... አብያተ ክርስቲያናት ያለው ነገር ተመሳሳይ ነው። ትኩስ ወይም ቀዝቃዛ እንድትሆኑለት ይፈልጋል። "ለብ" ያለውን አይወድም። ጴንጤቆስጤ የደረሰበት ደረጃ አሁን ያ ነው፡ ለብ ብለዋል። አልፎ አልፎ ፒያኖውን ነካ ነካ ያደርጉታል፡ ጥቂት ድራም፡ ትንሽ መታ መታ ያደርጋል፡ ከዚያ ሙዚቃው ያጥለቀልቀዋል፡ አንደኛውም ይነሳና... እንደምታውቁት፡ እንዲህ ይላል፡ "ጌታ ይባረክ! ሃሌሉያ!" ኧሃ-ሃህ። ከዚያ ሙዚቃው ረገብ ይላል፡ "ኧሃ፡ ኧሃ፡ ኧሃ፡ **ኧሃ**፡" ይኸው ነው። ኡህ፡ ማይ፡ የእግዚአብሔር ሆዱን ያቅለሸልሸዋል! አያችሁ? ኡኧሃ-ሃህ። በጣም ጥሩ።

130 የቀላ-ትኩስ ሪቫይቫል እንደሚያስመስሉት ሁሉ፡ ምንም የሚፈጠር ነገር የላቸውም፡ ቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ ግን እጅግ ብዙ ሜካኒካል መሣሪያዎች አላቸው፡ አያችሁ፡ ምክንያቱ ባለ ጸጎች ስለሆኑ፡ ኡህ፡ ማይ፡ አንድ ላይ በመሆናቸው እና ታላላቅ ጉባኤዎችን በማድረጋቸው ምክንያት ነው። በቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ ጥሩ ጊዜ አሳልፈዋል፡ ያ ሁሉ እውነት ነው፡ ሁሉም ግን መካኒካል መሣርያዎች ናቸው። እንጂ የመንፈስ ቅዱስ ሙቀት የላቸውም። አያችሁ?

131 እዚህ ላይ የተናገረውን ተመልከቱ፡ እዩት፦

> **ሥራህን አውቃለሁ፡... በራድ ወይም ትኩስ አይደለ**ህም፤ **በራድ ወይም ትኩስ** ብትሆንስ **መልካም በሆነ ነበር።**
>
> **እንዲሁ ለብ** ስላልህ፡... **በራድ**ም **ወይም ትኩስ ስላልሆንህ፡ ከአፌ ልተፋህ ነው።** (አያችሁ? )

132 አሁን፡ እንዲህ አለው፡ "በራድ ወይም ትኩስ ብትሆንስ። እንዲሁ ስላልሆንክ ግን፡ እ—እነሆ አስወግድሃለሁ፡ በቃ፡ ከአፌ ጠራርጌ አጠፋሃለሁ።"

133 አሁን፡ ብዙ ገንዘብ ነበራቸው፡ ጥሩ ሕንፃዎች ነበሯቸው፡ ታላቅ ነገሮችም ነበራቸው፡ የመንፈስ ቅዱስ ሙቀት ግን አልነበራቸውም። አቤት፡ ልዩ መሣሪያዎች-... እ—አገዛዞች አሏቸው። ኡህ፡ ማይ! የተባበሩት የቤተ ክርስቲያን አንድነት ፈጥረዋል፡ ይገርማል፡ ኡአይተውት የማያውቁትን ህንጻዎች፡ እና ብዙ ነገሮች ሆኖላቸዋል፡ መንፈስ ቅዱስ ግን አልነበራቸውም። አያችሁ? እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን የላከው፡ መንፈስ ቅዱስ ነው።

አሁን፡ በዚህ 16ኛው ቁጥር እንቀጥል።

134 ሁሉም አይነት ኮሚቴዎች አሏቸው፡ "ኡህ፡ ለዚያ የሚሆን ታላቅ አስተዳደር አለን። የአሮጌት የእናቶች ማሕበር፡ እና የ—የወጣት ወንዶች ፒኒኮል ጨዋታ፡

እና—የአርብ ማታ የቡንኮ ጨዋታ፡ እና የ—የእሁድ ከሰአት የቅርጫት ኳስ ጨዋታ፡ እና፡ ኦህ፡ የቤዝቦል ጨዋታ **ወዘ-ተረፈ-ናቸው።** እና፡ ኦህ፡ የ—የወንዶች ተጨዋቾች ማህበርም አሁን መሰርተናል። እና፡ ኦህ፡ ሁሉንም አይነት ነገሮች መሰርተናል።"

135 አላችኋለሁ፡ ማሕበሮች፡ እና ክለቦች፡ ቢትኒኮች፡ እና ሌሎች ነገሮች ሁሉ፡ በደንብ ጭናለች፡ የመንፈስ ቅዱስ ሙቀት ግን የለም። አያችሁ፡ ትልቅ አገዛዝ አሏችሁ፡ አንዳች የሚያሞቅ ነገር ግን የለውም። ለአለም እያሞቃችሁ ነው ለእግዚአብሔር ግን አይደለም፡ ለብ ያላችሁ ለዚህ ነው።

136 ኦህ፡ ከመቼውም ጊዜ በላይ አባላት አፍርታችኋል። "በትክክል፡ ወዳጄ! ለምን፡ በ 44 ውስጥ አንድ ሚሊዮን ተጨማሪ እናፈራለን፡" አለ ባፕቲስቱ። ያፈራችሁት—ግን ምንድነው? ትልልቅ መሣርያዎች ብቻ!

137 ያንን አስተያየት በሰማሁበት ቤተክርስቲያን ውስጥ፡ ፓስተሩ ተናፍሶ እንዲመለስ፡ ዲያቆናት እና ሌሎቹም ከእርሱ ጋር፡ እንዲያጨሱ፡ እና እንዲመለሱ፡ አስራ አምስት ደቂቃ እረፍት ይሰጣቸዋል። እያችሁ? ይኸው ነው። መጽሀፍ ቅዱስ እነዚህን ነገሮች በግልጽ ያወግዛል! "ይህን አካል ብታረክሱት... "

138 ዶክተሮቹኮ "በካንሰር ተበልቷል፡" በማለት ያወግዙታል። ከዚያም ሬዲዮ ላይ ገብተው "የባለ አእምሮ ማጣሪያ፡" ያስተዋውቁታል።

139 ቢሊ ግራሃም እንደተናገረው፡ "በመጀመሪያ እንደዚያ ማሰቡ ራሱ ሞኝነት ነው።"

140 "የባለ አእምሮ ማጣሪያ፡" **አእምሮ** ያለው ሰው'ማ ፈጽሞ አያጨሰም፡ በትክክል፡ ሁለተኛውን አሳብ ተቀበሉ። ሴቶቹንም ቆንጆ ቀጫጫ ያደርግሻል ይሏቸዋል፡ አያችሁ፡ የገዟቸውን አዳዲስ ዓይነት ቀሚሶች እንዲለብሱ በማለት ነው። ጉድ ነው፡ ያ በደንብ ያሸጥላቸዋል! በዚህ ሰዓት ከሚያጨሱ ወንዶች ይልቅ ሴቶች በዝተዋል፡ ሲጋራን በማጨስ፡ ከወንዱ ይልቅ ሦስት ለአንድ፡ ትበልጠዋለች። በትክክል እውነት ነው፡ ምክንያቱም ቀጭን መሆን ትፈልጋለች። እንደዚያ የሚያደርጋት ነገር ቲቢ እና ካንሰር እና ሌላው እንደሆነ አላወቀችም፡ ልክ በህፃን መልክ፡ ወደ እርሷ ይመጣል፡ እንዲሁ ይበላታል፡ ይገድላታል። ከዚያ ክፉ እንጂ ሌላ ነገር አይገኝም! በትክክል። አያችሁ? ያ ግን "የ—የባለ አእምሮ ሰው ማጣሪያ፡" ይባልለታል። ሃህ! ኦህ፡ ማይ!

141 "አይ! አይ! ኦህ፡" ሲያመካኙም፡ "ወንድም ብራንሃም ሆይ... እንዲህና እንዲያ'ኮ አለን፡ ይህ'ማ አንቀበልህም! ሰብሰባዎቻችን ታላላቅ ናቸው! ቢሊ ግራሃም በመላ አገሪቱ የሚያደርገውን ተመልከተው።" ኦህ፡ አዎን፡ ታላላቅ አገዛዞች፡ ቅጥረኞች ወንጌላውያን፡ ቅጥረኞች የመዝሙር መሪዎች።

142 አዎን፡ ወንጌላውያንን ይቀጥራሉ። "እሺ፡ ሪቫይቫሉ ጋር ተገኝቼ ካገለገልኩ ስንት ትከፍሉኛላችሁ? እሺ፡ እጅግ **ጠቀም-ያለ** ሺ ዶላሮች ካልከፈላችሁኝ አልመጣም። በትክክል። ዝማሬውን እንዲመራ ማንን ትጠራላችሁ? እሺ፡ ሂዱና **እከሌ-እና-እከሌ** ቅጠሩ፡ እርሱ ታላቅ የሶስሎ ዘማሪ ነው። እሱን ከቀጠራችሁ... ግማሹን ህዝብ ይሰብልኛል፡ ያደርገዋል።"

143 ቅጥረኛ የሶሎ ዘማሪ! ቅጥረኛ ወንጌላውያን! ለምን፡ ነፍሳትን-ማዳን ንግድ ሆኗል። ነፍሳትን-ማዳን የቤተክርስትያን ስራ አይደለም፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያለው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው እንጂ። ነፍሳት-ማዳን ማለት... በገንዘብ አትገዙትም። አይደረግም፡ ወዳጄ! አይደረግም! ይህ ሁሉ፡ ስራ፡ ስራ፡ ስራ ነው፡ ቅጥረኛ ወንጌላውያን፡ ቅጠረኛ መዝሙር መሪዎች፡ ቅጥረኛ ኳየሮች፡ ሌላው ሁሉ። እግዚአብሔር ይህን አይፈልግም፡ እነዚህ ሁሉ ሰራዎች ናቸው! እግዚአብሔር ሥራን አይፈልግም፡ መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ውስጥ እንዲሠራ ይፈልጋል እንጂ። ትክክል ነው።

144 17ኛው ቁጥር እንዲህ ይላል፦

> **... ፡ባለጠጋ ሆኜአለሁ፡ የምትል ስለሆንህ ሃብታም ነኝና፡ አንድም ስንኳ አያስፈልገኝም፡ የተራቆትህም መሆንህን ስለማታውቅ፡** (ኦህ!)... **ጐስቋላና፡... ምስኪንም፡... ድሀም፡... ዕውርም፡ የተራቆትህም መሆንህን ስለማታውቅ፤** (እህም! እህም!)

145 የዚህ የዘመን-ፍጻሜ ጴንጤቆስጤዎች “ሃብታም” ነን፡ ብለው አሰቡ። አሳባቸውም... በውጭ ሲታዩ እውነት ነው። አዎን፡ ወዳጄ። ሃብታሞች ናቸው። ከጥቂት አመታት በፊት የነበረችውን ቤተክርስትያን እስቲ አስቧት፡ አንድ ጥግ ላይ የተጣለች፡ ከቦታ ቦታ የምትንከራተት፡ ከባድ ጊዜ ታሳልፍ ነበር። አሁን ግን አሉ የተባሉ ታላላቅ ህንጻዎች አፍርታለች።

146 በአንድ ተራ የእንጨት ሕንጻ ውስጥ የነበሩ አሴምብሊስ ኦፍ ጋድ፡ የት እንደደረሱ ተመልከቷቸው። እንደዚህ ያለ ነገር ነበሩ፡ አሁን የስድስት-ሚሊዮን-ዶላር የሚያወጣ ሕንፃ እያስገነቡ ነው፡ ደግሞም “ኢየሱስ ወዲያው ይመጣል፡” ይላሉ። ስራዎቻችሁ ይህን እንደማታምኑ ያረጋግጣሉ። ግብዝነት ነው! በሚሊዮን-ዶላር የሚቆጠር ህንጻዎችን እና መሰል ነገሮችን በመገንባት፡ “ኢየሱስ ወዲያው ይመጣል፡” ይላሉ። ድሃ ሚሽነሪዎች ግን፡ ፈሪሃ-እግዚአብሔር ያላቸው እውነተኞች ሚሽነሪዎች፡ ለእግራቸው ጫማ እንኳ ሳይኖራቸው በየመስኩ ይገኛሉ፡ ለእግራቸው ጫማ ሳይኖራቸው፡ ለሳምንት በሁለት ራሽን እየኖሩ፤ ወንጌልን በጫካ ውስጥ እና በመሳሰሉት ነገሮች ለወንድሞቻቸው ለማድረስ፡ በሳምንት ሁለት ጊዜ ይመገባሉ። እኛ ደግሞ ስድስት-ሚሊዮን-ዶላር የሚገመት ህንፃዎችን፡ እና ቤተክርስቲያኑን፡ በትልቅ የመስታወት መስኮቶች፡ እና በልዩ ልዩ ነገሮች ገንብተን፡ እናስቀምጣለን። ኦህ፡ አንዳንድ ጊዜ በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ የብድር ማኅበራት እስኪያቋቁሙ ድረስ ብዙ ገንዘብ አከማችታችኋል። ትክክል ነው!

147 ወንጌላውያንን ወይም ሚሰዮናውያንን የሚመረምሩ የግል ዶክተር አሏቸው። ወደ መስክ ሊወጣ የተዘጋጀውን፡ ብቁ እንደሆነ የዶክተር ምርመራ ይደረግለታል... ወይም የሚበቃ መሆኑን ለማየት፡ የሳይካትሪስት... ኦህ፡ ማለት የአእምሮ ብቃቱ ትክክል ነው አይደለም፡ ኢያችሁ። መንፈስ ቅዱስ ራሱ የመረምራል፡ ሳይካትሪስት አያስፈልጋችሁም።

148 “ግን፡ ሃብታም ነኝ ምንም አያስፈልገኝም።” አቤት፡ በትክክል። የተትረፈረፈ ገንዘብ አከማችታችኋል። ከውጭ ስትታዩ፡ የተትረፈረፈ ሃብት፡ ግዙፍ ህንጻዎች፡ ባለ ቀለም መስታወት መስኮቶች አላችሁ።

149 እንደበተ ርቱዕ ሰባኪዎች! ኦህ፡ ማይ። አቤት፡ እኔ ልንገራችሁ፡ እህም፡ በእውነት እንደበተ ርቱዕ ናቸው። ሌሊቱን ሙሉ ቆመው ማውራት ይችላሉ፡ ምንም አይናገሩም። አያችሁ? በተነሡ ጊዜ... ማለቴ መናገር የሚገባቸውን ነገር፡ አያችሁ። ይቆሙና፡ ስለ አንዳንድ ኩታራ ነገሮች፡ ስለ **እከሌ-እና-እከሌ** እንዲሁም ስለ **እከሌ-እና-እከሊት** ያወራሉ። እንዴት እንደሆነ ታውቃላችሁ። ቅጥረኛ ዘማሪዎች። በትክክል። እሺ። ወደ ቹልቢቱ፡ እንደበተ ርቱዕ ሰባኪዎች ይወጣሉ። ቶክሲዶ ልብስ ካልለበሱ አንገትጌአቸው ወደኋላ ካልዞረ፡ እና ከኋላ-የተንጠለጠለ ኮት ካልደረቡ፡ እንዴ፡ ጉባኤቸው ይሸማቀቅባቸዋል።

150 ዘማሪዎቻቸው ሲወጡም፡ ሴቶቹ፡ እንደ ኤልዛቤል አይነት አጫጭር ጸጉር፡ ጉሮኖ የሚቀባ ያህል ቀለም ፊታቸው ላይ። የመኝታ ልብሳቸውን ባወለቁ ቅጽበት፡ ቁምጣዎቻቸውን እና የወንዶች ልብሶች ይለብሳሉ፡ መጽሐፍም እንዲህ አለ፡ "ሴት የወንድን ልብስ ብትለብስ፡ በፊቱ አስጸያፊ ነው።" አፍንጫቸውን ገትረው በየመንገዱ ይዞራሉ፡ ዝናብ ቢዘንብ ያስጥማቸዋል። ሊቅ መሳዮች፡ ትዕቢተኞች፡ ቶሎ-የሚቆጡ ኤልዛቤሎች! በእንደዚህ አይነት ሪቫይቫሎች ውስጥ የማንሆንበት ምክንያት ይህ ነው፡ ታላቅ የመሣሪዎች ትዕይንት ነው።

151 አቤት፡ ድምጻችሁ እንደ ሊቀ መላእክት ድምጽ መረዋ ሊሆን ይችላል፡ ስለዚያም እግዚአብሔር ይጠይቃችኋል! እነ ኤልቪስ ፕረስሊ እና ሌሎች፡ እነ ኤርን ፎርድ፡ ወይም ጥሩ ድምጾች ያላቸው ሌሎች በሙሉ ለዲያብሎስ የሚጠቀምባቸ ሁሉ፡ እግዚአብሔር "ከእጃቸው እቀበላለሁ፡" ብሏል።

152 ዓይነ ስውሯን ፋኒ ክሮስቢን የማከብራት ለዚህ ነው፥ ስጦታዋን ለአለም ሸጣ አታውቅም። ለእግዚአብሔር ጠበቀችለት።

153 እነዚህ ሰዎች ብዙዎቹ እንደበተ ርቱዕ ዘማሪዎች፡ እንደበተ ርቱዕ ሰዎች፡ ታላላቅ ሰዎች፡ ወዘተ፡ ተሰጦዎቻቸው ለእግዚአብሔር ከመጠቀም ይልቅ፡ ዲያብሎስ አጣምሟቸው እነሆ ለእርሱ ይሰራሉ። ሰብእናዎች፡ የራዲዮ እና የቴሌቪዥን ሰብእናዎች፡ እራሳቸውን የሚሸጡ፡ እራሳቸው ለእግዚአብሔር ከመስጠት ይልቅ ለዓለም የሚሰጡ። አንዳንዶቹ ወደ ቤተ ክርስቲያን መጥተው፡ ትልቅ ውድ ልብስ ለብሰው፡ ቤተ ክርስትያን ይገባሉ፡ እንዲህ ይመጡና ይዘምራሉ፡ ቀጣዩ ምሽት ላይ ወጥተው ይሄዱና ሮክ-ኤንድ-ሮል ይዘፍናሉ። የምናውቃቸው፡ የአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ዘማሪዎች፡ ይወጡና ፎቶዎች፡ ተንቀሳቃሽ ምስሎች ይነሣሉ፡ እየወጡ ሮክ-ኤንድ-ሮል ይዘፍናሉ። የሮክ-ኤንድ-ሮል ንጉሶች፡ እና ሃይማኖተኛ ነን ባዮች! የሰይጣን ተንኮል ነው!

154 በቂ እና ትክክለኛ—በቂ አስተሳሰብ ላለው ሰው። ሰባኪ እሆናለሁ ለሚል ሰው፡ እሁድ ጠዋት ለሰብከት የሚነሣ፡ ከዚያ በኋላ ወርዶ... ወደ ራዲዮ ሰርጭት ይሄድና ሮክ-ኤንድ-ሮል ይዘፍናል ሌሎች ነገሮችም ያደርጋል፡ በስተመጨረሻ ሸጉጡን አንስቶ ራሱን ይፈረክሳል። ያን በማድረጉ አከብረዋለሁ። ትክክል። ትክክል። ከ—ከ እነዚያ የተሻለ... እንደ አሳማዎቹ ያህል አስተሳሰብ ይኖረዋል፡ ብቻ፡ ዲያብሎስ በገባባቸው ጊዜ ወደ ውኃው ዘለው ገቡና ታፍነው አለቁ። አንዳንድ ሰዎች ያን ያህል እንኳ የላቸውም።

155 አውቃችኋለሁ... እ—እንዲህ አይነት ከባድ በመሆኔ ደስ አይለኝም፡ ግን፡ እህት፡ ወንድሞቼ ሆይ፡ ነገሩን በደንብ ጠበቅ ለማድረግ—እንዲህ

አርጋችሁ—በደንብ ማዞር አለባችሁ! ይህ የምንኖርበት ቀን ነው። ኢየሱስ ሄሮድስን "ያቺን ቀበሮ" ካለው፡ዮሐንስም "የእፉኝት ልጆች" ብሎ ከጠራቸው፡ እንግዲያውስ መልካም ነው እላለሁ።

156 ትልልቅ ህንጻዎች፡ ባለ ቀለም መስታወት መስኮቶች፡ እንደበተ ርቱዕ ሰባኪዎች፡ ቅጠረኛ ዘማሪዎች አሏቸው። አዎን፡ ወዳጄ። በውስጡ ማን አለ? ማን አለ? ከመንፈስ ቅዱስ አይደለም። እዚያ ሄደው በቁምጣ ይቆሙና፡ እዚህ መጥተው ኳየር ውስጥ ይዘምራሉ። እናንተ ራቁታም ግብዞች! እንዲሁ፡ ናችሁ። በትክክል።

157 እናንተም፡ ሌላ ቦታ የማታገኙትን ገንዘብ እዚያ ስለሚሰጣችሁ ብቻ የምትሄዱ፡ ሰባኪዎች ሆይ! ወንበዴዎች ናችሁ፡ ፑልቢት ላይ ለመውጣት አትበቁም። በትክክል። ገንዘብ! "**እጅግ-ብዙ** ሺህ ዶላሮችን ካልከፈላችሁን፡ በቀር፡ አንመጣም። ማ—ማ—ማኔጀሮቻችንን እና ሌሎችን እንልካለ፡ ገንዘቡን ካስገባችሁልን እንመጣለን። ከሁሉም ጋር ሙሉ ትብብር ካላገኘው፡ አልመጣም። ሁሉም በአንድነት ካልተባበሩ (አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ) ዕዳዬን የምከፍልበት ሙሉ ገንዘብ ካላዘጋጁልኝ፡ አልመጣም።"

158 ወንድሜ፡ እውነተኛ የእግዚአብሔር ሰው፡ መባው ምንም ያህል ቢሆንም መንፈስ ቅዱስ ቢመራው ይሄዳል። የሶዳ ብስኩቶችን ቢበላ እና የምንጭ ውሃ መጠጣት ካለበትም ይሄዳል። ትክክል፡ እውነተኛ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነው።

159 ሰዎች ግን በሬዲዮ እና በቴሌቭዥን እና በሰርጭት፡ ያን አይነት ገንዘብ እስኪያገኙ ድረስ፡ በሁሉም የአለም ነገሮች እራሳቸውን ያሰራሉ። በትክክል እውነት ነው። አያችሁ? ያ እግዚአብሔር አይደለም።

160 አለውም፡ "ኦህ፡ ሀብታም ነህን፡ ምንም አትፈልግም።" አዎን፡ የምትፈልገው ዋናው ነገር፡ ገና የለህም። በትክክል። ነገር ግን አታውቀውም። አያችሁ፡ "እንዳች የማያስፈልገኝ፡ ሃብታም።" ስለ ስራዎቻቸው የሚከፈላቸው፡ የካርታ-ቁማርተኞች። "ኦህ፡" "ትልልቅ ጉባኤዎች አሉን፡" ትላላችሁ። ኦህ፡ በትክክል። አዎን፡ ወዳጄ። "ትልቁ ጉባኤ! ታውቃላችሁ፡ የ—የከተማይቱ ከንቲባ፡ ቸርቻችን ይመጣል።" ኧሃ-ሃም። በትክክል። "ታውቃለህ፡ እነ፡ **እከሌ-እና-እከሊት፡** ወደዚህ ከተማ ሲመጡ፡ ወደ ቸርቻችን ይመጣሉ።" ኧሃ-ሃም። "ታዋቂ ሰዎች ሁሉ እና ቸርች ይመጣሉ።"

161 አዎን፡ ድሆች እና፡ ቅዱሳን ችግረኞች ወደ ቤተክርስቲያን ቢገቡ፡ እንደ ተረገሙ ትቆጥሯቸዋላችሁ። በእናንተ ዘንድ አትፈልጓቸውም። እየሰበካችሁ ሳላችሁ "አሜን!" የሚል ሰው ትፈራላችሁ።

162 በአንድ ትንሽ መጽሐፍ ውስጥ አንድ ጊዜ እንዳነበብኳት፡ አንድ ሴት ወደ ቤተ ክርስቲያን ገባችና። ልጆቿን፡ በእውነተኛ ፈሪሃ-እግዚአብሔር በጥንቱ ዘመን የቤተ ክርስቲያን አምልኮ ጫካ ውስጥ አሳድጋቸዋለች። ስለዚህ አ... አንድ ወጣት አንድ ቀን መጥቶ ልጅዋን አገባት። እና **የእህት** ቤተ ክርስቲያን አባል ነኝ አለ፡ እንደምታውቁት፡ ከሃይማኖት ተቋማቸው የዋናው እና የትልቁ ተቋም እህት ተቋም ነው። ስለዚህ እናቲቷን ክርስቲያን ነኝ ብሎ ነገራቸው። እና ልጃቸውን አግብቶ ወጣ።

163 እና፡ በመጨረሻ በተራራ ላይ ካለችው ትንሽዋ የገጠር ቤተክርስቲያን አውጥቶ፡ እዚህ ወዳለው ግሩም፡ እና ታላቅ ቤተ ክርስቲያን፡ አስመጣት፡ ተመሳሳይ ሰም፤ በዚያ ግን መንፈስ ቅዱስ አላቸው፡ እዚህ ጋር ምንም ነገር የላቸውም። እና እነሆ ወደዚህ፡ ታላቅ እና ግሩም ቤተ ክርስቲያን ገቡ።

164 እና እናትየው እንዲህ አሉ፡ አንድ ቀን፡ ልጃቸውን ለማየት—ወረዱ። እና፡ የሚያደርጓት ጠፋባቸው። እና ሲያዩአት ነዋየ መጻህፍት መሰላለች፡ ልክ እንደሌሎቹ፡ ሃይ-ኔክ ልብስ ለብሳለች፡ እንደምታውቁት፡ ረጅም እጅጌ፡ ጸጉሯ ወደ ኋላ ለጥ ብሏል፡ የተነሣ ሽንኩርት-ፊት መሰላለች፡ እንደው (ላይ ላዩን፡ እንደተላጠ)። ወረደችና፡ እንዲህ አለች፡ "እሰይ፡ ሃሌ ሉያ፡ የኔ ማር! ሁላችሁም ደህና ናችሁ?" እና፡ "እነሆ፡ ጠዋት እሁድ ነው፡" አለቻቸው። አሏትም፡ "ሁላችሁም ልትሰበሰቡ ነው፡ አይደል?"

165 (ባልየውም፡ "ምን እናድርጋቸው?" አለ፡ "እንዲህ ሆነው ልንወስዳቸው አንችልም!" እና "እንጃ፡ ምን ማድረግ እንዳለብን አላውቅም፡" አለ።) ደህና፡ አላቸውም፡ "ይኸውሎት፡ እማማ፡ እኛ..."

166 "ኦህ፡" "ግን'ኮ፡ የኔ ልጅ፡ ከቸርች መራቅ አልፈልግም። በርግጥም እዚህ ሰፈር **እከሌ-እከሌ** የሚሉት ቸርች አለ፡" አሉት። "ኦህ፡" እሳቸውም... እንዲህ አላቸው... "እዚያ ማዶ ላይ አንድ አይቻለሁና፡ ወደዚያ እሄዳለሁ፡" አሉት።

(እርሱም "ኦህ፡ እሺ፡ እኛም እንሄዳለን፡" አላቸው።)

167 ሄደው በደረሱ ጊዜም፡ ቀድመው እንዲገቡ አደረጓቸው፡ (እያችሁ?) አፍረውባቸው ነው። እነሆ እንደምታውቁት፡ ከዚያ ከምስኪን አለባበሳቸው ጋር መጽሐፍ ቅዱሳቸው ከብብታቸው ሰር አቅፈው፡ ወደ ጎዳናው መጡ። ወንድሜ ሆይ፡ **ማን የማን** ነው በሚሉት ነገር፡ ሰማቸው የማይታወቅ ሊሆን ይችላል፡ ሰማቸው ግን በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ላይ እንደነበረች አሰባለሁ። ዋናው ነገርም ያ ነው።

168 ወደ ቤተ ክርስቲያን እንደገቡ፡ ወንበር ለይተው፡ እንዲሁ ቁጭ አሉ፡ መጽሐፍ ቅዱስ ከፈቱና ማንበብ ጀመሩ። ከዚያ ሰው ሁሉ መገላመጥ ጀመረ፡ የሆነ ዘመን ያሰቆጠረ ነገር እንደወረደባቸው አሰቡ። እንዲህ ሲያገላመጡ፡ "ኦህ፡ ማይ!" የምታውቋቸው፡ የተለመዱ የሎዶቅያ ሰዎች፡ ውድ ልብሶቻቸው ለብሰዋል፡ የሚያምር ልብሳቸውን እና የመሳሰሉትን ሁሉ። ወደ ኋላ መለሰ ብለው ሲያዩ ምስኪን እናት እዚያ ተቀምጣለች፡ ፊቷ ላይ ትልቅ ፈገግታ ይታያል፡ እንዲሁም፡ መጽሐፍ ቅዱሰን ታነባለች። አዎና።

169 ፓስተሩም፡ ከትንሽ ጊዜ በኋላ፡ ሌሎቹን ነገሮች ሁሉ ካለፉ በኋላ፡ በስተመጨረሻ፡ የአሰራ አምሰት ደቂቃ ንግግር አደረገ። ተነስቶ "ጌታ መልካም ነው፡" አለ።

170 እሳቸውም "እግዚአብሔር ይመስገን! እውነት ነው! ሃሌሉያ!" አሉ፡ ወዲያውም ሁሉም እንደ ዳክዬ አንገታቸውን ሰግግ አረጉና፡ ተገላመጡ፡ "ማን ነው?"

171 ትንሽ ቆየና፡ እንዲህ አለ፡ "እሕ! እሕ! እሕ!" እንዲህ አለ፡ "በየትኛውም ዘመን ያሉ ክርስቲያኖች ደፋሮች፡ ጀግኖች፡ ኩሩዎች ክርስቲያኖች፡" ወይም እንዲህ አይነት ሰርዓት ሊኖራቸው ይገባል አለ።

172 እሳቸውም አሉ፡ “እግዚአብሔር ይመስገን! እውነት ነው!” ከዚያ ሁሉም ዙርያውን ተገላመጡ።

173 እርሱም፡ “እሕ!” አለና ወደ ዲያቆናት ሰብሳቢ ዞር ብሎ አየ።

174 ዲያቆናት ሰብሳቢው አሳቡን ተረዳና። ሴቲቱን በክንዳቸው ይዞ ከበር ውጭ አስወጣቸው፡ “ፓስተሩን እያቋረጡት ነው፡” አላቸው።

175 ሞታችኋል ነገር ግን አታውቁትም! አዎን። አቤት፡ በቀለም ያጌጠው መስታወታችሁ ምን ይጠቅማችኋል? ምንጣፎቻችሁ ምን ይጠቅማችኋል? የሐይማኖት ተቋማችሁ ሁሉስ? እንደ ውሻ ወደ ትፋቱ፡ በቀጥታ ገሃንም መግባት ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ ከሌላችሁ፡ ጠፍታችኋልና! ዳግመኛ ካልተወለዳችሁ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ማየት አትችሉም።

176 አዎን ይመራል። ለእኔ ካስተር ኦይል እንደመጠጣት ነው፡ “እማዬ፡ እኔ አልችልም፡” እላት ነበር።

177 “እንዲህ ካላቅለሸለሸህ፡ አይጠቅምህም፡” ትለኛለች። ስለዚህ ይህም ደግሞ እንዲሁ፡ ተመሳሳይ ነገር ነው።

178 አቤት፡ እንዴ ሰትናገሯቸው! አቤት፡ ታላቅ፡ ውብ ህንጻዎች፡ ወዘተረፈ። አቤት፡ እ—እ—እነሱ... ወደ ቤተ ክርስቲያናቸው ግባና፡ እስኪ ተናገራቸው... ወደ ቤተ ክርስቲያናቸው ገብተህ እንዲህ በሏቸው፡ “ታዲያስ፡ እናንተ፡ ጴንጤቆስጣሎች ናችሁን? ”

“ኦህ፡ አዎና። ኧሃ-ሃህ። አዎን። ጴንጤቆስጤዎች ነን።”

“ዳግም በመወለድ ታምናላችሁ? ”

“አዎን።”

“እስኪ፡ አንድ ነገር ላሳይህ እንዴ... ”

179 “ኦህ፡ ይህን ህንጻ ተመልከተው! ይህ ህንጻ ምን ያህል... የህንጻው ዋጋ ታውቀዋለህ? ይህንን ለመሰራት የአንድ ሚሊዮን ዶላር ሶስት ሩቦች ፈጅቷል። ታውቃለህ፡ ከዚህ በፊት ይህ አልነበረንም። ከአውራ ጎዳናው ማዶ ላይ—ነበርን።” ኧሃ-ሃም፡ ዙርያውን ተመልከት፡ ያካበቷቸው እነዚያ ታላላቅ ነገሮች እዩዋቸው። አዎን፡ ወዳጄ። ከዚያ በኋላ እንዲህ ይላሉ፡ “ኦህ፡ እነዚህ ሁሉ—ነገሮች የኛ ናቸው!” ስለ ጠፉ ነፍሳት ግን ምንም ሸክም የላቸውም! ሁልጊዜ ምን ያህል ሕንፃ እንዳላቸው ሊያሳዩ ይፈልጋሉ። “የሰንበት ትምህርት ቤታችንን ዘገባ ተመልከት፡ እጅግ ትልቅ ነው!” መንፈስ ቅዱስን ከሌላቸው ያ ምን ይጠቅማል? “ሀብታም፡ ባለጸጋ፡ ምንም የማያስፈልገኝ።”

180 እንዲህ አላቸው፡ “እናንተ እንዲህ ነን ብላችሁ ታስባላችሁ፡ ድሃ፡ እና ጎስቋላ፡ ምስኪን፡ ዕውር፡ ራቁት ናችሁ። መሆናችሁን ግን አታውቁትም!” አያችሁ? ይኸው ነው።

181 እነርሱ ሲናገሩ፡ ኦህ፡ አዎን፡ “አየህ? ድሮ እንዲህ ነበርን... ትንሿ ቤተ ክርስትያናችን ከጀርባ ነበረች፡ ይሄኛው ትልቁ ነው!” ይኸውላችሁ፡ እነዚህ ሁሉ ነገሮች ሲሆኑላቸው ማየት ካልሆነ በቀር፡ ስለ ነፍሳት ግድ የላቸውም። የሴቶች እርዳታ፡ እና ሌሎች ነገሮች በሙሉ፡ በትክክል እንዲሰሩ ማሰብ እንጂ፡ ስለ ጠፉ

ነፍሳት ግድ የላቸውም። ኧረ፡ ሰዎች ሆይ፡ ምነው—ይህች ቤተ ክርስቲያን ምን ውስጥ ገባች!

182 ሸክማቸው ስለ ብልጽግና ነው እንጂ፡ የነፍሳት ሸክም የላቸውም። ይህ እውነት ነው። ሸክማቸው የተሳሳተ ነው። ስለ ብልጽግና ሸክም ነበራቸው እንጂ የነፍሳት አደራ ሸክም አይደለም። መጽሐፍ ሲናገር፡ "ጎስቋሎች መሆናቸውን አያውቁም፡" (ኦህ!) "ምስኪን፡ ዕውር።"

183 በገንዘብ ዓለምን መቀየር የሚችሉ ይመስላቸዋል። "ኦህ፡ በዚህ በምናዘጋጀው ፕሮግራም፡ ብዙ ገንዘብ መሰብሰብ ከቻልን፡ ዓለምን መለወጥ እንደምንችል እምናለሁ። ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ያሉ አንዳንድ ባለጸጎች፡ እንዲያው እንዲቆፍሩ ብናደርጋቸው፡ ወደ ምድር ሁሉ እየዞረ—ዓለም መለወጥ የሚችል ማህበረሰብ—መፍጠር እንደምንችል እምናለሁ። በአውሮፕላኖች እየሄድን፡ ጽሑፎችን በመላው አፍሪካ እና የመሳሰሉትን ማራገፍ እንችላለን። ትንሽ ገንዘብ ቢኖረን!"

184 ወንድሜ፡ አለም በገንዘብ አትለወጥም። ዓለም የምትለወጠው በመንፈስ ቅዱስ ነው፤ የመንፈስ ቅዱስ እና የመስቀል ታላቅ ሰብከት አለምን የሚቀይር ብቸኛው ነገር ይሆናል። የእግዚአብሔር ፕሮግራም ገንዘብ አይደለም። መንፈስ ቅዱስ ነው፡ ለሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ዘመን ወይም ለሌላ ማንኛውም የቤተ ክርስቲያን ዘመን የእግዚአብሔር ፕሮግራም ይህ ነው። አዎን፡ ወዳጄ።

185 መንፈስ ቅዱስን ይፈልጋሉ። እነርሱ ግን፡ ኦህ፡ "እኛ… ወርቅ አለን" ይላሉ። አዎን፡ ትክክለኛው ዓይነት አልነበረም እንጂ፡ ወርቅ ነው። ብዙ ወርቅ ነበራቸው ነገር ግን ትክክለኛው ዓይነት አልነበረም። እንግዲህ፡ በኢየሱስ የተመከሩት፡ "ባለጠጋ እንደ ሆንህ፡ ወርቅም እንዳለህ፡ ምንምም እንዳትፈልግ አውቃለሁ።" ግን፡-

**በእሳት የተፈተነውን ወርቅ ከእኔ** እንድት**ገዛ እመክርሃለሁ**፡…

186 ይህ ወርቅ፡ አዎን፡ በጋለ እቶን ስጥ የተፈተነ ሌላ ዓይነት ወርቅ ነው፡ በሞት እሳት መካከል አልፎ፡ በቀራንዮ አልፎ፡ የወጣ ነው።

187 አሁን አለን የምትሉት ወርቅ ሁሉ፡ ዝገት ነው፡ ይዝጋል። ማስታወሻ መያዝ ከፈለጋችሁ፡ ያዕቆብ… ቅዱስ ያዕቆብ 5፡1 እስከ 4፡ ምን እንደሚል ታዩታላችሁ፡ እንዲህ ይላል፡ "እናንተ ባለ ጠጎች፡ ሂዱ፡ የበጌታ ምጽአት ሆኗልና፡ መከራችሁ በራሳችሁ ደርሷልና አልቅሱ ዋያ ዋይም በሉ፡ ወርቃችሁም ይዝጋል።" አያችሁ፡ የሚዝግ ወርቅ ማለይ ይህ አይነቱ ነው።

188 ኢየሱስ የሚሰጠው ወርቅ ግን መንፈስ ቅዱስ ነው፡ ወደ ልባችሁ የሚፈሰው፡ ወርቃማው የመንፈስ ዘይት ነው። ስለዚህ—ስለዚህም፡ ኦህ፡ ማይ፡ "ባለጸጋ እንድትሆን፡ መጥተህ እንድትገዛ እመክርሃለሁ።" ኦህ፡ የሰ።

189 በተጨማሪ፡ ደግሞ "ዕውሮች" ነበሩ። ይህም፡ ከባድ ነገር ነው። እነዚህ ክርስትያኖች "እጭር ርቀት የሚያዩ" ስለነበሩ ፈጽመው ዕውራን ነበሩ አልልም። እጭር ርቀት የሚያዩ ናቸው እንደነበሩ እምናለሁ። ብቸኛው ማየት የሚችሉት ነገር ትልልቅ ህንጻዎቻቸው ብቻ ነው። ብቸኛው ማየት የሚችሉት ነገር ጉባኤያቸው ነው። የሚያዩት ብቸኛው ነገር በደንብ-የተሸለመ እና ያጌጠ ልብሶች የለበሱ ኳየሮቻቸው ብቻ ነው። እንደሚመስለኝ እጭር ርቀት የሚያዩ፡

ከአፍንጫቸው ማዶ፡ ለማየት የሚቸገሩ ናቸው። አጭር ርቀት ማየት የሚችሉ ነበሩ እንጂ፡ ዕውራን ነበሩ አልልም። የሚያዩት ነገራቸው ብቻ ነው… “እየሀ፡ ታውቃለህ? እኛ’ኮ ከእነ **እከሌ-እና-እከሊት** ጋር ነን!” ታላላቅ የሐይማኖት ተቋማቸው፡ ታላላቅ ጉባኤዎቻቸው፡ ብዙ አባላቶች፡ ሰንደይ ስኩላቸው፡ ውብ ህንጻዎቻቸው።

190 “ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ያስፈልጋቸዋል።” አላቸው ኢየሱስም። መንፈስ ቅዱስ ያስፈልጋቸዋል! ጌታም እንዲህ አላቸው፡ “አይናችሁ… ከተቸገረ… ዓይኖች ከተቸገሩ፡ እና እዚህ ካለው ትልቅ ሕንፃችሁ እና ከትልቅ ጉባኤያችሁ በስተቀር ሌላ ማየት እስካልቻሉ ድረስ ቅርብ የሚያዩ ናችሁ፡ እንዲሁም… የከታማይቱ ከንቲባ እና ወደ ቸርቻችሁ የሚመጡትን፡ እና ታዋቂዎቹን ብቻ የምታዩ ናችሁ። እኔን ረስታችሁኛል። አይነ ሰውር ከሆናችሁ፡ አይናችሁ ከታመማችሁ ግን፡ የአይን ኩል እሸጥላችኋለሁ።” አዎን።

191 አያችሁ፡ እነዚህ የሰነ መለኮት ዶክተሮች ይህ በእነርሱ ዘንድ አለመኖሩ የሚያስገርም ነገር ነው፡ አይደል? ብዙ ሸቶዎች፡ ብዙ ቲኦሎጂዎች አሏቸው። ይሁን እንጂ የጌታን መምጣት አጥርተው ማየት እንዲችሉ አይኖቻቸውን የሚታሹበት፡ የዓይን ኩል፡ ማለት መንፈስ ቅዱስ ያስፈልጋቸዋል፡ መጽሐፍ ቅዱስን አጥርተው የሚያዩበት፡ ቃሉን አጥርተው የሚያዩበት። እንዴት “ኤ-መን” እንደሚሉ በደንብ የተካኑ ናቸው። ሸቱውም፡ ዘይቶቹንም ሁሉ ነበራቸውና። “የዓይን ኩል” ግን፡ አስፈለጋቸው። አለ ጌታ። “ዓይኖቻችሁን ይከፈቱ ዘንድ፡ እነሆ ጥቂት የዓይን ኩል ያስፈልጋችኋል፡” አላቸው።

192 ትንሽ ልጅ በነበርኩ ጊዜ፡ እንዲህ ነበር… ይመስለኛል፡ ይህንን ተናግሬዋለሁ፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ ተናግሬ ሊሆን ይችላል። አሁን ወደ አእምሮየ መጣ። ያደግኩት፡ በከፊል በኬንታኪ ተራሮች ላይ ሲሆን፡ መኖሪያችን በጣውላ በተሰራው ያረጀ ቤት ውስጥ ነበር። እናቴ፡ ቤ… ቤቱ ላይ ትንሽ—ቆጥ ነበረ፡ ፍራሻችን—ከገለባ የተሰራ ነበር። ከዚያም በገለባ ፍራሽ ላይ የላባ ፍራሽ ልብስ ነበረበት። የላባ ፍራሽ ልብስ ታውቁት እንደሆነ፡ እና እንዳልሆነ እንጃ፥ የድሮ አልጋ ነው፡ እጅግ ድሆች ነበርንና። አባቴ እና እማ ምድር ቤት ላይ አልጋ ነበራቸው። እና ወደ ቆጡ የምንወጣበት መሰላል ነበረበት፡ እና እናቴ—አንዳንድ—አንዳንድ ጊዜ፡ የሆነ ነገር፡ እንደ ሸራ ነገር ትሸፍነዋለች፡ ጥቅሙም… እንደው፡ እንደምታውቁት… እንዲህ ተኝተን ባረጁ ጣውላዎች መካከል ከዋክብት እንቆጥራለን ጨረቃው ብርሃን አብርቶላቸው፡ እንደው፡ ጣራው ላይ ተለቅ ተለቅ ያሉ ቀዳዳዎች ነበሩበት።

193 እና ስለዚህ በረዶ ወይም የሆነ ነገር፡ ወይም ዝናብ በሚዘንብበት ጊዜ፡ ህጻናት የሆንን ሁላችንም—ከሸራው ስር እንገባለን፡ ይህም፡ ዝናቡን ለመከልከል… እርጥበቱን ለማስቀረት ነው። እና አንዳንድ ጊዜ በቀዳዳዎቹ በሚያልፉ ቅዝቃዜዎች፡ እ—እ—እንቀዘቅዛለን ዓይናችንም ይዘጋል። እነሆ፡ ሁላችንም በቅዝቃዜ እንዘጋለን፡ አይናችን ላይ ቅዝቃዜ ይይዛል። እና እናቴ በማለዳ “ኑ ውረዱ፡” እያለች ትጠራናለች። “መምጣት አልችልም፡ እናቴ፡ ዓይኖቼ ተጣብቀዋል፡” እላታለሁ። አያችሁ፡ አይኔ ላይ የሆነ ነገር—ይኖርብኛል፡ ቅዝቃዜ። ታውቃላልችሁ፡ አልከፈትም ይሉኛል። በዚያ የተኛን ሁላችንም ህጻናት፡ እኔ እና ሃምፒ ሌሎቹም አይናችን ለመግለጥ እንሞክራለን አንችልም፡ እንታወራለን።

194 ወንዱ እያቴ አጥማጅ ነበረ፡ ኩኖችን፡ ራኩኖችን ያጠምዳል። እና በቤታችን የነበረን መድኃኒት፡ የኩን-ቅባት ብቻ ነበር። ጫማዎቻችን በኩን ቅባት እንገርሰው ነበር። ግጎሮሮአችን ስንታመም፡ ትንሽ ከተርፐንታይን ይጨመርበታል፡ ከዚያ፡ ትውጡታላችሁ፡ ይህም፡ ለጉሮሮው ህመም ነው።

195 እና የሁላችንም አይኖች ሲጣበቁ፡ እናቴ ይህ ነገር ትይዝና... "እሺ፡ መጣሁ፡ የኔ ማር።" ወጥ ቤት ውስጥ ሮጣ የኩን ቅባት የያዘውን ትልቅ ኩባያ አምጥታ ትጥደዋለች፡ እና በደንብ ታሞቀዋለች። ከዛ ትመጣለች፡ እያችሁ፡ ነገሩ ሰራውን እስኪሰራ ድረስ አይናችንን ታሸናለች። እና ከጥቂት ጊዜ በኋላ ማየት እችላለሁ፡ ዓይኖቼን እከፍታለሁ። የኩን ቅባት ይ... ከፍተዋል።

196 እና እላችኋለሁ፡ በጣም አስከፊ የሆነ ቅዝቃዜ ያገኘናል! እያችሁ? አገሪቱን የሚያናውጥ ቅዝቃዜ ይመጣብን ነበር። ባፕቲስቶችም፡- "የተአምራት ዘመን አልፏል። መንፈስ ቅዱስ የሚባል ነገር፡ እና በልሳን መናገር የለም። በጌታ በኢየሱስ ስም ጥምቀት የለም።" እና፡ አቤት፡ ልዩ ልዩ አይነት ቅዝቃዜዎች፡ ብቻ የሆነ መንፈሳዊ ቅዝቃዜ ብዙ አይኖች ዘጋግቷል። ወንድሜ ሆይ፡ አይኖቻቸውን ለመክፈት ከኩን ቅባት በላይ የሆነ ነገር ይጠይቃል። ዓይኖችዎን ማሸት እና ማየት እንድትችሉ... ? ... አዲስ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን ይጠይቃል; የእግዚአብሔር ቃል እውነት መሆኑን እንድታዩ ቅርብ የማየት ችሎታችሁን አሰወግዱ። ትክክል። ኦህ፡ "ዓይኖቻችሁን የምትኳሉትን ኩል፡ ከእኔ ትገዙ ዘንድ እመክራችኋለሁ።" ስለዚህ... ስለዚህ...

197 የቲኦሎጂ ዶክተሮች የራሳቸው ይዘዋል... ሁሉም አይነት ቲኦሎጂ፡ እና ሽቶ ነገሮች አላቸው፡ ይሁን እንጂ ከዚያ የበለጠ ይጠይቃል። የሰማይ ኃይሎች ሲሠሩ ለማየት መንፈሳዊውን ራዕይ ለመስጠት መንፈስ ቅዱስ ያስፈልጋል። መንፈስ ቅዱስ፡ የመንፈስ ቅዱስ ኩል! ይህ ኩል የጋለ ቅባት እንደሆነ፡ እናውቃለን፡ ደግሞም መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ዘይት ነው።

198 እና እነዚያ ሁሉ ቲኦሎጆዎች እና ሽቶዎች፡ "ኦህ፡ ወንድሜ፡ ውዴ፡ ችግር የለውም ደህና ነህ። ምንም መጥፎ ነገር የለም... ሁሉም ነገር ደህና ነው። እንዴ፡ የከተማው ትልቁ ቤተክርስቲያን የእኛ ነው።" ያ ሽቶ አይሰራም! አይደለም፡ ጌታዬ! **እዚህ** ድረስ እንድታይ ይረዳሃል (አጭር ርቀት ማየት) ከዚያ "አዎን፡ ቤተ ክርስቲያናችን ከሁሉ ይልቅ ይተልቃል፡" ይላል። ነገር ግን እናንተ የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን አባላት ሆይ፡ እግዚአብሔር መልስ እንድትሰጡበት ስለሚመጣው ፍርድስ?

199 ንግግሬ እዚህ ላላችሁ አይደለም፡ በዓለም ዙርያ ላሉ በቴፕ ለሚያዳምጡ ነው፡ እያችሁ፡ ስለዚህ አሁን ለብዙ ሚልዮኖች እየተናገርኩ ነው፡ እያችሁ።

200 ስለዚህ ያ ነው። ሎዶቅያ! ለብ ያሉ! የወደቁ! አጭር ርቀት የሚያዩ! ሌላ ምን እንደምላቸው አላውቅም። በቅሎዎች! በቅሎ ድቅል ነው፡ የግል ተነሣሽነት የለውም። እንዴ ስትናገሩት፡ ትልልቅ ጆሮዎቹን ወደላይ ያነሣና፡ "ሃው! ሃው! ሃው! ሃው!" እያለ ይሄዳል፡ ምንም አይነት ደግነት የለውም። ዲቃላ ነው፡ የፈረስ እና የአህያ ውጤት ነው። አሁንም ጉዳዩ ያ ነው፡ ኒቆላውያንን እና ሎዶቅያዎችን አንድ ብታዳቅሉ፡ አሁንም አህያ ይወጣባቸዋል። እኛ የሚያስፈልገን... በትክክል። አያውቁትምም። ስለ መለኮታዊ ፈውስ፡ እና በኢየሱስ ስም ስለ መጠመቅ ንገሯቸው። "ሃው! ሃው! ፓስተሬ አላለም... ሃው!

ሃው! እኛ ፕረስባይተሪያኖች ይህን እናምንም፡” ይላሉ። አላዋቂዎች! ልትሏቸው የምትችሉት ይህ ነው... ? ...

201 እኔ በቅሎ እጠላለሁ። ይኸውላችሁ፡ ጥሩ፡ ረጋ ያለ የዘር ፈረስ እወዳለሁ፡ በቃ፡ አንዳች ነገር ልታስተምሩት ትችላላችሁ። እንዲሰግድ ልታስተምሩት ትችላላችሁ፡ ሰርከስ ውስጥ ታስገቡታላችሁ፡ እንደ ሰው መሆን ይችላል፡ ምክንያቱ... የሆነ ነገር ያውቃል። መረጋጋት አለው። በቅሎ አባቱ ማን ነው እናቱ ማን ናት አያውቅም፡ ራሱን ማራባትም አይችልም። እነዚህ አንዳንድ ያረጁ፡ የቀዘቀዙ፡ ተራ ተቋሞች ጋርም እንዲሁ ናቸው፡ እንደገና ፈጽመው አይነሡም። ቤተ ክርስቲያን ተቋም የሆነች ለታ፡ ሙት ናት! ዳግም አትነሳም። ይህ ምንድነው? ድቅል ነው!

202 ማርቲን ጥሩ ነበረ፡ በተደራጀ ጊዜ ግን ምን አደረገ? ሜቶዲስት ጥሩ ነበረ፡ በተደራጀ ጊዜ ግን ምን አደረገ? ጴንጤቆስጤ ጥሩ ነበረ፡ በተደራጃችሁ ጊዜ ግን ምን አደረጋችሁ? አዳቀላችሁት፡ ከካቶሊክ ከኒቆላውያን ጋር ተዳቀላችሁ። ያደረጋችሁት ነገር! የጥምቀቷን መልክ ዘረፋት፡ መንገዷንና ድርጊቷን ወሰደ፡ መጽሐፍ ቅዱስም እንዲህ አላት፡ “አንቺ ግልሙትና፡ የጋለሞታዋ ሴት ልጅ ነሽ። የግልሙትና ሴት ልጅ!” በትክክል!

203 ጥሩ የፈረስ ዝርያ፡ አይ፡ ጨዋ’ኮ ነው። አቤት፡ ደግ ነው። ራሱን ትከሻችሁ ላይ ያደርጋል፡ ሩህሩህ፡ እና አፍቃሪ ነው። ለምን? አባቱ ማን እንደሆነ ያውቃል፡ አያቱ ማን እንደሆነ ያውቃል፡ የአያቱ አባት ማን እንደሆነ ያውቃል። ጥሩ ዝርያ ስለሆነ፡ እጅ መንሣት ይችላል።

204 እውነተኛ ዘር የሆነ ክርስቲያን ማየት እወዳለሁ! ባለፈው ሳምንት ሜቶዲስት፡ በዚህ ሳምንት ባፕቲስት፡ በዚያ ሳምንት የጴንጤቆስጤ እምነት ተከታይ፡ ቀጣይ ሳምንት ፕሊግሪም ሆሊነስ፡ መሆኑ የሚገልጽ ደብዳቤ ያልያዘ ሰው። ይህ አባቱ ማን እንደሆነ እናቱም ማን እንደሆነች አያውቅም። ልንገራችሁ፡ ከእግዚአብሔር መንፈስ የተወለደ ሰው ግን ወደ ጴንጤቆስጤ ቀን ወድያው ይመልሳችኋል፥ ጥሩ ዘር መሆኑን፡ ጴንጤቆስጤ ነኝ ይላችኋል! አሜን! ከራሴ እስከ እግር ጥፍሬ ድረስ ጴንጤቆስጤ መሆን እፈልጋለሁ። የጴንጤ እምነት ተቋም ማለቴ አይደለሁም። ከሞት የተነሳው የክርስቶስ እውነተኛ ኃይል፡ የእውነተኛው የጴንጤቆስጤ በረከት ማለቴ ነው።

205 ኩል፡ ወደ ኋላ መለስ ብለን ለማየት ከየት እንደመጣ ለማየት ዓይንህን ክፈት። ዛሬ ያለችውን ቤተ ክርስቲያን ብቻ እያያችሁ ስለሆነ፡ ወደኋላችሁ መለስ ብላችሁ ከየት እንደመጣች ተመልከቱ፡ እና ወደፊት ወደ እግዚአብሔር ተጓዙ፡ ያን ጊዜ ከዚያ ትርቃላችሁ። አዎን፡ ጌታዬ።

206 እሺ፡ ሌላውም እንዲህ መባላቸውን፡ አስተውያለሁ፡ “ራቁታሞች ናቸው፡ እርቃናቸው ግን አያውቁትም።” አዎን።

207 ኦህ፡ እርቃን መሆናቸውን አያውቁም። እንግዲህ፡ አንድ ሰው ምስኪን፡ እውር፡ ጎስቋላ፡ እራቁት ከሆነ፡ እንዲህ አይነት ሰው ጎስቋላ ነው። እንግዲህ፡ መሆኑን ካ—ካወቀ፡ እራሱን ያርማል፤ ካላወቀ ግን፡ ይህ ድኃ ሰው አእምሮ የታወከበት ነው። ልክ ነው? አቤት! ጠንከር ይላል። በአእምሮው ጠፍቷል፡ እራሱን ለማረም በቂ እውቀት የለውም።

208 አንድ ምስኪን፡ ጎሰቋላ፡ ዕውር፡ ድሃ፡ እና ራቁት ሰው፡ በመንገድ ላይ ሲወርድ አይታችሁ፡ "ወንድሜ፡ እርቃን ነህ፡" ትሉታላችሁ። "ኦህ፡ ወይኔ? ኦህ፡ ኦህ፡ ወንድሜ፡ እርዳኝ፡ ልብስ ፈልግልኝ።"

209 ነገር ግን ወደ እነርሱ ቀርባችሁ፡ "ካመናችሁ ወዲህ መንፈስ ቅዱስ ተቀብላችኋል፡ ብትሏቸው? "

210 "አንተ ደሞ ማን ነህ፡ ወንበር-ሰባሪ? እሺ፡ ምን፡ ለማለት ፈልገህ ነው? አንተ እንዲህ አትለኝም፡ እኔ'ኮ ፕሬስባይቴሪያን ነኝ፡ እኔ ባፕቲስት ነኝ፡ ከእነ **እከሌ-እና-እከሌ** እና **እከሌ-እና-እከሊት** ጋር ነኝ።"

211 እርቃንህ አታውቀውም! እንግዲህ፡ እኔ አላልኩም፡ የተናገረው መጽሐፍ ቅዱስ ለዚህ ዘመን ነው፡ "እርቃን መሆንህን አታውቀውም። ና ከእኔ ዘንድ ልብስ ግዛ፡" አለው።

... **ነጭ ልብሰ**...

ነጭ ልብሰ የቅዱሳን ነው፡ የቅዱሳን ጽድቅ ነው። አያችሁ?

212 እርቃን? ኦህ፡ በትክክል! አዎን፡ ጌታዬ! ኦህ፡ አባባልህ፡ "ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ ቸርቻችን ማለትህ አይደለም፡ በከተማው ካሉ ሁሉ በአለባበስ ምርጡ የእኛ ነው!" ያንን አልጠራጠርም፡ አንዳንድ የቅርብ ጊዜ ፋሽኖች፡ ምርጥ የተቆረጡ ቁሳቁሶች፡ የቅርብ ጊዜዎቹ የሆሊውድ ኮከቦች ልብስ፡ ሴሰኛ ከመሆኑ በጎዳና ላይ ያለውን ወንድ ሁሉ ቀልብ ይሰባል። ኧሃ-ሃም። በትክክል።

213 አንዲት ሴት፡ እንዲህ አለችኝ፡ "ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ ምን ማለትህ ነው ንገረኝ? እንግዲህ፡ እነዚህ ቀሚሶች ከሱቅ የገዛናቸው ናቸው ገበያ ላይ ያሉት እነዚህ ብቻ ናቸው።"

214 እኔም "ጥሬ ዕቃዎች እና የልብስ ሰፌት ማሽኖች አሁንም ድረስ ይሸጣሉ። ይህ ምክንያት ሊሆን አይችልም፡" አልኳት።

215 "ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ከእርስዋ ጋር አመንዝሯል፡" ይላል መጽሐፍ ቅዱስ። ልክ ነው? እሺ፡ ታዲያ፡ ሴትየዋ እራሷን ሴሰኛ ልብስ ለብሳ ራሷን ከወንድ በፊት ብታቆም፡ ተጠያቂው ማን ነው? ሴትየዋ ናት፡ ቀስቃሽ ራሷ ናት። በትክክል እውነት ነው።

216 ምናልባት አሁን፡ ለባልሽ እንደ ሊሊ አበባ ንፁህ ልትሆኚ ትችያለሽ። በህይወትሽ ምንም ሰህተት የማታውቂ ወጣት ሴት ልትሆኚ ትችያለሽ፡ ባል ስታገቢም ድንግል ሁኚ። እንደዚህ ለብሰሽ ወንድ እንዲህ እንዲያይሽ ከዳረግሽ ግን፡ በልቡ ከ**አንቺ** ጋር አመንዝሯል። ያ ኃጢአተኛ አይቶሻልና። ክርስቲያን እንደመሆንሽ በከተማው ውስጥ ምርጥ የተቆረጠ ልብስ ለብሰሽ ይሆናል፡ ከሱፍ የተሠሩ ምርጥ፡ እንደዚህ መልበስ ግን ለእግዚአብሔር ቅዱስ መሆን አይገባም።

217 [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—እርታዒ።] ኦህ፡ አዎን፡ ይህ በእግዚአብሔር ልጆች የለም።

218 "ኧረ፡ ተው እንጂ፡" ይላሉ። እንዴ፡ ይላሉም፡ "ቤተ ክርስቲያናችን... " በደንብ-ለብሳችኋል? ነበርን አሉ። "ምንም የማያስፈልጋቸው፡ ባለጸጎች" ነበሩ። አዎን። እንዴ፡ ይላሉ፡ "ፓስተራችን ሳይቀር ትልቅ እና የሚያምር ካባ ይለብሳል። መዘምራን ሁሉ ታላቅ ካባ ለብሰው ይወጣሉ።" ሰይጣን ከሥር

ይንከባለልበታል። ኧሃ-ሃም። ኧሃ-ሃም፡ ትክክል ነው። ኦህ! እህም፡ እህም! እሺ፡ ምንም ባልናገር ይሻለኛል። ምናልባት፡ ያኛው እንዳይሄድብኝ። እሺ።

219 ኦህ፡ እነዚህ ሁሉ ታላላቅ ነገሮች! ያጌጡ ኳየሮች፡ ስለዘመሩ የሚከፈላቸው፡ ቅጥረኞች ኳየሮች። እህም። ሰባኪውን አብዝተው ካልከፈሉት የተሻለ ክፍያ የሚከፍለውን ሌላ ከፋይ ፍለጋ ይወጣል። ባለአደራውን ቦርድ በአንድነት ጠርቶ እንዲህ ይላል፡ “አሁን፡ ወንድሞች ሆይ፡ እ—እ... ለእኔ በጣም ደጋጎች ነበራችሁ፡ በሳምንት **ብዙ-መቶ** ትሰጡኝ ነበር፡” ወይም ሌላ እንደዚህ ያለ ነገር ይላል። “ሌላኛው የፕሪስባይቴሪያን ቤተክርስቲያን ግን... ” (“ጴንጤቆስጤ” ወይም ሌላ ብላችሁ ጥሩት።) “እነዚያ ማዶ ላይ ያሉት፡ እነሆ ከዚህ **እጅግ-በበለጠ** እንደሚከፍሉኝ—ቃል ገብተውልኛል።” ኦህ፡ ማይ!

220 ታዲያ ምስኪን ቅዱሱ ምን ይዋጠው? ምን ምርጫ ይኖራቸዋል? በመንፈስ ቅዱስ የተሞላች አንዲት ድሃ ትንሽ ቤተ ክርስቲያን ምን አላት፡ ምን ምርጫ ይኖራቸዋል? ያን ያህል የመክፈል አቅም አይኖራቸውም። ስለዚህ ጌታ ራሱ አንዱን ያስነሳላችኋል፡ አሜን፡ ያም በራሱ-እጅ የተመረጠ፡ በመንፈስ ቅዱስ ይሞላውና የበላይ ጠባቂ አድርጎ ይሾመዋል። ይልከዋል... “መጥተህ ነጭ ልብስ ከሱ ትገዛ ዘንድ እመክርሃለሁ፡” ብሏል። መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር፡ “ነጩ ልብስ የቅዱሳን፡... ጽድቅ ናቸው።”

221 ስለዚህ፡ አሁን እምነቴ... እስኪ ጉዳዩን ለመመልከት—ወደ 19ኛው ቁጥር እንለፍ። እንደ እኔ እይታ፡ ከ20ኛው ቁጥር የሚጀምር ይመስለኛል። አዎን፡ አዎን፡ በዚህም እንዘጋለን። አሁን፡ አሁን ይህን ስናነበው እጅግ በጽሞና ሁኑ። አሁን ስሙት፦

> **እነሆ፡ በደጅ ቆሜ፡ አንኳኳለሁ፤ ማንም ድምፄን ቢሰማ፡ ደጁንም ቢከፍትልኝ፡ ወደ እርሱ እገባለሁ... ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ፡ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል።**
>
> **እኔ ደግሞ ድል እንደ ነሣሁ ከአባቴም ጋር በዙፋኑ** ላይ **እንደተቀመጥሁ፡** ድል ለነሣው **ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ፡ ይቀመጥ ዘንድ እሰጠዋለሁ።**
>
> **መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን፡ ጆሮ** ያለው **ይስማ።**

222 ይህ በአዲስ ኪዳን ካየኋቸው በጣም አስደናቂ አባባሎች አንዱ ነው። “ደጅ ላይ ቆሜ አንኳኳለሁ፡” እንድታስተውሉት እፈልጋለሁ። ይህ በአጠቃላይ ለኃጢአተኞች፡ ይግባኝ የምንልበት ጥቅስ ነው። ልክ ነው? ኃጢአተኞችን፡ “ኢየሱስ እያንኳኳ፡ ደጅ ላይ ቆሟል” ስንላቸው ኖረናል። እዚህ ጋር ግን ከዚህ ቀደም አብሮ ይጓዝ **ከነበሩት** በኋላ ግን፡ (በድርጅታቸው እና በዓለማዊነት በቅዝቃዜአቸው ምክንያት) ባገለሉት ቤተ ክርስቲያን ደጅ እያንኳኳ ነው። እነሆ ከቤተክርስቲያን ውጪ ነው።

223 አሁን፡ በመዝጊያ ላይ፡ አስታውሱ፡ በቤተ ክርስቲያን ዘመን መጀመሪያ፡ በሰባቱ የወርቅ መቅረዞች (ልክ ነው? )፡ በሰባቱ የቤተ ክርስቲያን ዘመናት መካከል ይመላለስ ነበር። እና እዚህ መጨረሻ ላይ፡ ከየትኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ውጪ ሆኖ እናገኘዋለን? ከሎዶቅያ፡ ሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን። እርሱን፡ ወደ ውጭ እንዲሆን አግ-... አግለውታል። እንዴት፡ ከውጭ ቆሞ ወደ ውስጥ

ለመግባት ሲሞክር ይታያልና። እንዴት ያለ አሳዛኝ ምስል ነው! በራሱ ደም ከገዛት ቤተ ክርስቲያን ውጭ የቆመ፡ የዓለም አዳኝ። አሳፋሪዎች!

224 "ደጅ ላይ ቆሜ አንኳኳለሁ።" ከተገፋ በኋላ ወይም ከተባረረ በኋላ፡ ለመመለስ እየሞከረ፡ እየተሳበ ቀርቦ በሩን ያንኳኳል። በአዲስ ኪዳን ውስጥ እጅግ አስደናቂው ጽሑፍ ይህ ነው። ከዚህ የበለጠ የሚያሳዝን ነገር እንደሌለ አስባለሁ፡ የዓለምን አዳኝ ከገዛ ቤተ ክርስቲያኑ፡ ከሎዶቅያ ዘመን ወጥቶ ማየት ያሳዝናል። ያደረጉትን ሁሉ እና ሃብታቸው እና ነገሮቻቸውን በሙሉ፡ እንዲሁም ማንነታቸውን ከነገራቸው በኋላ፡ ማለት እንዴት ለብ ያሉ እንደሆኑ ወዘተረፈ፡ ሊተፋቸው አልወደደም... እነርሱ ራሳቸው—እነርሱ... .ራሳቸው፡ ተፍተው አሰወ**ጡት**። እነሆ አሁንም ይህ ነው፡ ተመልሶ ለመግባት እየሞከረ፡ ደጁ ላይ እያንኳኳ ነው። ለምን? የዘላለም ሕይወት እንዲሰጣቸው። በቀራንዮ የገደሉት እነርሱን፡ ነፍሳቸውን ለማዳን እየሞከረ ነው። በህይወቴ ካየሁት፡ ካሰብኩት ሁሉ ይልቅ በጣም አሳዛኝ ምሰል ያ ነው።

225 ተገለለ! የተገለለው ከምንድነው? ወዳጆች ሆይ፡ አሁን፡ ስሙኝ። አይደንቅም ወይ! እስኪ ሳሉት፡ ወደ ልባችሁ ውስጥ ዘልቆ ይግባ። መድኃኒታችን፡ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ፡ ከራሱ ሕዝብ ተገለለ። የተጠላ ሆነ፡ ተገለለ። አለም እርሱን እግሎ ሰቀለው። አሁንም፡ ከገዛ ቤተክርስቲያኑ፡ ተገለለ። ከእንግዲህ አይፈለግም፡ እሱ አላሰፈለጋቸውም። የሒይማኖት ተቋም ስለነበራቸው፡ አልፈለጉትም። ጳጳስ አለላቸውና፡ ከእንግዲህ እሱን ለምን ይፈልጉታል? ሊቀ ጳጳስ፡ የበላይ ተመልካች አለላቸው፡ ከእንግዲህ መንፈስ ቅዱስ ጥቅም አልባ ነው። ከእንግዲህ አያስፈልጋቸውም። ክርስቶስ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ እሱን አላሰፈለጋቸውም። ስለዚህ እነሱ...

226 እኔ እሱን ስላላወቁት፡ ተነሰተው ጣሉት ብየ አላምንም። ስለሱ መዝሙር ይዘምሩለት ነበርና፡ ስላላወቁት አይደለም። ሰባኪው አሁንም ስለ እርሱ ይናገር ነበር፡ ስለዚህም እርሱን ስላላወቁት አይደለም። ነገር ግን የራሳቸው ዓለማዊነት እና ድርጅታቸው፡ መደራጀታቸው፡ "የተአምራት ዘመን አልፏል **እንዲህ** እና **እንዲያ** ያለ ነገር የለም፡" ማለታቸው ነው።

227 ልጠይቃችሁ። (የታሪክ ምሁራን፡ ለሆናችሁ) ከዚህ በፊት የነበሩ ሪቫይቫሎች በሙሉ፡ ማለት፡ በእነዚህ ሁሉ፡ በእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ፡ የነበሩ ሪቫይቫሎች በሙሉ፡ ሁ... ሁልጊዜ ከድርጅት ውጪ የነበሩ ናቸው። ሪቫይቫሉን ያስጀመረ ማንኛውም ሰው፡ ከድርጅቶቹ ውጭ የነበረ ነው። እና በእያንዳንዱ ጊዜ የሚነሱ—ሪቫይቫሎች፡ በልሳን በመናገርና በፈውስ የመናገር ምልክትና ተአምራት ነበራቸው፡ እንዲሁም እንደዚያ የመሳሰሉ ነገሮች፡ ያስከትላሉ። መሰራቹ እንደሞተ ያን ጊዜ፡ አደራጅተው ድርጅት ያቋቁማሉ፡ ወዲያውም "ይሞታሉ" ከዚያ በኋላ እግዚ አብሄርም ዞር ብሎ አያያቸውም። ይህ ትክክል ነው።

228 አሁንም በመጨረሻው የቤተክርስቲያን ዘመን ላይ፡ ሁሉን ቻይ አምላክ፡ እነሆ ከውጭ ቆሟል። ያን—ሳሰበው ራሱ ልቤን ይሰብረኛል። ጌታዬ በገዛ ቤተ ክርቲያኑ ደጅ አፍ ቆሟልና፡ በአለማዊነት እና በቀዝቃዛነት እና በሒይማኖት ተቋም እና በግዴለሽነት ከተገፋ በኋላ፡ ተመልሶ ለመግባት እየሞከረ፡ ከበሩ

ውጭ ቆሞ፡ ያንኳኳል። ቀደም ብዬ፡ ይህን ሳስብ፡ ጠረጴዛዬ ላይ ተደግፌ ማልቀስ ጀመርኩ። አሰብኩት...

229 ብዙ ጊዜ አሰበዋለሁ፡ ኢየሱስ በዚያ ፈሪሳዊ ቤት ተቀምጦ ሳለ፡ እግሮቹ አቧራ ለብሰው፡ እሱን ትኩረት ያደረገለት ሰው አልነበረም። በር ላይ አልተቀበሉትም እግሩን አላጠቡትም ቅባትም አልቀቡትም፡ ይሄድበት ከነበረውን መንገድ፡ ልብሱ ከሚጎትታቸው ጋር እስከነ ፍጉ እና ሌላው፡ ፈረሶች እና ሌሎች ነገሮች ከሚጓዙባት መንገድ ነካክቶት መጣ፡ ያን—ያን ሁሉ ጠረን ሁሉ ነበረው።

230 ያኔ እግር ማጠብ፡ የዘወትር ባህላቸው ነበረ። እና እግር-አጣቢ ባሪያዎች ደጅ ላይ ይቆማሉ። ሰው ሲመጣ፡ እግር ያጥቡ ነበር፡ ከዚያም ይሄዱና የእንግዳውን እግር ልክ ሰንደል ያመጣሉ፡ ያጠልቁላቸው ነበር። ከዚያም ራሱን በዘይት ይቀቡታል... መልካም መዓዛ ያለው ሹቱ ያርከፈክፉበታል፡ ከጸሐይ ጨረር የተነሣ የከሰለው አንገቱ ላይ ይደረጋል፡ ጸጉሩ ይበጠርለታል። ከዚያ በኋላ ይገባል።

231 እና የእንግዳው የእንኳን ድህና መጣህ አቀባበላቸው፡ እንዲህ ነበረ... ፓት፡ አንዴ እዚህ ጋር ቁምልኝ፡ አንድ ነገር አሳያችኋለሁ። የእንኳን ደህና አቀባበላቸው፡ እንዲህ ነበረ። አሁን፡ እንደሚመስለኝ... አይደለም፡ እንዲህ ነው፡ ሰርዓቱ በዚህ መልኩ ይመስለኛል፡ **እንደዚህ** እንኳን ደህና መጣችሁ ለመባባል፡ አያችሁ፡ ይተቃቀፋሉ። ያን ጊዜ እንኳን ደህና መጣህ ተባለ።

232 በጴንጤቆስጤ በዓል እንደመጣ፡ ኢየሱስ ወደዚያ ግብዣ በመጣ ጊዜ ግን፡ እሱን ያልተረዳ ሰው ነበረ። ቢሾፑም ሌሎቹም ሁሉ በዚያ ነበሩ፡ በገዛ ጉዳዮቻቸው ላይ እጅግ ተጠምደው ነበር። ኢየሱስም ተጋብዞ ነበር ይሁን እንጂ እግሩን ያጠበው ሰው አልነበረም። በዚያም በማእዘኑ በኩል ተቀምጦ ነበር፡ በዚያም እንዳለ ትዝ አላላቸውም፡ እግሩ ቆሽሿል፡ ዙርያው ሁሉ አቧራው፡ አፈር ነበረ።

233 በዚያም በሰፈሩ ጎዳና ላይ አንዲት ጋለሞታ ሴት ነበረች እነሆ እሷም ወዳዛ መጣች፡ ቦርሳዋ ውስጥ ጥቂት ገንዘብ ብቻ ነበራት። እርሰዋም ተመልከተችውን እና ኢየሱስን በዚያ በቆሸሸ እግሮች ተቀምጦ አየችው። ልቧ ተሰበረ። እንዲህ ብላ አሰበች፡ "ይህ ሰው ኃጢአቷን ይቅር ያለላት ሰው ነው። ይፈውሳል ሲባል የሰማሁት ሰው ይህ ነው። ለምን ትኩረት አይሰጡትም? "

234 ኤጲስቆጶሳቱና ሁሉም በዙሪያው ነበሩ፡ እሱን ግን አግለውት ነበርና። በዚያም... እንዲመጣ የጋበዙት እነርሱ ናቸው።

235 እኛም እንደዚያው ነን። ወደ ሰብሰባዎቻችን እንዲመጣ እንጋብዘዋለን፡ ሲመጣ ግን በእርሱ እናፍራለን። "እረ፡ እኔስ ተነስቼ'ማ 'ጌታ ይባረክ' አልልም። እረ፡ አልልም፡ እነ ጆኒዎች በዚያ ተቀምጠዋል፡ ወንበር-ሰባሪ ነው ብለው ቢያስቡኝስ።" አንተ ግብዝ! በትክክል። "በልሳኖች እንዳልናገር እፈራለሁ 'የልሳን ሰው' ይሉኛልና።" አንተ ምስኪን ጎስቋላ ነህ!

236 አሁን፡ አስታውሱ፡ ይህ ይገባል፡ አያችሁ። ምስኪን፡ ጎስቋላ፡ ድሀ፡ እርቃን፡ እና ዕውር ነህ፡ ግን አታውቀውም።

237 ኢየሱስ ባልታጠበ እግሩ ቁጭ ብሏል። ጎዳናው ላይ ጋለሞታዋ፡ ስትወርድ እያታለሁ፡ እስኪ ለአንድ ደቂቃ ያህል እንውሰዳት—እና እስኪ... እንነጋገርባት። ወደ ሱቅ ስትወርድ እያታለሁ፡ እና እንዲህ አለች "እ... " እንባዋም ፊቷ ላይ መፍሰስ ጀምሯል፡ እንዲህ ትላለች፡ "ይ—ይህ ቢቀርብኝ ይሻላል። ይህ ዕቃ ወደዚያ ከወሰድኩ፡ ገንዘቡን ከየት እንዳመጣሁት ያውቅብኛል። እንዴት እንዳገኘሁት ያውቃል፡ ያለኝ ግን ይህ ብቻ ነው።"

238 እሱም የሚፈልገው ያ ብቻ ነው። የሚፈልገው ያ ብቻ ነው። ተመልከቱ? ግድ የለውም። "በእጄ ምንም የለኝም፡" እያላችሁ ብቻ ኑ።

239 ትንሽ ቅባት አገኘች እና ገዝታ አመጣች። ወደ ቦታው ደረሰችና እና አሰበች፡ "አቤት፡ እሱን ብቻ ባየሁት!" እና ሾልካ ገባችና በሩ አጠገብ ቆመች።

240 እነሆ፡ እንኳን ደህና መጣህ፡ አላሉትም ነበር። የአልባስጥሮስ ቢልቃጥ ወሰዳ ሰበረችው እነሆ... በእግሩ ስር አስቀመጠችው፡ እግሩንም ማጠብ ጀመረች። ማልቀስ ጀመረች፡ "ኦህ፡ እሱ ራሱ ሳይሆን አይቀርም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሁል ጊዜ ያነበብኩት ሰው ይህ ነው። እንደሚያውቅልኝ አውቃለሁ።" የመጀመሪያ ነገር ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ... እንዴት ያለ ውኃ ለእግሩ፡ የንሰሓ እንባዎች በእግሩ ላይ ተንጠባጠቡ። እግሩን የምትጠርግበት ምንም ጨርቅ አልነበራትም፡ እጇን ዘርግታ ፀጉሯን ያዘች። ቆንጆ ጥቅልል ጸጉሯ ሁሉ ዝርግፍ አለ፡ እንባዋም በፊቷ እንዲህ ይወርዳል። እግሩን አጠበች፡ እየቆየች፡ "**ትስመዋለች**፡" እግሩን እየሳመች፡ እንዲሁህ እግሩን ታጥበው ነበር።

241 ኢየሱስ የቆሸሹ እግሮች ያሉት፡ ስለሱ ማንም ትኩረት የሰጠው የለም። ዛሬ ደግሞ ሆሊ-ሮለር የተባለ የቆሻሻ ስም ተሸክሟል፡ **እንዲህ የመሳሰሉ ሌላ** ጭምር፡ ሰዎች ስለ እርሱ ለመቆም ሐሞት የላቸውም!

> የተቀደሰውን መስቀል እሸከማለሁ፡
> ሞት ነፃ እስኪያወጣኝ ድረስ፡
>
> ስለ ጌታ ከተናቁ ከጥቂቶች ጋር እጓዛለሁ፡
> አሻግረኝ፡ ጌታ ሆይ፡ ከኢየሱስ ጋር ጀምሬአለሁ።

242 ጌታ ሆይ፡ ምንም ዋጋ ቢያስከፍለኝም፡ አሻግረኝ፡ እንደ ያዕቆብ፡ የድንጋይ፡ ትራስ፡ አለኝና። ምን ልዩነት ይፈጥራል? እሱ ለኔ ያደረገልኝ!

243 እና ይህች ምስኪን ሴተኛ አዳሪ፡ እያለቀሰች፡ ታነባለች። መጀመሪያ የሆነው ነገር፡ እነሆ ስምኦን ተነሣ፡ ይህ እንዲመጣ የጋበዘው ሰው፡ እንዲህ ማለት ጀመረ፡ "አይይ፡ አይይ፡ አይይ፡ አይይ! ይህ ነብይ መሆኑን እና አለመሆኑን ያሳያል፡ ምን አይነት ሴት እንደነበረች ባወቀ ነበርና።" ግብዝ!

244 ስለዚህ ከጨረሰች በኋላ... እነሆ ኢየሱስ እግሩን አላንቀሳቀሰም፡ ቁጭ ብሎ እያየ ትኩር ብሎ ያያታል። አቤት፡ ደስ ይላል። አንዳንዴ እኛ በምናደርጋቸው ትልልቅ ነገሮች ሳይሆን፡ ሳይሰሩ በምንተዋቸው ትንንሽ ነገሮች ነው። እሷን ትኩር ብሎ፡ ትኩር ብሎ እያያት ተቀምጧል። ለሱ ትኩረት የሰጠው ሰው አልነበረም፤ በስተመጨረሻ ግን፡ በእንባዋ እግሮቹን ማጠብ ስትጀምር፡ አትኩሮት ማድረግ ጀመሩ፡ የህዝቡን ቀልብ ሳበ። ምንም ቃል ሳይተነፍስ፡ ትኩር ብሎ ያያት ነበር።

245 ሽማግሌው ስምኦን ቆሟል፡ እንዲህ ማለት ጀመረ፡ “እህም! ነብይ መሆኑን አለመሆኑን አያችሁ፡ አይደል? ነግሬአችሁ ነበር! ነግሬአችሁ ነበር! ነብይ ቢሆን፡ ሴቲቱ ማን እንደሆነች ያውቃት ነበር። አያችሁ፡ የሰፈሩ ትልቁ ቤተ ክርስቲያን እኛ ነን፡ አያችሁ፡ ስለዚህ፡ እኛ እናውቀዋለን። ነብይ አለመሆኑን እናውቀዋለን፡ ቢህንስ ያውቅ ነበርና።”

246 ከ... ከጨረሰች በኋላ፡ የንሰሐ እንባዋች በፊቷ ፈሰው፡ የኢየሱስን እግር አጥባ ጨረሰች። እነሆ... አሁን ትንሽ ምቾት የተሰማው ይመስለኛል።

247 አምላክ ሆይ፡ እዚያ ብሆን ኖሮ ደስ ይለኛ ነበር! እኔም እንደገና ባጠብኳቸው ነበር። አዎን፡ ጌታዬ።

248 አቤት፡ በዚህ ዘመን ላለች አንዲት ሴት ልጅ በገዛ ጸጉሯ እግር ማጠብ አይከብዳትም ነበርን? ይሄን ለማድረግ በራሷ መቆም ይጠይቃታል፡ እንዲሁም በቂ ጸጉር ሊኖራት ይገባል። አዎን፡ ጌታዬ፡ ይቆራርጡታልና።

249 በዚያ ግን፡ ስለ ኢየሱስ እግር፡ ግድ ያለው አልነበረም... (ወሳኝ ነው)፡ ከነ እግር ቆሻሻው፡ ተዋርዶ ቁጭ ብሏል። እሷ አጠበችው። ያን ከፈጸመ—ከፈጸመ በኋላ፡ “በጣም ጥሩ፡” እንደ ማለት አየት አደረጋት።

250 ማዶ ላይ አየና፡ እንዲህ አለ፡ “ስምኦን ሆይ፡ የምልህ ነገር አለኝ። አንተ ወደዚህ ጋበዝከኝ፡ በር ላይ አልተቀበልከኝም። እግሬን የምታጠብበት ምንም ውሃ አልሰጠኸኝም። ሰገባ ራሴን ከቶ አልቀባኸኝም፡ የፀሐይን ቃጠሎ ከላዬ ላይ አላነሳህም። ሰገባ እንኳን ደህና መጣህ ብለህ አልሳምኸኝም። ይቺ ምስኪን ሴት ግን፡” (ኦህ፡ ማይ።) “ይህች የውጭ ሰው፡ የመንገድ ላይ ጋለሞታ፡ እግሬን የምታጥብበት ውሃ አጥታ በእንባዋ አጠበቻቸው። የምትጠርግበት ነገር ስለሌላት፡ ፀጉሯን ተጠቀመችና፡ ጠራረገቻቸው። ያለማቋረጥ እግሬን ትስመኛለች። አሁን ልነግርህ፡ ብዙ የነበረው፡ ኃጢአቷ፡ ተሰርዮላታል።” ትክክል፡ የእሱን በተመለከተ አንዳች አላለውም። “ብዙ የሆነውን፡ ኃጢአትሽ፡ ተሰረየልሽ።”

251 ዛሬ ደግሞ ኢየሱስ፡ ከጴንጤቆስጤ ድርጅቶች፡ ከባፕቲስት ድርጅቶች በር ውጪ ቆሞ፡ ከሜቶዲስት ድርጅቶችም እንዲሁ፡ በድጋሚ ወደ በዓለ ሃምሳ ለመመለስ እየሞከረ፡ ህዝቡ ግን እንዲሁ እያለፈው ይገኛል። ዓለማዊነታችሁ እና ሌሎች ነገሮቻችሁ ገፍተው ካስወጡት... በኋላ፡ እንደገና ለመግባት እየጠየቀ፡ እና እየሞከረ፡ ቆሟል። እና፡ አቤት፡ በህይወቴ ካየኋቸው አሳዛኝ ነገሮች ጥልቁ ይህ ነው። አላስፈለጋቸውም! እነሆ፡ እርሱ፡ ለመግባት ፈልጎ፡ ከውጭ ቆሞ ያንኳኳልና። አሁንም ለማድረግ እየሞከረው ያለው ተመሳሳይ ነገር ነው። ለምን? ለምን? ከውጭ ስለሆነ።

252 ፈጽመው አላባረሩትም። አሁንም ስለ እርሱ ይዘምሩለታል፡ ስለ እርሱ ይሰብካሉ፡ በመገኘታቸው አጥተውት አያውቁም። ይህ ልክ ነው። በትክክል እየሄዱ ነበር። ለምን? እይታቸው የቅርብ ርቀት ስለነበረ። ትልቅ ሕንፃቸውን ይመለከቱ ነበር። ሀብታም ነበሩ። የነበራቸውን ታላላቅ ድርጅቶች እያዩ፡ እሱን ለመገንባት እየሞከሩ ነበር። ተጨማሪ አባላት እንዲገቡ ይሰራሉ፡ እሱን አላጡትም። አይ፡ አላጡትም። በልሳኖች መናገር አላጡትም። ልብን ቆራርጠው ልብን የሚገርዙ ታላቅና ኃይለኛ የሆኑ፡ የእግዚአብሔር መልእክቶች

አላጡም፡ የዓለምን ነገር ቆራርጦ እንደ ቦቆሎ ቅንጣት የሚልጣቸው አላጡም። ኦህ፡ እነዚህ ሁሉ...

253 በቤተ ክርስቲያናቸው እንደዛ ከሰበካችሁ ግን ያባርሯችኋል። መንፈስ ቅዱስ የሰበከውም በዚህ መንገድ ነው። ኢየሱስም፡ “እናንተ የእፉኝት ልጆች! እ—እናንተ የሳር ውስጥ እባቦች!” ዮሐንስም፡ እንዲሁ አደረገ፡ ባለ ታላላቅ ቅባት የሆኑ ሰዎች ሁሉ፡ የተደበቁበት ሁሉ ገላለጠባቸው። በትክክል።

254 ያ ስላልነበራቸው ግን፡ እሱን አልናፈቃቸውም። አያችሁ? ጀርባቸው እንዲህ እያሻሸ እንዲህ የሚላቸው አንዳች አበባ መሳይ ነገር ስለ ነበራቸው፡ “ብቻ ናና ህብረት አድርግ፡ ስምህንም አስመዝግብ፡ ከዚያ—የአባልነት ማረጋገጫ እናወጣልሃለን። ሂድና ወረቀትህን ከሌላኛው ቤተ ክርስቲያን ይዘህ ና እንቀበልሃለን፡ እና—ወዘተ። አሁን፡ ብቻ በዓመት ሰንት ለመክፈል ቃል ትገባለህ?” አያችሁ፡ ይኸው ነው፡ “ሃብታም፡ ምንም የማያስፈልገው።” ኦህ! የሚያስፈልግህ ታላቅ ነገር አለ ገና አላገኘኸውም፡ ኢየሱስ ከውጭ ቆሞ ወደ በዓለ ሃምሳ ለመመለስ እየፈለገ ነው።

255 መንፈስ ቅዱስ በቤተክርስቲያኑ ላይ ቢወርድ ዛሬ ማታ በሜቶዲስት ቤተክርስቲያን ውስጥ ምን እንደሚሆን ይመስላችኋል በመጮህ፡ በመዝለል፡ በልሣን መናገር እንደሰከረ ሰው ቢመስሉ... የሰከሩ ሰዎች ቢመስሉ ምን ይሆን ነበር? እንዴ፡ ኮንፈረንሱ—የሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያንን ከኮንፈረንስ ያሽቀነጥራታል። ታውቃላችሁ። በባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቢከሰት ምን ይሆናል? ተመሳሳይ ነገር። በጴንጤቆስጤዎች? ለምን፡ ብዙዎቹ ላይ፡ ተመሳሳይ ነገር። በትክክል። አዎን፡ ጌታዬ፡ ትርጉም አልባውን ነገር አይታገሱትም። “እንዴ፡ አዲሱ ምንጣፋችን ሳይቀር አበላሹብን፡” ባሉ ነበር። ኧሃ-ሃም፡ በትክክል። ማይ! ማይ! ምንኛ ጎሰቋሎች ስብስብ ናቸው። እውነት ነው።

256 አዎን፡ እሺ፡ ያኔ አብሯቸው ነበረ፡ በሰባቱ የወርቅ መቅረዞች መካከል ከእነርሱ ጋር ተመላለሰ። መልሱ ይህ ነው፥ የሐይማኖት ተቋሞች እና ዓለማዊ ነገሮቻቸው፡ ቢሾፖቻቸው፡ ካርዲናሎቻቸው፡ ዓለማዊነታቸውም ሁሉ፡ እርሱን አወጣ እና እርሱን ፈጽሞ አልናፈቃቸውም። እና ቤተ ክርስቲያንም...

257 አሁን፡ እሱን ለመመለስ ምን እናደርጋለን? አሁን ከጴንጤቆስጤ ቤተክርስትያን ውጭ ከሆነ፡ እሱን ለመመለስ ምን እናድርግ? እርሱን ለመመለስ የህዝቡን የድምጽ ምርጫ ይመልሰዋልን? አዲስ ጳጳስ፡ አዲስ ካርዲናል መምረጥ ያስፈልግ ይሆንን? ወይም ምናልባት አዲስ—አዲስ—የሐይማኖት ተቋም መመስረት። ያ በጭራሽ አያስፈልግም! በፍጹም መፍትሔው አይደለም። አዲስ የሐይማኖት ተቋም፡ እና አዲስ—ካ—ካ—ካ—ካ—አዲስ ካርዲናል መፍትሄ አይደለም፡ አዲስ ፓስተር መፍትሄ አይደለም፡ ጥሩ-ደመወዝ ተከፋይ ወንጌላዊ መፍትሄ አይሆንም። ከእናንተ ከራሳችሁ በበለጠ ሌላ ሊሆን የሚችልበት በዓለም ላይ አታገኙም። እሱን እንዴት እንመልሰዋለን? በምርጫ አይደለም። አይደለም፡ ጌታዬ። ኢየሱስን በምርጫ ኣንመልሰውም፡ እርሱም ኣይመጣልንምና።

258 እነሆ—እነሆ እንዲህ ነው፡ “ማንም ድምፄን ሰምቶ በሩን ቢከፍትልኝ።” አሁን፡ በሩ ምን እንደሆነ እናውቃለን። “ማንም ድምጼን ሰምቶ፡ ደጁንም

ቢከፍትልኝ።”

259 “ማንም ቤተ ክርስቲያን… ማንም ድርጅት… ” አይደለም—አይ አይደለም፡ ጌታዬ። በእነርሱ ዘንድ አይሰራም፡ ከጅምሩ የሞቱ ናቸውና። ይጠላዋል፡ ሁሌም አይወደውምና። እጠላዋለሁ ብሏልና! ዛሬ ማታም ይጠላዋል!

260 “ማንም ሰው ግን፡” ማንኛውም የሜቶዲስት ሰው፡ ማንኛውም የባፕቲስት ሰው፡ ማንኛውም የፕሪስባይቴሪያን ሰው፡ ወይም ማንኛውም የካቶሊክ ሰው፡ ማንኛውም የቸርች ኦፍ ጋድ ሰው፡ የናዝሬን ሰው፡ የጴንጤቆስጤ ሰው። “ድምፄን ሰምቶ ደጁንም የሚከፍት ሰው፡ እኔ ገብቼ ከእርሱ ጋር እበላለሁ እርሱም ከእኔ ጋር።” ለጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን መልእክቷ ይህ ነው። የጴንጤቆስጤ ድርጅትን ለማደስ አትሞክሩ፡ ነገር ግን የጴንጤቆስጤውን በረከት በግለሰብ ልብ ውስጥ አድሱት። ብቸኛው መንገድ ይህ ነው። “እኔም ከእርሱ ጋር እራት እበላለሁ፡ እርሱም፡ ከእኔ ጋር።”

261 ታዲያ የቤተክርስቲያኒቱ መልእክተኛ… የቤተክርስቲያኒቱ መልእክት ምን እሰ፡ ምን እሰ—እስተማረን? የመንፈስ እድገት አይደለም። አይደለም፡ ጌታዬ። የመንፈስ ውድቀት፡ ሁል ጊዜ ውድቀት አለብን። እነዚያ ሜቶዲ… የ—የቤተ ክርስቲያን መልእክተኞችና ለእያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን ዘመን የተላለፈው መልእክት የሐይማኖት ተቋምን አውጓል። ለቤተክርስቲያን የተነገረው እያንዳንዱ መልእክት፡ ቤተክርስቲያን ያለማቋረጥ እያሽቆለቆለች እንደነበረች ሲሆን አልሰሙትም። ለ—ለቤተ ክርስቲያን የተላለፈው መልእክት የሐይማኖት ተቋምን የሚያወግዝ ነበር። እናም ስለ እግዚአብሔርም ሆነ፡ ስለ መንፈስ ቅዱስ፡ ምንም የማያውቁ፡ ክርስትያን-ተብዬዎች ድቅል ክርስቲያኖች አደረጋቸው። ዛሬ ማታ በዚህ መድረክ ላይ የቆምኩትን ያህል ይህ ሁሉ እውነት ነው። ከአፉ ለመተፋት የተዘጋጁ፡ ጥሩ እና ለብ ያሉ አባላት።

262 ጳውሎስ ስለ አሕዛብ፡ ቅርንጫፍ ስለመሆናቸው አስጠንቅቆ ነበር። አሁን፡ አንዳንዶቻችሁ፡ ከቻላችሁ፡ ወደ ሮሜ ሰዎች፡ 11ኛ ምዕራፍ፡ ከ 15ኛ እስከ 27ኛው ቁጥር እንሂድ፡ ምናልባት ሁላችሁ፡ ማስታወሻ እንድትይዙ ነው። እና፡ አሁን ስለመሸ፡ ከመሄዳችን በፊት ይህ አንቀጽ እነብላችኋለሁ፡ ምክንያቱ… አሁን፡ መጻፍ ለምትፈልጉ፡ ሮሜ ሰዎች፡ 11፡15 እስከ ሃያ-… እስከ 27። ጳውሎስ፡ ለአሕዛብ፡ ሲነግራቸው፡ ለሮሜ ሰዎች ሲናገር፡ እንዲህ አላቸው፡ “እግዚአብሔር… ” አሁን፡ በቤተ ክርስቲያንን ዘመናት መዝጊያችን ላይ በደንብ አድምጡኝ! ጳውሎስ እንዲህ አለ፡ “እንዲህ ከሆነ… እግዚአብሔር በፍጥረቱ የወይራ ዛፍ ለሆን አልራራለትም፡ ነገር ግን ባለማመኑ ቆረጠው።”

263 ልክ ነው? እንዲቆረጡ ያደረጋቸው ምንድን ነው? በዓለ ሃምሳን ባለመቀበላቸው። ልክ ነው? በበዓለ ሃምሳ ቀን ላይ በመንፈስ ቅዱስ ተሳለቁ።

264 ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ፡ እንዲህ አለ… እንዲህ ብለው ስለ ጠሩት—“ብዔልዜቡል” ስላሉት፡ “ዲያብሎስ ነው፡” ብለው ስለጠሩት፡ እና “ሟርተኛ ነው፡” እና ሌላ ነገር ሁሉ ብለውት ነበርና።

265 እንዲህ አላቸው፡ “እኔ ይቅር ብያቸዋለሁ፡ መንፈስ ቅዱስ በመጣ ጊዜ ግን ስለሱ ክፉ እንዳትናገሩ፤ ስለሱ ክፉ ብትናገሩበት፡ ፈጽሞ ይቅር አይላችሁምና።”

266 እና ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን “ወደ አሕዛብ እንዳይሄዱ፡” ባዘዛቸው ጊዜ ታስታውሳላችሁ። ልክ ነው? “ነገር ግን ወደ ጠፉት የእስራኤል በጎች ሂዱ።”

267 ራሳቸውን እንዴት ኮነኑ? መንፈስ ቅዱስን በመሳደብ፡ የእግዚአብሔርን መንፈስ “ርኩስ ነገር ነው” በማለታቸው ነው። በጴንጤቆስጤ ቀን በመንፈስ እያሸበሸቡ፡ እና ሁሉም ነገር እያደረጉ በነበሩ ጊዜ፡ ተሳለቁበት። እርሱን በተሳለቁበት፡ በዚያች ከተማ ውስጥ፡ ቲቶ በዚያው ውስጥ ገደላቸው ደማቸውም ገደ ጅ ውጭ ፈሰሰ። በዚያው ክፍለ ዘመን፡ የገዛ ልጆቻቸው እና ሌላው ነገር ነገር ሁሉ በልተዋል። እና ትክክል ነው። በአንድ ወቅት ከዓለም ታላላቅ አገሮች አንዷ የነበረች ዝቅተኛ ሆነች፡ እነሆም ወደ አራቱ የምድር ንፋሳት ሁሉ-... ተበታተኑ። ለምን? አለማመን! በአንድ ወቅት ኦሪጂናል ግንድ፡ ኦሪጂናል ዛፍ የነበረች፡ እስራኤል።

268 ጳውሎስ በዚያ አላለምን? ቃሉን የገለጠ ሰው ካለ? ከፍተሃል፡ ፓት? ተነሥተህ ከ15ኛው እስከ 27ኛው ቁጥር አንብብ። [ወንድም ፓት ሮሜ ሰዎች 11:15-27 አነበበ—አርታዒ።]

**[የእነርሱ መጣል ለዓለም መታረቅ ከሆነ፡ ከሙታን ከሚመጣ ሕይወት በቀር፡ መመለሳቸው ምን—ምን ይሆን?]**

**[በኵራቱም ቅዱስ ከሆነ፡ ብሆው ደግሞ ቅዱስ ነው፤ ሥሩም ቅዱስ ከሆነ፡ ቅርንጫፎቹ ደግሞ ቅዱሳን ናቸው።]**

**[ነገር ግን ከቅርንጫፎች አንዳንዱ ቢሰበሩ፡ አንተም፡ የበረሀ ወይራ የሆንህ፡ በመካከላቸው ገብተህ፡ ከእነርሱ ጋር የወይራ ዘይት ከሚወጣው ሥር ተካፋይ ከሆንህ፤]**

**[በቅርንጫፎች ላይ አትመካ። ብትመካባቸው ግን፡ ሥሩ አንተን ይሸከምሃል እንጂ፡ ሥሩን የምትሸከም አንተ አይደለህም።]**

**[እንግዲህ፡ እኔ እንድገባ፡ ቅርንጫፎች ተሰበሩ ትል ይሆናል።]**

**[መልካም፤ እነርሱ ከአለማመን የተነሣ ተሰበሩ፡... ]**

አዳምጡት፡ “አለማመን።” በጣም ጥሩ፡ ቀጥል።

**[... አንተም ከእምነት የተነሣ ቆመሃል። ፍራ እንጂ፡ የትዕቢትን ነገር አታስብ፤]**

**[እግዚአብሔር እንደ ተፈጠሩት ለነበሩት ቅርንጫፎች የራራላቸው ካልሆነ፡ ለአንተ ደግሞ አይራራልህምና።]**

**[እንግዲህ የእግዚአብሔርን ቸርነትና ጭከና ተመልከት፤ ጭከናው፡ በወደቁት ላይ ነው፤ በቸርነቱ፡ ግን ጸንተህ ብትኖር፡ የእግዚአብሔር ቸርነት በአንተ ላይ ነው፤ ያለዚያ አንተ ደግሞ ትቆረጣለህ።]**

**[እነርሱም ደግሞ፡ በአለማመናቸው ጸንተው ባይኖሩ፡ በዛፉ ውስጥ ይገባሉ፤ እግዚአብሔር መልሶ ሊገባቸው ይችላልና።]**

**[አንተ በፍጥረቱ የበረሀ ከነበረ ወይራ ተቆርጠህ፡ እንደ ፍጥረትህ ሳትሆን በመልካም ወይራ ከገባህ፤ ይልቁንስ እነዚያ**

**በፍጥረታቸው፡ ያሉት ቅርንጫፎች፡ በራሳቸው ወይራ እንዴት አይገቡም?**]

እህም!

[**ወንድሞች ሆይ፡ ልባሞች የሆናችሁ እንዳይመስላችሁ፡ ይህን ምሥጢር፡ ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ፤ የአሕዛብ ሙላት እስኪገባ ድረስ፡ ድንዛዜ በእስራኤል በአንዳንድ በኩል ሆነባቸው።**]

[**እንደዚሁም እስራኤል ሁሉ ይድናል፤ እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፡ መድኃኒት ከጽዮን ይወጣል፡ ከያዕቆብም ኃጢአተኛነትን ያስወግዳል፤**]

[**ኃጢአታቸውንም ሰወሰድላቸው፡ ከእነርሱ ጋር የምገባው ኪዳን ይህ ነው።**]

269 ገብቷችኋል? ጳውሎስ ሲናገር፡ "እስራኤል መጥተው የመንፈስ ቅዱስ ምልክቶች አይተው፡ ከተቆረጡ..." አስታውሱ፡ ይህ ሁሉ የጳውሎስን መልእክት ስላልተቀበሉ ነው (በኢየሱስ ስም መጠመቅ፡ ንስሐ መግባትና በኢየሱስ ስም መጠመቅ፡ እማኙን የሚከተሉ ምልክቶችና ድንቆች)፡ አልተቀበሉትም። እነርሱም፡ "እነሆ፡ ወደ አሕዛብ ዘወር እንላለን" አሉ። ልክ ነው?

270 እንየው እስኪ፡ ይህም እንደሚመስለኝ... ለመጀመሪያ ክርስትያን ተብለው በተጠሩበት፡ በኤፌሶን፡ ማለቴ፡ በአንጾኪያ ነበር።

271 እንግዲህ—አሁን፡ የመጀመሪያው ዛፍ፡ ቅርንጫፎቹም፡ የመጀመሪያው ዛፍ—ቅዱስ ከነበረ፡ ጳውሎስ የሰበከውን የጴንጤቆስጤ መልእክት ስላላመኑ (ልክ ነው? )፡ እግዚአብሔር ቈረጣቸውና የበረሃ የወይራ ዛፍን አመጣ (ይህም፡ አሕዛብ እኛ ነን) እነሆ ከዚያ ከ-... ከዛፉ ሕይወት መኖር እንችል ዘንድ እኛን አስገባ።

272 ታዲያ፡ በዚህ ዘመንስ የጴንጤቆስጤውን መልእክት በምንቃወምበት በዚህ ዘመንስ ይህ በቤተክርስቲያን ዘመናት የወረደው፡ እግዚአብሔር ያን የበረሃ ዛፍ ከእርሱ ላይ፡ እንዴት አብልጦ ሊያራግፍ፡ እና ሌላውን መልሶ ሊያገባ ይችል ይሆን? ምክንያቱ እነዚህም ባለማመን ጠንቅ፡ ይቃወሙታል። አሁን ይህ ጥዋት ከተማርነው ጋር አጣምሩት። አሁን የት እንደቆምን ታውቃላችሁ፡ አይደል? የአህዛብ ቤተክርስቲያንን በምንወሰድበት፡ በምትነጠቅበት በመጨረሻ ጊዜ ላይ ነን፤ በአይሁድም ላይ የመንፈስ ቅዱስ መስጠት በሚመጣበት፡ ኢየሱስም ራሱን ይገለጥ ዘንድ፡ መቶ አርባ-አራት ሺህ በሚያትምበት ጊዜ ላይ ነን። ይኸው ነው። የመጀመሪያውን ዛፍ (ወደ በረከት) እንደገና ወደ እስራኤል ማምጣት ነው።

273 ኢየሱስ ከቤታችሁ በር ውጭ ቆሞ ሁል ጊዜ አይንኳኳም። የሚበቃበት እና የሚዞርበት ጊዜ አለ፡ ከዚያ በኋላ እናንተ በተራችሁ ታንኳኳላችሁ ፈጽማችሁ አታገኙትም። ጊዜ ሳላችሁ ኑ። በሚያንኳኳ ጊዜ ኑ። በበዓለ ሃምሳ እንዳደረጉት ከመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ባነሰ ነገር አታመቻምቹ፡ በተመሳሳይ የውኃ ጥምቀት፡ እዚያ ካደረጉትን ተመሳሳይ ነገሮች ጋር አታወዳድሩ። ከዚህ ያነሰ ምንም ነገር በልባችሁ ውስጥ እንዲቀመጥ አትፍቀዱ።

274 አሁን፡ ለእናንተ የካቶሊክ ጓደኞቼ፡ አንድ ነገር ልንገራችሁ፡ በድንግል ማርያም ታምናላችሁ። ድንግል ማርያምም፡ የኢየሱስ ክርስቶስ እናት ሆና፡ በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት ወደ በዓለ ሃምሳ መጓዝ ነበረባት፡ እሷም እንደ ሰከረ ሰው ሆናለች። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከተቀበሉት፡ በአንድ መቶ ሃያዎቹ መካከል እሷም ነበረችበት፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ተሞልታ፡ በልሣኖች እየተናገረች እንደሰከረ ሰው ሆናለች። ድንግል ማርያምም ወደ ክብር ለመግባት ይህን ማድረግ ከነበረባት፡ እናንተስ ከዚያ ባነሰ ነገር፡ እንዴት ትገባላችሁ? አስቡበት። በትክክል።

275 ባፕቲስቶችም... እዚህ ጋር ያለው የባፕቲስት ሰባኪ ለባፕቲስቶችም መነገሩን እርግጠኛ መሆን ይፈልጋል። ይህ ለሰው ሁሉ ነው፡ ማንም ይሁን ማን ግድ የለም።

276 ወደ ቤተ ክርስቲያን መቀላቀል እና የሃይማኖት መግለጫ መድገም፡ እና በየእሁድ ጥዋት ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ፡ አንድም ጥሩ ነገር አይጠቅማችሁም። የምትሳለቁት በእግዚአብሔር ላይ ነው። ወይ እውነተኛ ክርስቲያን ሁን ወይም ምንም አትሁን። ትኩስ ወይም ቀዝቃዛ ሁኑ። እንዲህ ካልሆናችሁ ትገለፋላችሁ... ጥቁር ነጭ ወፍ አይታችሁ አታውቁም... መሆንም አትችሉምና፡ ንቁና ሰካራም ሰው አይታችሁ አታውቁም፡ ቅዱስ-ሐጢአተኛ ሰው አይታችሁ አታውቁም። በፍጹም፡ አላያችሁም፡ ሊሆን አይችልም። ወይ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልታችሁ እግዚአብሔር በእናንተ ይኖራል፡ ወይም ፈጽማችሁ አይደላችሁም። ናችሁ—ወይም አይደላችሁም ነው።

277 ስለዚህ ኢየሱስ—በበራችሁ ውጭ መቆሙን የግድ ማስታወስ አለባችሁ፡ በእነዚህ ቀናት እንዲሁ እንደሚሆን የእግዚአብሔርን ተስፋ ቃል አስቡ፡ በምን ምክንያት? ባለመቀበላቸው። የመጀመሪያ የሆነው ዛፍ፡ እስራኤል እንዲቆረጥ ያደረገው ምንድን ነው? የጳውሎስን የጴንጤቆስጤ መልእክት ስላልተቀበሉ። ይህስ የመጨረሻው የቤተክርስቲያን ዘመን ነው ብላችሁ ታምናላችሁን? መጽሐፍ ቅዱስም ይመሰክራልና! እና ምን ይደርስባቸዋል አለ? የጴንጤቆስጤውን መልእክት ባለመቀበላቸው ይቆረጣሉ፡ እግዚአብሔርም እንደገና ወደ አይሁዶች ይመለሳል።

278 እስራኤልም ሁሉ ይድናል፡ ምክንያቱም እንደ ግለሰብ ሳይሆን፡ እንደ ሕዝብ ስለሚወሰዳቸው ነው። ለእኔ እና ለእናንተ ግን በግለሰብ ደረጃ ነው፡ ምክንያቱ ወደ አይሁድ በመጣ ጊዜ... የሐዋርያት ስራ፡ በሐዋርያት ስራ መጽሐፍ ላይ፡ "ከአሕዛብ ዘንድ ስለ ሰሙ ህዝብ ያወጣ ዘንድ" ማለት ሙሽራ እንዲያወጣ፡ ወደ አሕዛብ መጣ። "ሕዝብ፡" አንድ ከዚህ፡ አንድ ከዚያ፡ አንድ ከወዲያ፡ ከእኛ ጋር በግለሰብ ደረጃ ይሰራል፡ ዘራችን፡ አዋልዳችን፡ ወይም ቀለማችን ምንም ይሁን። ከእኛ ጋር በግለሰብ ደረጃ ይሰራል፡ በመሰውያው አጠገብ የሚያኖረው ጉንጉን አበባው ነው። ከአይሁዶች ጋር ግን፡ ከእስራኤል ጋር እንደ አገር ይሰራል፡ የአገሪቱ ህዝብ ናቸው፡ የእርሱ አገር።

279 ዛሬ ማታ ይህ መልእክት በመሰማታችን ደስተኛ ነኝ። በዚህ በመገኘታችሁ እጅግ ደስ ብሎኛል፡ መገኘታችሁ በእኔ ዘንድ የተከበረ ነበር። ያየሁትን እንድመለከት ስለፈቀደልኝ ሁሉን ቻይ አምላክን አመሰግናለሁ፡ ወደዚች ቤተክርስቲያን ማድረስ መቻሌ ጭምር፡ እና አሁን ከልቤ ተራግፏል። ለተወሰነ

ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በልቤ ላይ አኖረው፡ ማራገፍ ስላልቻልኩ፡ ተሸክሜ መዞር ነበረብኝ።

እንዳደርግ የተሰማኝ ሁለት ነገሮች ናቸው።

280 ወይ ከወንድም ሙር ጋር፡ ጉባኤ ለማድረግ ወደ ሽሬቬፖርት፡ ሉዊዚያና መሄድ። እዚህ የተቀመጠችው ሚስቴ ትናግራችኋለች። ለሳምንታት ያህል አልቅሼ ነበር፡ "ወደ ሽሬቬፖርት መሄድ እፈልጋለሁ። **ለምን**? " በሽሬቬፖርት የነበረ ማንም ሰው **ለምን** እንደሆነ አሁን ማወቅ ይችላል። እንደዚህ ያለ ነገር አይተውም ሰምተው አያውቁም። ከየቦታው ሰባኪዎች፡ ባፕቲስቶች እና የተለያዩ አይነቶች መጥተዋል። አንድ ሰው፡ እጁን በበረዶ ሣጥኑ ላይ ጭኖ፡ መንፈስ ቅዱስም በእርሱ ላይ መጥቶ እንዲህ አለው፡ "ወደ ሽሬቬፖርት፡ ሉዊዚያና ሂድ፡ የምታደርገውን በዚያ ይነግሩሃል።" ሰሜንና የት እንደምገኝ ነገረው… "ምን ማድረግ እንዳለብህ ይነግርሃል፡" አለው።

281 እኔም "ገንዳው ከደረጃዎቹ ሰር በታች ተዘጋጅቶልሃል። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትም ያስፈልግሃል፡" አልኩት። እነሆም…

282 እንደዚህ ያሉ ብዙ ነገሮች፡ ሰዎች ተናግሯል፡ ትንቢትም—ተንብየዋል በመካከላችን የተከሰቱትን ነገሮች አስቀድመው ተናገሩ።

283 እኔም እንዲህ አልኩ፡ "ወደ ጀፈርሰንቪል ሄጄ ይህን መጽሐፍ መጻፍ አለብኝ፡ ለምን ያህል ጊዜ እዚህ እንደምቆይ አላውቅምና። ይሁን እንጂ እኔ ይህን ከገለጽኩት ይህም ወደ ጽሑፍ ከተቀየረ፡ እኔ ከሄድኩ በኋላ ቃሎቹ ህያዋን ይሆናሉ።" በመጽሐፉ ውስጥ ሊካተቱ የሚገባቸው ታሪኮች አቀናጅቻለሁ። እኔም የመንፈስ ቅዱስን ምሪት ለመፈለግ በቤተ ክርስቲያኒቱ ፊትም ለማቅረብ እነሆ መጣሁ፡ ምክንያቱም እኔ ራሴ እነዚህን ነገሮች አላውቃቸው ነበርና። ይህ ሁሉ እውነት ነው። በጌታ ስም እላችኋለሁ፡ እውነት ነው፡ "አላውቃቸውም ነበር።"

284 አሁን እንደተገላገልኩ ይሰማኛል፡ እግዚአብሔር መልእክቱን እንዳመጣን ይሰማኛል። በመንገዱ መጨረሻ ላይ እንደሆንን እምናለሁ፡ የእግዚአብሔር መገለጥ በመካከላችን የሚገለጥበት ጊዜ አሁን እንደሆነ እምናለሁ። ምን ያህል እንደሚዘገይ አላውቅም፡ ሰዓቱ ግን በደጅ ነው።

285 ያ ታላቁ እንዲነሣ እንጠባበቃለን። በእኔ ዘመን ሊመጣ ይችላል፡ በእነዚህ ብላቴኖች ዘመን ሊመጣ ይችላል፡ እኔ አላውቅም። ምናልባትም በመካከላችን ይሆናል፡ ይህ ነው ማለት አንችልም። መንፈስ ቅዱስ እስከዚያ ጊዜ ድረስ ሊመራን ተዘጋጅቷል፡ ከዚያም ይህ መሪ እኛን ሲወስደንም በመንፈስ ቅዱስ የተቀባ ይሆናል፡ ይህም—እርግጥ ነው፡ የሚመጣው፡ ኤልያስ ነው። እርሱ ግን የልጆችን ልብ የሚመልስ መሪ ይሆናል፡ ወይም፡ የልጆችን ልብ ወደ አባቶች መልእክት የሚመልስ፡ በበዓለ ሃምሳ ቀን መንፈሱን ወዳፈሰሰ ወደ ሰማይ አባታችን መልእክት ይመልሰናል።

286 ይህች ትንሿ ድንበር፡ በቻልኩት መጠን በታሪክ እና በመጽሐፍ ቅዱስ እነሆ አምጥቻታለሁ፡ እናም ይህች ነገር በአብያተ ክርስቲያናት ዘመን ላይ መምጣቷን አሳይቻለሁ፡ ይኸው በዚህ ቀን፡ የሐይማኖት ተቋማት በእግዚአብሔር ፊት እርግማን መሆናቸው አሳየኋችሁ። ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ፡ በሐዋርያት ሥራ፡ በታሪክ እና በሁሉም፡ በአእምሮአችሁ እንደሚጸና ተስፋ አደርጋለሁ። ያ…

287 እግዚአብሔርም ቤተክርስቲያኑን ያደራጀበት አንድም ጊዜ የለም። የተደራጁ አብያተ ክርስቲያናት እናት የሮማ ካቶሊክ የስልጣን ተዋረድ ናት። የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን፡ የድርጅቶች እናት ናት። ሪቫይቫል በተነሣበት በማንኛውም የፕሮቴስታንት ቡድን ውስጥ፡ ወዲያውኑ ወደ ኋላ ተመልሰው ተመሳሳይ ነገር ያደርጋሉ። መጽሐፍም "ከእርስዋ የተገኙ አብያተ ክርስቲያናት፡ የራሷ የሆኑ ሴቶች ልጆች አሏት። ጋለሞታ ነች፡" ይላታል። ጋለሞቶች ለመባል፡ ሴቶች መሆናቸው ያስፈልጋልና። ይኸው ይህች ናት። ስለዚህ እኛም...

288 እርሱ ግን እንዲህም ደግሞ ብሏል፡ "አንተ ታናሽ መንጋ፡ መንግሥቱን ሊሰጣችሁ የአባታችሁ በጎ ፈቃድ ነውና፡ አትፍራ።" ስለዚህ በዚያ ቀን፡ እናንተ ሜቶዲስቶች፡ ባፕቲስቶች፡ ማንም ይሁን፡ ሁላችንም፡ "በሩን ከሚከፍት ሁሉ ዘንድ፡ እኔ እገባለሁ ከእርሱ ጋር እራት እበላለሁ።"

289 ወንድሞቼ፡ እህቶቼ ሆይ፡ በዚያ ቀን፡ ከታናሺቱ መንጋ ጋር የተቆጠሩ ያድርገን። ሊወስዳቸው ወደ ዓለም ይመጣልና፡ እርሱ ሲመጣ ከሚጠብቁት የታናሺቱ መንጋ አካል ያርገን። ንጥቀት—ዓለም አቀፋዊ ይሆናልና። "በአልጋው ላይ ሁለት ይተኛሉ፡ አንዱን እወስዳለሁ፡ በእርሻ ውስጥ ሁለት፡ አንዱን እወስዳለሁ።" በአንደኛው የምድር ክፍል ሌሊት በሌላኛው ክፍል የቀን ብርሃን እንደሚሆን ያሳያል፡ አያችሁ። ስለዚህ፡ እነሆ፡ "ሁለት በአልጋ ላይ ይሆናሉ፡ ሁለቱም በእርሻ ውስጥ ይሆናሉ፡" አያችሁ፡ "ከእያንዳንዳቸው አንዱን እወስዳለሁ።"

290 እና ዛሬ ጠዋት እንዳልኩት፡ ከእናትህ ጋር እየተጫወትህ፡ እነሆ መንገድ ላይ እየተጓዝክ ቆይተህ፡ ዙርያህን ስታየው፡ እነሆ እሷ የለችም። ጠረጴዛው ላይ ተቀምጠህ ትጠጣለህ—ቡናህን ወይም ቁርስህን ትመገባለህ፡ ወይም—ወይም የሆነ ነገር ታደርጋለህ፡ እና መጀመሪያ የምታየው ነገር፡ ዙርያህን ስታይ እነሆ ዳዲ የለም። በትክክል እውነት ነው። እየመጣ ነው፡ እና ምን ሰዓት እንደሆነ አናውቀውም። ዋናው ነገሩ ግን፡ አንዴ ከተፈጸመ በኋላ ተፈጸመ ነው፡ ከዚያ በኋላ ምንም ማድረግ አይቻላልችሁም። "ከረጅም ጊዜ በፊት ሰምቼዋለሁ፡" ትላልችሁ። ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ ደግመህ ትሰማዋለህ። እውነት ነው። የጌታ ቃል ነውና ይሆናል። እነሆ፡ አስታውሱ፡ በእነዚህ በሰበኳቸው ስምንት ምሽቶች አንዴ ሳይፈጸም የቀረ ነገር አለን? ነገር ግን—ኢየሱስ እዚህ ጋር የተናገራቸው፡ እነሆ ተፈጸሙ፡ እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን ዘመን እንደተነገረለት ተፈጽሟል።

291 ይህች የቤተ ክርስቲያን ዘመንም፡ በትክክለኛው ሰዓት ወደዛ ስትገባ አይተናታል። ዛሬ ጠዋት እንኳን፡ እነዚያን ደናግል በጥላ ስናስቀምጣቸው፡ የእነዚያ ሰነፎች ደናግል... አሁን፡ አስታውሱ፡ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰነፎቹ ደናግል ሲናገር... ጩኸቱ በተሰማ ጊዜ፡ "እነሆ፡ ሙሽራው ይመጣል" የጌታ መምጣት፡ የቃሉ መሰበክ። ከዚያ ምን ሆነ? "ጊዜው ደርሷል፡ አቶሚክ ቦምቦች እና ሁሉም ነገር ተዘጋጅቷል፡" ሰባኪዎቹ በየመንገዱ እየወጡ መልእክቱን ማሰማት ጀምረዋል።

292 ይህን ባደረጉ ጊዜ፡ ያን ጊዜ ታላልቆቹ አብያት አክርስትያናት፡ ሰነፎቹ ደናግል፡ እንዲህ አሉ፡ "አይ፡ አንዴ፡ እኛ'ኮ ከብዙ ዘመን ጀምረን ፕረስባይቴርያን ነን፡ ምናልባት ጥናት አርገን እንደርስበታለን። አዎን፡ ታውቃለህ፡ መንፈስ ቅዱስ

እንደሚያስፈልገን እናምናለን።" አሁንም እነሆ ፓፍሌቶችን እና ሌላ ነገሮችን አየተጻፉ ናቸው፡ መውጣት ይጀምራሉ። እነርሱም ይላሉ፡ "ጥቂቱን ለእኛ ታካፍሉናላችሁን? "

እነዚያም ይሏቸዋል፡ "አይ፡ ለራሳችን ብቻ የሚበቃ ይዘናል።"

293 ስለዚህ መንፈስ ቅዱስን ለማግኘት እንደ አብያተ ክርስቲያናት፡ ለመጸለይ፡ ወደ ላይ በወጡ ጊዜ፡ የዛሬዎቹ ድርጅቶች፡ እና ታላላቅ አብያተ ክርስቲያኖቹ እንደሚያደርጉት። ዘይት ፍለጋ በወጡ ጊዜ፡ እነሆ ሙሽራው መጣ። ስለዚህ እነዚህ ታላላቅ አብያተ ክርስቲያናት፡ እና ድርጅቶች፡ አሁን ለማግኘት እየጣሩ ይገኛሉ፡ በተደራጁት አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ—ታላላቅ የዓለም አቀፍ ጉባኤዎች ላይ፡ እንዲህ ይላሉ፡ "ወደ ጴንጤቆስጤ በረከት መመለስ አለብን። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መለኮታዊ ፈዋሾች ሊኖረን ይገባል። ልሳን ያላቸው ተናጋሪዎች ሊኖረን ይገባል። የቋንቋ ተርጓሚዎች ሊኖረን ይገባል። በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ እነዚህን ሁሉ መንፈሳዊ ስጦታዎች ሊኖሩ ይገባል፡ ስለዚህ እነዚህ ለማድረግ ጉባኤዎችን መጀመር አለብን።" ያን ለመጀመር፡ ምክር እየተቀበሉ ይገኛሉ። ያንን ለማድረግ ሲሄዱ፡ ሙሽራው የሚመጣው በዚያን ጊዜ ነው ዘይቱንም በመብራታቸው የያዙትን ይዞ፡ ይሄዳል።

294 እነርሱም በመጡ ጊዜ፡ ምን ሆነ? በውጭ ወዳለው ጨለማ ተጣሉ (የታላቁ መከራ ጊዜ) ሙሽራይቱ በገነት ሰትቆይ፡ እነሆ ልቅሶና ዋይታ ጥርስ ማፏጨት ይሆናል። ኦህ፡ ማይ!

295 ከዚያም በዚያ ሦስት ዓመት ተኩል መጨረሻ ላይ፡ ዮሴፍ መጥቶ ራሱን ለወንድሞቹ እንዳስተዋወቃቸው እንዲሁ ያደርጋል። በሁሉም ላይ ለቅሶን ያስከትላል፡ እንዲህም ይላሉ... የእያንዳንዳቸው በየቤተሰቦቻቸው ይከፋፈላሉ፡ እያለቀሱም—እንዲህ ይላሉ፡ "እነዚህ ጠባሳዎች ከወዴት አገኙህ? " የወጉትም—ደግሞ... የወጉትም ሁሉ በአይናቸው ያዩታል፡ ራሱንም ለወንድሞቹ ይገልጣል።

296 አሁን እራሱን ለቤተክርስቲያኑ ለማስታወቅ በሞከረ ጊዜ፡ ወደ ውጭ ገፍተውታል። አሁንም ድረስ ቆሞ፡ እንዲህ እያለ፡ ያንኳኳል፡ "ሌላ የቀረ ሰው የለምን? ገብቼ ከእርሱ ጋር እንድነጋገር የሚፈቅድልን አንድ አለን? "

297 ኦህ፡ ደስ ብሎኛል፡ ስለዚህም አመሰግናለሁ... ከብዙ አመታት በፊት፡ ከሃያ-ሰምንት ዓመታት በፊት፡ ልቤ ውስጥ ሲንኳኳ ተሰምቶኛል። እነሆ በእኔም... እርሱ ገባ፡ ከዚያ ጊዜ ወዲህ እኔ ከእርሱ እርሱም ከእኔ ጋር እንበላለን። የጴንጤቆስጤውን በረከት፡ መንፈስ ቅዱስን ተቀብያለሁ።

298 ለኃጢአቴ ሰርየት በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም ተጠምቄአለሁ። በሕይወቴ የተጠመቅኩበት ብቸኛ ጊዜ፡ አንድ ጊዜ ነው። ገና ከታናሽነቴ ጀምሮ፡ ሶስት አማልክት አሉ ብሎ ሊነግረኝ አልቻለም። በፍጹም፡ ያን አንገቴ ላይ ማሰር አትችሉም። እግዚአብሔር ምን እንደሆነ ለሚያውቅ... ለማንም ሰው ያንን መስጠት አትችሉም። በትክክል። ያኔ ሰጠመቅ... እኔን ያጠመቀኝ የባፕቲስት ሰባኪ ነው። "በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም መጠመቅ እፈልጋለሁ፡" አልኩት። ዶክተር. ሮይ ኢ. ዴቪስ ገና ወጣት እያለሁ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም አጠመቀኝ። አያችሁ? በትክክል። እነሆ አ—አምኛለሁ፡ እምነቴን

ጠብቄአለሁ፡ እውነት እንደሆነም አውቄአለሁ። የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ቃል ነው። ትክክል። ትክክል ነው።

አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።

አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።
አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።

እነዚያ ሰዎች መሃይም ቢሆኑም፡
በዓለማዊ ዝና የማይመኩ፡
መንፈስ ቅዱስ ተቀብለዋል፡
በኢየሱስ ስም ስለ ተጠመቁ፡
በቅርቡ እና በሩቅ ላሉ፡ ዜናውን እያወሩ፡
ኃይሉ አሁንም ብርቱ ነው ይላሉ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ...

299 ደስተኞች ናችሁ? ከሆናችሁ፡ እጃችሁን ወደ ላይ አንሡ።

አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ፤

አንዴ የእርሱ ከሆናችሁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ከኃጢያት ሁሉ በላይ ናችሁ።

ና፡ ወንድሜ፡ ይህንን በረከት ፈልግ
የሚያነጻህም ከኃጢያት ከአመጽ፡
የደስታ-ደወል ይጀምርልሃል
ነፍስህንም ያቀጣጥላታል፤
ኦህ፡ እነሆ በልቤ ይቀጣጠላል፡
ኦህ፡ ክብር ለስሙ፡
አንዱ በመሆኔም ደስተኛ ነኝ።

ኦህ፡ አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ፤ (ሃሌሉያ!)
አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።

በላይኛው ክፍል ውስጥ ተሰብስበው፡
በስሙ ሲጸልዩ፡
በመንፈስ ቅዱስም ተጠመቁ፡
የአገልግሎት ኃይል አገኙ፤
ያኔ ለእነርሱ ያደረገላቸው
ለእናንተም እንዲሁ ያደርጋል፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ...

300 አሁን ፊት፡ ከኋላ፡ እና ዙሪያውን፡ እጅ እንጨባበጥ።

አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ፤

አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።

ኦህ፡ አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስኛ ነኝ፤
አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።

አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ፤
አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።

ከነሱ አንዱ ስለሆናችሁ ደስተኛ አይደላችሁም? [ጉባኤው እንዲህ አለ፡ "አዎን! አሜን! ሃሌ ሉያ!"—አርታዒ።] ደስ ይላል። የአንድነት ድምጽ!

ሽሽ! ሽሽ! [አንድ ወንድም በልሳን ተናገረ፡ ሌላ ወንድም ተረጎመ—አርታዒ።]

301 አባት ሆይ፡ ስለ ቸርነትህ፡ እና ለእኛ ለማይገባቸው ስላረግከው ምህረትህ፡ አቤቱ እናመሰግንሃለን። ለሕዝቡ የተገባው ቃል፡ ጌታ ሆይ፡ መልእክትህን አሁን እንደምታረጋግጥ ስናስብ እናመሰግናለን። እግዚአብሔር ሆይ፡ ምሕረትህ እንዲያድርባቸው፡ እጸልያለሁ።

302 እርሱን እንደ አዳኝ የማያውቅ ሰው እዚህ ካለ፡ እርሱን አሁን በልባችሁ እንደ አዳኝ ልትቀበሉ የምትፈልጉ ሁላችሁ፡ እናንተን በጸሎት ስናቀርባችሁ በእግሮቻችሁ ለመቆም ፈቃደኞች ትሆናላችሁን? አደርጋለሁ እንዳለ... ይህንን መልእክት ሰጠ አሁንም ቃሉን ሊያረጋግጥላችሁ ፈለገ። እርሱን የማታውቁ እና መንፈሱን ያልተቀበላችሁ አንዳንድ እዚህ ካላችሁ፡ አሁን ለእናንተ እየተናገረ ነው።

303 እሺ፡ እዚያ ከኋላ አንድ አለ። ወንድሜ፡ በእግርህ ጥቆም አንዴ? [አንድ ወንድም ተናገረ—አርታዒ።] በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ ይፈልጋል፡ ልክ ነው፡ ወንድሜ? እግዚአብሄር ይባርክህ። ባለህበት ቁም:: ሌላ ተነስቶ "በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ እፈልጋለሁ፡" የሚል ሰው አለ? እግዚአብሔር ይባርክህ ወንድሜ። እግዚአብሄር ይባርክህ። ጥሩ ነው። ባለህበት በእግርህ ቁም። ባለህበት ቁም። መንፈስ ቅዱስን ተቀብሎ መጠመቅ የሚፈልግ ሌላ ሰው ይኖር ይሆን፡ አሁን በጸሎታችን መታሰብ፡ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ ይፈልጋሉ የሚፈልግ ሰው አለ? እኔ ያስተካከልኩትን፡ ከመናገሬ በፊት፡ ቆሞ መካተት እፈልጋለሁ የሚል ሌላ ሰው አለ?

ኦህ፡ ከመንጋው እንደ አንዱ መቆጠር ትፈልጋለህ ወይ?
(ትታዘዛላችሁ? )
በውስጣችሁ ንጹኃን ሁኑ፡ ያንን መልክ ለመሆን ጠብቁ
ትጉ፤
እንደገና ይመጣልና።

304 እንደገና ይመጣልና። ጠላቱ መሆን ወይስ ልጁ መሆን ትፈልጋላችሁ? የተቆጣው አምላክ በሚገለጥባት ማለዳ፡ ከኢየሱስ ደም በቀር ሌላ

አያውቅም። በጭራሽ... የቤተ ክርስቲያን አባልነትህ ለእርሱ ምንም አይሆንም። ደም ብቻ ነው!

> ኦህ፡ ፍጹም ብሩክ ምንጭ
> ኃጢአቴን ያጠበው፤

ረጋ ብለን።

> ሌላ ምንጭ አላውቅም፡
> የክርስቶስ ደም ብቻ ነው።
>
> ኃጢአቴን ማን ያጥበዋል?
> የክርስቶስ ደም ብቻ ነው፤
> ምን ንጹሕ ያደርገኛል?
> የክርስቶስ ደም ብቻ ነው።
>
> ኦህ፡ ፍጹም ብሩክ ምንጭ
> ኃጢአቴን ያጠበው፤
> ሌላ ምንጭ አላውቅም፡
> የክርስቶስ ደም ብቻ ነው።
>
> [ወንድም ብራንሃም **የክርስቶስ ደም ብቻ ነው እያለ** አንጎራጎረ—አርታዒ።]
> የክርስቶስ ደም ብቻ ነው፤
> ጽድቄ ይህ ሁሉ ነው፡
> የክርስቶስ ደም ብቻ ነው።

ሌላ አለ?

> ኦህ፡ ፍጹም ብሩክ...

ምንም አይቋቋማችሁም፡ ወንድም፡ እህቴ። አለም እየሰመጠች ሄዳለች፡ አልቆላታል!

> ... ያጠበው፤
> ሌላ ምንጭ አላውቅም፡
> የክርስቶስ ደም ብቻ ነው።

305 እስኪ፡ ከቻልክ፡ ረጋ አርገህ ቴዲ፡ “የሕይወትን ምንጭ ደም፡ ከአማኑኤል ጎን ሲወጣ እየሁ።”

306 አሁን፡ በእግራችሁ የቆማችሁ፡ ወዳጆች—የጌታን የኢየሱስን ጣፋጭነት ለመቀበል እየሞከሩ ነው። እነዚህ ነገሮች እንደሚሆኑ የሚነግረን ያው መጽሐፍ ቅዱስ፡ እርሱ በገባው ቃል መሰረት እንዲፈጸሙ በትክክል አድርጓል። “እንግዲህ፡ የተሰፋው ቃል፡” አለ ጴጥሮስ፡ “ለእናንተ እና ለልጆቻችሁ እንዲሁም በሩቅ ላሉ ሁሉ፡ ጌታ አምላካችን ለሚጠራቸውን ሁሉ ነው።”

307 የእግዚአብሔርን በረከት በእናንተ ላይ ስለምትፈልጉ ቆማችኋል። እኔም እንደ ባሪያው፡ ስለ እናንተ እጸልያለሁ፡ እግዚአብሔር የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት እንዲሰጣችሁ እጸልያለሁ። ይህን በልባችሁ እንዲኖር አስባለሁ፡ ቅኖች ሆናችሁ፡ በእግዚአብሄር ፊት ቃል ብትገቡ፦ “እግዚአብሔር ሆይ፡ እኔ፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በእግሬ ቆሜ፡ ይህንን የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት

እየፈለግሁ፡ በመንፈስ ቅዱስ እስክትሞላኝ ድረስ እጠብቃለሁ ያለማቋረጥም እጸልያለሁ።" እጆቻችሁን አንስታችሁ ለእግዚአብሔር ያንን ቃል ኪዳን ትገባላችሁን? "በጣፋጭነት፡ እና በመንፈስ ቸርነት፡ እስክትሞላኝ ድረስ ያለማቋረጥ እጸልያለሁ።"

ራሶቻችን ዝቅ እንዳለ ስለ እናንተ ጸሎቴን አሳርጋለሁ፦

308 የሰማይ አባታችን ሆይ፡ እነዚህ የመገኘትህ ፍሬዎች ናቸው። የአንተ ከመሆናቸው የተነሣ እነዚህ ቅላቶች እውነት መሆናቸውን ተረድተዋል። የእግዚአብሔር ቃል ስለሆኑ፡ ከመንፈስ ቅዱስ እንደተሰጡ ያውቃሉ። አንተን ስለመፈለጋቸውም እርግጠኞች ሆነዋል፡ ይህም በሕይወታቸው ውስጥ የማሸነፍ ኃይልን ለመስጠት የመንፈስ ቅዱስ ጣፋጭነት እንደሚያስፈልጋቸው ነው። "ከእርያም ኃይልን ይቀበሉ፡" ክርስቲያናዊ ሕይወት ለመኖር ኃይልን ይቀበሉ፡ ፈተናዎችን ለማሸነፍ ኃይልን ለመቀበሉ። እንደዘመርነው መዝሙር፡ "በላይኛው ክፍል ተሰብስበው በሰሙ ይጸልዩ ነበር፡ በመንፈስ ቅዱስ ተጠመቁ ለአገልግሎትም ኃይል መጣ።" የሚፈልጉት ያ ነው፡ የአገልግሎት ኃይል በእነሱ ላይ እንዲመጣ ነው።

309 እባክህ አባት ሆይ፡ እንደ አገልጋይህ፡ እጃቸውን ሲያነሱ እንዳየሃቸው፡ እለምንሃለሁ፡ ይህን ፈጽመው እንደማይተውት እና ወደ ጎን እንደማይሉት፡ እነሆ ቃል ገብተዋልና፡ ነገር ግን ጌታ ሆይ፡ በሕይወታቸው ውስጥ የቅዱስ መገኘትህን እስኪጠግቡ እስክትሞላቸው ድረስ፡ ይጸልያሉ። ጌታ ሆይ፡ እንደ አገልጋይህ፡ በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞሉ፡ ስለ እነርሱ ጸሎቴን አቀርባለሁ። ጌታ ሆይ፡ ይህ ሳይሆን ከዚህ ቤተ ክርስቲያን እንዳይወጡ እጸልያለሁ፡ እያንዳንዱ ነፍስ በመንፈስ ቅዱስ እስክትሞላ ድረስ እዚህ እንዲሆኑ። አርግልን፡ ጌታ ሆይ።

310 አንተ ሁሉን ቻይ፡ አምላክ ነህ፡ የዓለምን ኃጢአት ታስወግድ ዘንድ በሥጋ ተገልጠሃል። በሦስተኛው ቀን ተነሥተህ፡ ወደ ላይ ዐረገህ። እና አንተ ዛሬ ማታ፡ በመንፈስ ቅዱስ ስም፡ በመካከላችን ነህ። እናም አባት ሆይ፡ አንተ ውድ ጌታችን ሆይ፡ እያንዳንዳቸውን፡ በገዛ አንተነትህ፡ እንድትሞላቸው እንፀልያለን። እንዲሁም እነሆ በሚመጣው ዓለም—ለመንግስትህ በረከት ይሁኑ። አንድ ቀንም በመጨረሻ የመንገዱ ፍጻሜ ዘንድ ሲደርሱ፡ ምናልባት ዛሬም ሊሆን ይችላል፡ መቼ እንደሚሆን እናውቀውም። ነገር ግን ጌታ ሆይ፡ እኔም ደግሞ፡ በመነጠቅ ከሚሄዱት መካከል ልቆጠር። እነዚህም በመነጠቅ ከሚሄዱት ጋር ይሁኑ። እያንዳንዱ ሰው፡ በመለኮታዊ መገኘት እና በመንፈስ የተሞሉ፡ የእግዚአብሔር የሆኑትን ሁሉ፡ በመነጠቅ ይወሰዱ።

311 ዛሬ ማታ እነዚህን ውሰድ፡ አባቴ። አሁን የአንተ ናቸው፡ ለአንተ አደራ እሰጣቸዋለሁ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም። ኣሜን።

312 አሁን ከእነዚህ ሰዎች ጎን የምትቆሙ ሌሎቻችሁን እፈልጋለሁ፡ መንፈስ ቅዱስ ያላችሁ ሰዎች፡ ተነሱ እና፡ እጆቻችሁ ጫኑባቸው።

... የሕይወትን ምንጭ አየሁ፡
ከአማኑኤል ሲወጣ ከጎኑ፡
በየሱስ ደም የታጠቡ፡
ከኃጢአት ይነጻሉ።
ከኃጢአት ይነጻሉ፡

ከኃጢአት ይነጻሉ፤
በየሱስ ደም የታጠቡ፡
ከኃጢአት ይነጻሉ።

ሌባው በሞት አፍ ሆኖ
ያን ምንጭ አየ በዘመኑ፤
እኔም ከእርሱ፡ ብከፋም፡
ኃጢአቴን ሁሉ አጠበኝ።
ኃጢአቴን ሁሉ አጠበኝ፡
ኃጢአቴን ሁሉ አጠበኝ፤
በየሱስ ደም የታጠቡ፡
ከኃጢአት ይነጻሉ።

313 አሁን እጆቻችሁን ወደ እግዚአብሔር አንሡ እና እሱን ብቻ አመስግኑት። እንዲህ በሉት፡ "አመሰግንሃለሁ፡ ጌታ ሆይ። በእግሬ ቆሜ፡ አመሰግንሃለሁ። ስለ በረከትህ፡ ስለ ቸርነትህ፡ እና ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ስለሰጠኸኝ አመሰግንሃለሁ።" ተመስገን፡ ጌታ ሆይ! ተመስገን፡ ጌታ ሆይ! ውድ አምላክ ሆይ፡ ስለሰጠኸን ነገር፡ ተመስገን... እንደተናገርከው፡ ቃልህን ፈጽመሃልና። እናምንሃለን።

314 ደስ አላላችሁምን? "ጌታ ይመስገን!" በሉ፡ ቴዲ፡ አንድ ጊዜ ብቻ... ፍቀድልኝ፡ "ብዙ ሰዎች ይህን እንደማያቁ ተረድተናል... " **ይህ ለእኔ እንደ ሰማይ ነው።**

ብዙ ሰዎች ይህን እንደማያቁ ተረድተናል
ለምን በጣም ደስተኛ እና ነፃ መሆናችን፤
ዮርዳኖስን ማዶ ወደ ከነዓን ውብ ምድር ተሻግረናል፡
ይህ ለእኔ እንደ ገነት ነው።

ኦህ፡ ይህ ለእኔ እንደ ገነት ነው።
ኦህ፡ ይህ ለእኔ እንደ ገነት ነው፤
ኦህ፡ ዮርዳኖስን ማዶ ወደ ከነዓን ውብ ምድር ተሻግረናል፡
ይህ ለእኔ እንደ ሰማይ ነው።

ኦህ፡ ኧረ ደስተኛ ስሆን እዘምራለሁ እልል እላለሁ፡
ዲያብሎስ ይህን አያምንምና፡ እኔ እይቻለሁ፤
እኔ ግን በመንፈስ ተሞልቻለሁ፡ ምንም ጥርጥር የለኝም፡
እና በእኔ ላይ ያለው ይህ ነው።

ኦህ፡ ይህ ለእኔ... እንደ ገነት ነው፡ (እግዚአብሔር ይመስገን!)
ኦህ፡ ይህ ለእኔ እንደ ገነት ነው፤
ዮርዳኖስን ማዶ ወደ ከነዓን ውብ ምድር ተሻግሬአለሁ፡
እና ይህ ለእኔ እንደ ገነት ነው።

315 ደስተኛ አያደርጋችሁምን? በጣም ጥሩ። ከአንድ ሰው ጋር እጅ እየተጨባበጣችሁ፡ "ጌታ ይመስገን!" ተባባሉ፡ ጌታ ሆይ፡ ይህ ለእኔ እንደ ገነት ነው።

የኢየሱስ ስም ከእናንተ ጋር ይሁን፡
የዋይታና የሐዘን ልጆች፡
ደስታ እና ምቾት ይሆንላችኋል፡
በሄዳችሁበት አትለዩት።

ድንቅ ስም፡ ኦህ ውብ ስም!
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ፡
ድንቅ ስም፡ ኦህ ውብ ስም!
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ።

ለኢየሱስ ስም ስገዱ፡
በእግሩ ስር ውደቁ፡
የነገሥታት ንጉሥ እክሊል ያጠልቃል፡
ሩጫችን ሲጠናቀቅ።

ድንቅ ስም፡ ኦህ ውብ ስም!
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ፤
ድንቅ ስም፡ ኦህ ውብ ስም! (ውብ ስም)
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ።

አሁን፡ በጸጥታ፡ አንገታችንን ደፍተን፣

... የኢየሱስ ስም ለዘላለም፡
ከእያንዳንዱ ወጥመድ እንደ ጋሻ፡
ፈተናዎች ሲከቧችሁ፡
ቅዱስ ስሙን ተንፍሱ።

ድንቅ ስም፡ ኦህ ውብ ስም!

60-1211E የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ዘመን
ብራንሃም ተበርናክል
ጀፈርሰንቪል, ኢንዲያና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2024 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings
P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.
www.branham.org